# ሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንግስት

# ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ የህዝብ አስተያየት ጥናትና የኮሙዩኒኬሽን አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት የተጠኑ የስራ መደቦች መዘርዝር

ታህሳስ 2018 ዓ.ም

<u>ሐዋሳ</u>

| የሥራ ዝርዝር መግለጫ ቅጽ | | |
|---|---|---|
| I. አጠቃላይ መግለጫ | | |
| **የመስሪያ ቤቱ ስም** | **የስራ መደቡ መጠሪያ** | **የሥራ ዘርፍ/የሥራ ሂደት** |
| ሲ/ብ/ክ/መ/የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ | የህዝብ አስተያየት፤ ጥናትና የኮሙዩኒኬሽን አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር | የህዝብ አስተያየት ጥናትና የኮሙዩኒኬሽን አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት |
| | | |
| **የቅርብ ኃላፊ የሥራ መደብ /ተጠሪነት** | | |
| | **የሥራ ደረጃ** | **የሥራ ኮድ** |
| ለዘርፍ ኃላፊው | XVII | |
| | | |
| **መስሪያ ቤቱ የሚገኝበት ቦታ** | | |
| **ሀዋሳ** | | |
| II. የሥራ መደቡ ዋና ዓላማ፣ውጤቶችና ተግባራት | | |

2.1. **የሥራ መደቡ ዓላማ፡-**

- መንግስት በሚያከናውናቸው የልማትና የመልካም አስተዳደር ተግባራት ህዝቡ ያለውን አስተሳሰብና አመለካከት እንዲሁም አዝማሚያውን ለመረዳት የህዝብ አስተያየት በመሰብሰብና በመተንተን እና የተገኘውን ውጤት ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ ሲሆን በተጨማሪም የጥናት ስራዎችን በማቀድ፣ የጥናትና ምርምር መረጃዎች በተገቢው መንገድ መሰብሰባቸውን በማረጋገጥ፣ የግኝቶችን ትክክለኛነትና ጥራት በማረጋገጥና ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ የመንግስት አካላትና ሌሎች ተገልጋዮች የተደራጀ የህዝብ አስተያየት ጥናት ውጤቶችን እንዲያገኙ ማድረግ ነው።
- የኮሙኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ አቅም ለመገንባት የሚያስችሉ ጥናቶችን በማድረግ አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶች መዘርጋት፣ሞጅሎችን ማዘጋጀት ስልጠና ፕሮግራሞችን መቅረፅና ስልጠና መስጠት፣ የስልጠናዎችና ልምድ ልውውችን ውጤታማነት መገምገም፣ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ሥራውን ውጤታማ ማድረግ ነው፡፡
-

2.2.**ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት፣**

**ውጤት 1፦ የጥናትና ስራዎችን ማቀድ፣ መምራትና ማስተባበር።**

- የጥናት ስራዎች ያቅዳል፣ የማስፈፀሚያ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ለየጥናት ርዕሶቹ የጥናት ባለሙያዎችን ይመድባል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይደግፋል፤
- የህዝብ አስተያየት ጥናት ሊካሄድባቸው የሚገቡ ወቅታዊ ርዕሰ ጉዳዮችና አጀንዳዎችን መርምሮ ይለያል፣ በእነዚህ ላይ የህዝብን አመለካከት፣ ስሜት፣ እርካታ፣ ቅሬታ፣ ፍላጎትና ዝንባሌ ለማወቅ የሚያስችሉ ጥናቶች እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

**ውጤት 2፦ ለጥናት ስራዎች መረጃ የሚገኝበትን ስልት መቀየስ፤መረጃዎች በተገቢው መንገድ መሰብሰባቸውን ማረጋገጥ።**

- የጥናትና ስራን የሚያሰሩና ወደፊት ያሰራሉ ተብለው የሚገመቱ ተቋማትን ያነጋግራል፣ የስራውን አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ያስረዳል፣ ስምምነት ላይ ሲደረስ ውል እንዲያዝ ያደርጋል፤
- እሴት ባላቸው ክልላዊ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ጉዳዮች ላይ ጥናት እንዲካሄድና የተደራጀ መረጃ ለፖሊሲ አውጪዎችና ውሳኔ ሰጪዎች እንዲቀርብ በማድረግ የጥናቶቹ ተፈላጊነት እንዲያድግ ያደርጋል፤
- የጥናትና ስራዎችን እስፖንሰር የሚያደርጉ አካላትን ያፈላልጋል፣ የማግባባት ስራ ይሰራል፣ በተደረሰበት ስምምነት መሠረት እንዲፈፀም ያደርጋል።
- በጥናትና መካተት ያለባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች /Target group/ በትክክል መለየቱን ያረጋግጣል፤
- ለጥናትና ስራዎች መረጃ ለመሰብሰብ የሚዘጋጁ መጠይቆች ግልፅ፣ አጭርና ቀላል ሆነው የተፈለገውን ዓላማ የሚያሳኩ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤
- መረጃዎች በጥራትና በሚፈለገው መጠን እንዲሰበሰቡ ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል።

**ውጤት 3፦ የጥናትና ግኝቶችን ትክክለኛነትና ጥራት ማረጋገጥና ጥቅም ላይ ማዋል፤አሰራርን ማሻሻል።**

- የጥናትና ስራዎች ሙያዊ ስነ ምግባርና የክልሉ ህግ በሚፈቅደው መሠረት መከናወናቸውንና የተሟሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤
- በጥናት ባለሙያዎች የተሰሩ የጥናት ውጤቶችን የመጨረሻ የእርማት ስራ ይሰራል፤
- በደንበኞች ፍላጎት መሠረት የጥናት ውጤቶች ለምክክር መድረኮች እንዲቀርቡና በተጠኑት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ውይይት ተደርጎ መግባባት እንዲፈጠር ያደርጋል።

- ለመረጃ መሰብሰብና ለትንተና ስራዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በወቅቱ ለይቶ ያስፈቅዳል፣ በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
- ተመሳሳይ ስራ ላይ ከተሰማሩት የሀገር ውስጥና የውጭ ተቋማት ልምድ ይቀስማል፣ ተሞክሮዎችን ይቀምራል፣ በውይይት ዳብሮ እንዲተገበር ያደርጋል፤
- የጥናትና  ስራዎችን ጥራትና ቅልጥፍና ለማሳደግ የሚያስችሉ የአሰራር ማሻሻያ ማኑዋሎችን ያዘጋጃል፣ እንዲተገበር ያደርጋል፤

**ውጤት 4፡- ክልላዊ የኮሙዩኒኬሽንና ሚዲያ ጥናትና ምርምር ስራዎችን ማቀድ፣ መምራት፣ ማስተባበርና መከታተል፡፡**

- ከዳይሬክቶሬቱ እቅድ በመነሳት የጥናት-ምርምር ስራዎች የሚመሩበትን እቅድ አዘጋጅቶ ለባለሙያዎች ያወርዳል፤ ያስተባብራል፣ ተፈጻሚነቱን  ይከታተላል፣ ውጤቱንም ይገመግማል፣
- የሚዲያና የኮሙዩኒኬሽን ኢንዱስትሪን ለማዘመን የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን፣ መልካም አጋጣሚዎችን የሚለይ እና የዘርፉን ስትራተጂክ ግቦችን የአፈጻጸም አቅጣጫዎች የሚያመላክት ፍኖተ-ካርታ በማዘጋጀት የፖሊሲ ምክረ ሃሳብ ያመነጫል፤
- በዘርፉ የጠለቀ የትብብር ምርምሮች እንዲካሄዱ ግንኙነት በመፍጠር ሥራዎችን በአመለካከት፣ ዕውቀትና ክህሎት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይደግፋል፣ ያበቃል፣
- የጥናትና-ምርምር ስራ የሚያከናውኑ በዘርፉ ስር ያሉ የተለያዩ ተቋማት የራሳቸውን ተግባራት በብቃት እንዲያከናውኑ ይደግፋል፣ ያስተባብራል፣
- የዳታ ኢንዱስትሪ ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ፕሮግራሞች በመፈተሽና ፎርማት ቅጾችን በማዘጋጀት ወደ ኮምፒውተር የሚገቡ መረጃዎችን ያረጋግጣል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣ ጥራቱን የጠበቀና አስተማማኝ መረጃ ለተጠቃሚው እንዲደርስ እገዛ ያደርጋል፡
- ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በቡድኑ ስር ያሉ ባለሙያዎችን እንዲሁም ለክልሉ ለጥናትና ምርምር መረጃ ሰብስበው የሚልኩ አካላትን የአቅም ክፍተቶች ይለያል፣ አቅማቸው እንዲጎለብት ያደርጋል፣
- መንግሥት ፈጣን ለውጥ ለማምጣት ከሚያደርጋቸውን ጥረት ጋር ተያይዞ ያሉትን ጉዳዮች በማጥናት የለውጥ መሳሪያዎችን በክልላችን እስከ አሁን ምን ለውጥ እንዳመጡና በተግባር ሲፈፀሙ ያጋጠሙ ችግሮችን ይለያል፤ የመፍትሄ አቅጣጫ እንዲሰጥበት ያደርጋል፡፡
- የባለሙያዎች የስራ አፈጻጸም በየደረጃው ይገመግማል፤ ሪፖርቶችን ያዘጋጃል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል፤
- የሰው ሀይል፣ የማቴሪያልና በጀት እንዲሟላለት የረጅምና የአጭር ጊዜ ዕቅዶችን ነድፎ ተግባራዊ ያደርጋል፤
- የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ለኃላፊዉ ያቀርባል፣

**ውጤት 5፣ በኮሙኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ በምርምር፣ በጥናት፣ በትንተና እና በስርጸት ብቃትና ብስለት ያላቸው ሳይንሳዊና ዘመን ተሻጋሪ ሃሳቦችን ማፍለቅና ማስረጽ፤**

- በቁልፍ ህገ መንግስትታዊ፣ ዓላማዎች፣ መርሆዎች፣ እሴቶች፣ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ስልቶችና ፕሮግራሞች እንዲሁም በሌሎች ወቅታዊ መሠረታዊ ጉዳዮች እና ክልላዊ አጀንዳዎች ዙሪያ የጋራ ብሄራዊ መግባባት መድረስን እንዲሁም ክልላዊ ገጽታችን በተመዘገቡና በሚመዘገቡ ስኬቶች መጠን መታወቁን በጥናት ያረጋግጣል፣
- የጥናትና የምርምር ስራዎች ውጤት ለመንግስት ከፍተኛ ሀላፊዎች ለተለያዩ ባለድርሻ አካላትና ለህዝብ ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል፣ ለግብአትነት መዋላቸውንም ያረጋግጣል፤
- የኮምዩኒኬሽን ምርምሮችና የህዝብ አስተያየት ጥናቶችን በዋና ዋና ክልላዊ ወይም ሰፊ ተደራሽነት ባላቸው የሃገር ውስጥና የውጭ ሚዲያዎች እንዲሰራጩ ያደርጋል፤ ዓውደ ጥናቶችና ምክክሮች ያካሂዳል፤ በክልላዊና በተለያዩ ዓለም አቀፍ ጆርናሎችም ታትመው ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
- መሠረታዊ በሆኑ የክልላችን ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ስራዎች ክፍተቶች ላይ ሙያዊና ፖለቲካዊ ጥናት ያካሂዳል፣ ይህንንም በማያቋርጥ ሂደት በየጊዜው በማከናወን ውጤታማነቱን ይገመግማል፤
- ቀልጣፋና ውጤታማ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ለማድረግ የመንግስት የኮሙኒኬሽን ፍላጎት(Government communication needs) እና የህዝቡ የኢንፎርሜሽን ፍላጎት(Public information needs) በጥናት ይለያል፣ የጥናቱን ውጤት በመገምገም ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለሀላፊው ያቀርባል፣
- ከውጭና ከአገር ውስጥ የጥናት-ምርምር ተቋማት የሚገኙ የጥናት ውጤቶች እንዲሁም በትምህርታዊ ጉብኝቶች የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችና ልምዶች እንዲቀመሩና እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ ውጤታማ የሚሆኑበትን ስልት በመንደፍ ያስገኙትን ውጤት ይገመግማል፤
- የኮሙኒኬሽንና የሚዲያ ምርምር እና የህዝብ አስተያየት ጥልቅ ጥናቶች ያካሂዳል፤ እንዲካሄዱም አመራር ይሰጣል፣ የተገኙ ውጤቶችን መሠረት በማድረግም የኮሙኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ በየወቅቱ በተለያዩ ቋንቋዎች የሚያስተገቧቸው ክልላዊ አጀንዳዎች እንዲቀረጹ የውሳኔ ሃሳብ ለኃላፊ ያቀርባል፣
- በሀገር ውስጥ ወይም በውጭ ሙያተኞች ጥልቅ ምርምር የሚሹ ጉዳዮችን በመለየት የጥናት- ምርምር ፕሮጀክት ምክረ ሃሳብ ያዘጋጃል፤ የፕሮጀክት ሰነዶችን ይገመግማል፣ እንዲጸድቁና ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣
- የክልላን ራዕይና የህዳሴውን ጉዞ እውን ለማድረግ በየወቅቱ የሚቀርጻቸው ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች፣ ስትራቴጂዎች፣ ስልቶች እንደግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ ክልላዊ የኮምዩኒኬሽን ምርምሮችና የህዝብ አስተያየት ጥናቶች ያካሂዳል፤ እንዲካሄዱ ያደርጋል፤ ለመንግስት ከፍተኛ አመራር አካላት ያቀርባል፤ ውጤቱንም ይገመግማል፤
- በልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ዝግጅትና ትግበራ ዙሪያ ህብረተሰቡ የተሟላ መረጃ እንዲኖራው የኮምዩኒኬሽን ምርምርና የህዝብ አስተያየት ጥናቶች የተቀመሩ ሰነዶችን የማህበራዊ ሚዲያ (social media) ጨምሮ በተለያዩ የኮምዩኒኬሽንና ሚድያ አውታሮች በተለያዩ ቋንቋዎች ወቅታዊና የደረጁ መረጃዎችን ለህዝቡ በማቅረብ ግልፅነት ይፈጥራል፤ በዓለም አቀፉ ህብረተሰብ ዘንድ ስለክልላችን ቀዳሚና

የተሟላ የመረጃ ምንጭ መሆን  የሚቻልበትን አቅም ይገነባል፤

**ውጤት** 6. የህዝቡን አመለካከት ለመለየት የህዝብ አስተያየት መሰብሰብና መተንተን ውጤቱን ለሚመለከተው አካል ማቅረብ

- የህዝቡን አስተያየት አዝማሚያውን በመለየት ለጥያቄያቸው ምላሽ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፤
- ግብረ መልስ መስጠት

**ውጤት** 7 . የኮሙኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ አቅም ለመገንባት የሚያስችሉ ጥናቶችን በማድረግ አዳዲስ  የአሰራር ስርዓቶች መዘርጋት፣ሞጅሎችን ማዘጋጀት ስልጠና መስጠት፤

- የስልጠናዎችና ልምድ ልውውችን ውጤታማነት መገምገም፣ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ሥራውን ውጤታማ ማድረግ ነው፡

## III. የሥራው ባህሪ መግለጫዎች

### 3.1 የሥራ ውስብስብነት፣

- ሥራው ወቅታዊ የሆኑ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ የጥናት ርዕሶችን በመምረጥ፣ ከደንበኞች ጋር ግንኙነት በመፍጠርና በመግባባት፣ ፕሮጀክት በመቅረጽ፣ የህዝብ አስተያየት ጥናት ሊካሄድባቸው የሚገቡ ወቅታዊ ርዕሰ ጉዳዮችና አጀንዳዎችን መርምሮ በመለየት፣ እሴት ባላቸው ክልላዊ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ጉዳዮች ላይ ጥናት እንዲካሄድና የተደራጀ መረጃ ለፖሊሲ አውጪዎችና ውሳኔ ሰጪዎች እንዲቀርብ በማድረግና የጥናቶቹ ተፈላጊነት እንዲያድግ በማድረግ፣ መረጃዎች በጥራትና በሚፈለገው መጠን እንዲሰበሰቡ ስልት በመቀየስ፣ ተመሳሳይ ስራ ላይ ከተሰማሩት የሀገር ውስጥና የውጭ ተቋማት ልምድ በመቅሰም፣ ተሞክሮዎችን በመቀመር እና የጥናትና ምርምር ስራዎችን ጥራትና ቅልጥፍና ለማሳደግ የሚያስችሉ የአሰራር ማሻሽያ ማኑዋሎችን ማዘጋጀት ነው፡፡
- ክልላዊ የኮሙዩኒኬሽን ጥናትና ምርምር ስራዎች የሚመራበትን እቅድ አዘጋጅቶ ማከፋፈል፤ ማስተባበር፣ ተፈጻሚነቱን መከታተል፣ ውጤቱንም መገምገም፣ የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በአፈፃፀም ወቅት የሚያጋጥማቸውን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ ጥናትና ምርምሮችን ማካሄድ፤ በምርምር በትንተና እና በስርጸት ብቃትና ብስለት ያላቸው ሳይንሳዊና ዘመን ተሻጋሪ ሃሳቦችን ማፍለቅ፤ በሃይማኖቶች እኩልነትና የሴኩላሪዝም መርሆዎች ዙሪያ፣ በመቻቻልና የጋራ እሴቶች የማጠናከር ጉዳይ እንዲሁም አክራሪነትና ፅንፈኝነት በመድፈቅ ዙሪያ በመላው ህዝብ ዘንድ ብሔራዊ መግባባት እንዲፈጠር ሁሉን አቀፍ፣ ተከታታይ፣ የተቀናጀና ወጥነት ያለው ሰፊ ምርምር ማካሄድ፤ ከክልሉ ፕሬዝደንት መግለጫዎችና

ንግግሮች ሲቀርቡ የሕዝብ አስተያየቶችን በማሰባሰብና አያይዞ በመተንተን ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመንግስት ከፍተኛ ኃላፊዎች መስጠት፣ ለግብዓትነት መዋላቸውንም ማረጋገጥ፤

- የጥናትና ምርምር ተቋማት በቅንጅት ለመስራት ፈቃደኛ አለመሆን፣ ህዝቡ የሚፈልገውን ኢንፎርሜሽንና ሃሳቡን በግልፅ አለማሳወቅ፣ የጥናትና ምርምር ሰነዶች፣ የፕሮጀክት ሰነዶች፣ መመሪያዎች፣ ማንዋሎችና ስታንዳርዶች የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው አለመዘጋጀት፣ አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶች ቶሎ ተቀባይነት አለማግኘት የሚያጋጥሙ ችግሮች ናቸው፡፡
- እነዚህም ችግሮች የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በአፈፃፀም የሚያጋጥማቸውን ችግሮች በጥናት ላይ ተመስርቶ በመፍታት፤ የመፍትሔ ሃሳብ በማመንጨት፤ በየወቅቱ ያለውን እድገት እና ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ አዳዲስ ሀሳቦችን በማቅረብ፤ በሃይማኖቶች እኩልናትና የሴኩላሪዝም መርሆዎች ዙሪያ፣ በመቻቻልና የጋራ እሴቶች በማጠናከር፤ አክራሪነትና ፅንፈኝነት በመድፈቅ ዙሪያ በመላው ህዝብ ዘንድ ብሔራዊ መግባባት በመፍጠር፤ የሕዝብ አስተያየቶችን በማሰባሰብና በመተንተን ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመንግስት ከፍተኛ ኃላፊዎች በመስጠት፣ በህዝቡ ዘንድ የተፈጠሩ አዎንታዊና አሉታዊ አስተሳሰቦች እንዲሁም የዓለም ማህበረሰብ ያለውን አተያይ በማሳወቅ፤ ምርምርና ጥናት የሚሹ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን በመለየት፤ የምክር አገልግሎት በመስጠት፤ ተራማጅ አስተሳሰብ ያላቸው ዜጎች በማፍራት፤ መልካም ገፅታ ለመገንባት የሚያስችሉ የጥናትና ምርምር ተግባራትን በሚዲያና ኮሙኒኬሽን አግባብ በመፈጸምና በማጎልበት፤ የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት የማያቋርጥ የግንዛቤ ስራ በመስራት፣ በአለም ላይ ያለውን ተጨባጭ እውነታ ከክልሉ የዕድገት ደረጃ ጋር የተጣጣመ ምርምርና ጥናት እንዲካሄድ በማድረግ፣ የተሟላ መረጃ እንዲይዙ ተገቢውን ጥረት በማድረግ፣ ከአሳማኝ መረጃ ጋር በማቅረብና አስፈላጊውን ማብራሪያ በማቅረብ፣ የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሞ የህብረተሰቡን ሀሳብ በማግኘት፣ የአደረጃጀቶችን ባህሪይ ታሳቢ ባደረገ መልኩ የዳሰሳ ጥናቱ እንዲካሄድ አቅጣጫ በመስጠት፣ የፕሮጀክት ሰነዶችና የአሰራር ስርአት ሰነዶች ጥራታቸው የሚፈተሽበት ሥርዓት ተግባራዊ እንዲሆን በማድረግ፣ የቅርብ የክትትል፣የድጋፍ፣የመግባባትና የማሳመን ስራ በመራስት የሚፈቱ ናቸው፡፡

- **በሥራው ክንውን ወቅት** ደንበኞች ከበርካታ ወቅታዊ ጉዳዮችና አጀንዳዎች መካከል የተመረጠውን ርዕሰ አስፈላጊነት አለመረዳት፣ ክልላዊ እሴት አላቸው ተብለው በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የተካሄዱ የጥናት ውጤቶችን ፖሊሲ አውጪዎችና ውሳኔ ሰጪዎች በሚፈለገው ደረጃ ወስደው ለመጠቀም አለመፈለግና ዕውቅና አለመስጠት፣ የሚሰበሰበው መረጃ ጥራት መጓደል፤ ተቋማት መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ያለመሆን የሚያጋጥሙ ችግሮች ናቸው።
- **እነዚህም ችግሮች** የጥናትና ስራው የሚሰራላቸው ተቋማት ኃላፊዎችን በተከታታይ አግኝቶ ስለስራው አስፈላጊነት፣ ጥልቀትና አድካሚነት በሚገባ በማስረዳት፣ ግልጽ የሆኑ የጥናቶቹን

አጠቃሎ /summery/ በማዘጋጀት ለፖሊሲ አውጪዎችና ውሳኔ ሰጪዎች አቅርቦ ሙሉ ጥናቱን እንዲያነቡ በማበረታታት፣ በመረጃ መሰብሰብ ሂደት ሊከሰቱ የሚችሉ ስህተቶችን የሚያስቀር ስልት በመቀየስ፣ የቅርብ ክትትል በማድረግና በመደገፍ፣ ልምድና ተሞክሮዎችን ቀምሮ በመተግበር ይፈታሉ።

### 3.2 ራስን ችሎ መስራት፣

#### 3.2.1 ሥራው የሚከናወንበት አግባብ፣

- ሥራው ህጎችን፣ የተቋሙን አጠቃላይ የትኩረት አቅጣጫና ስትራቴጂክ ዕቅድ መነሻ በማድረግ የሚከናወን ነው።

#### 3.2.2 ሥራው የሚጠይቀው የክትትልና ድጋፍ ደረጃ፣

- ሥራው ለተቋማት፣ ለፖሊሲ አውጪዎች፣ ለውሳኔ ሰጪዎችና ሌሎች ደንበኞች በሳይንሳዊ መንገድ ተሰብስቦ የተተነተነ መረጃን የማቅረብ ዓላማን ከማሳካት አንፃር ስለመከናወኑ በመጨረሻ ይገመገማል።

### 3.3 ተጠያቂነት

#### 3.3.2 ተጠያቂነት ለሥራ ውጤት /Responsibility for Impact/፣

- ሥራው ወቅታዊ የሆኑ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ የጥናት ርዕሶችን በመምረጥ፣ ከደንበኞች ጋር ግንኙነት በመፍጠርና መግባባት፣ ፕሮጄክት በመቅረጽ፣ የህዝብ አስተያየት ጥናት ሊካሄድባቸው የሚገቡ ወቅታዊ ርዕሰ ጉዳዮችና አጀንዳዎችን መርምሮ መለየት፣ እሴት ባላቸው ክልላዊ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ጉዳዮች ላይ ጥናት እንዲካሄድና የተደረጃ መረጃ ለፖሊሲ አውጪዎችና ውሳኔ ሰጪዎች እንዲቀርብ ማድረግና የጥናቶቹ ተፈላጊነት እንዲያድግ የማድረግ፣ መረጃዎች በጥራትና በሚፈለገው መጠን እንዲሰበሰቡ ስልት የመቀየስ፣ ተመሳሳይ ስራ ላይ ከተሰማሩት የሀገር ውስጥና የውጭ ተቋማት ልምድ የመቅሰም፣ ተሞክሮዎችን በመቀመር እና የጥናትና ስራዎችን ጥራትና ቅልጥፍና ለማሳደግ የሚያስችሉ የአሰራር ማሻሻያ ማኑዋሎችን ማዘጋጀት ሲሆን፤ እነዚህ ተግባራት የሙያውን ስነ ምግባርና የክልሉን ህጎች መሠረት አድርጎ በጥንቃቄ ባይከናወኑ ፖሊሲ አውጭዎችንና ውሳኔ ሰጪዎችን ያሳስታሉ፣ ሀብት እንዲባክን ያደርጋሉ፣ ይህም በተቋሙ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

#### 3.3.3 ተጠያቂነት ለሚስጥራዊ መረጃ፣

- የመንግስት፣ የድርጅቶችና የግለሰብ ዕቅዶች፣ ሪፖርቶች፣ የአሰራር መመሪያዎችና የተለያዩ ምስጢራዊ ሰነዶች ከባከኑና ላልተፈቀደላቸው ሌሎች አካላት ተላልፈው ከተሰጡ የደንበኞቹ ጥቅም ይጎዳል፣

በደንበኞቹና በተቋሙ መካከል ውዝግብና አለመተማመን ይፈጠራል።

3.4 ፈጠራ

- ሥራው ወቅታዊ የሆኑ የጥናት ርዕሶች መርምሮ መምረጥና ፕሮጀክት መቅረጽን፣ በተመሳሳይ ስራ ላይ ከተሰማሩት የሀገር ውስጥና የውጭ ተቋማት ልምድ መቅሰምን፣ ተሞክሮዎችን በመቀመር እና የጥናትና ምርምር ስራዎችን ጥራትና ቅልጥፍና ለማሳደግ የሚያስችሉ አዳዲስ ሐሳቦችን በማመንጨት የአሰራር ማሻሻያ ማኑዋሎችን አዘጋጅቶ መተግበርን ይጠይቃል።

3.5. የሥራ ግንኙነት /Work Communication/

3.5.1 የግንኙነት ደረጃ

- በውስጥ ከህዝብ ግንኙነትና የህዝብ አስተያየት ዳይሬክቶሬት፣ ከተጓዳኝ የቡድን መሪዎችና ባለሙያዎች እና በውጭ የስራ ግንኙነት ከመሰረቱት ተቋማትና አገልግሎት ፈላጊ ድርጅቶች ኃላፊዎችና የቡድን መሪዎች ጋር ይገናኛል።

3.5.2 የግንኙነቱ ዓላማ

- የስራ መመሪያና መረጃ ለመቀበል፣ መረጃ ለመስጠት፣ ስለስራው ባህሪና አስፈላጊነት ለማስረዳትና ለማግባባት፣ ስራው በምን አግባብ መከናወን እንዳለበት ለመወያየት፣ አፈፃፀሙን ለመገምገም፣ ግብረ መልስ ለመቀበል፣ ልምድ ለመቅሰምና ተሞክሮዎች ለመቀመር ነው።

3.5.3 የግንኙነቱ ድግግሞሽ

- ከቀን የሥራ ሰዓት 50 % ይሆናል።

3.6 ኃላፊነት

3.6.1 ኃላፊነት ለሰው ሀብት

3.6.1.1 በኃላፊነት የሚመራቸው ሠራተኞች ብዛት

- 11እስከ 15 የሚደርሱ ባለሙያዎችን የመምራት ኃላፊነት አለበት።

3.6.1.2 የኃላፊነት አይነትና ደረጃ

- በተለያየ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የጥናት ባለሙያዎችን የዕቅድ ኦሬንቴሽንና የአፈፃፀም አቅጣጫ መስጠት፣ ለስራ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ማሟላት፣ ስራ ማከፋፈል፣ መከታተልና መደገፍ፣ አፈፃፀሙን

መገምገምና መመዘን ነው።

### 3.6.2 ኃላፊነት ለንዋይ

- የለበትም።

### 3.6.3 ኃላፊነት ለንብረት

- ለሥራው የሚያስፈልጉ በግምት ብር 300,000 /ሦስት መቶ ሺህ ብር/ የሚሆኑ ላፕ ቶፕና ዴስክ ቶፕ ኮምፒውተሮች፣ ፕሪንተር፣ ቴሌቪዥን፣ ወንበሮች፣ ጠረጴዛና ሼልፍ ያሉ ንብረቶችን በአግባቡ በመያዝ የመጠቀም ኃላፊነት አለበት።

## 3.7. ጥረት

### 3.7.1 የአዕምሮ ጥረት

- ሥራው ወቅታዊ የሆኑ የጥናት ርዕሶችን መምረጥ፣ ከደንበኞች ጋር ግንኙነት መፍጠርና ማግባባት፣ ፕሮጀክት መቅረጽ፣ የህዝብ አስተያየት ጥናት ሊካሄድባቸው የሚገቡ ወቅታዊ ርዕሰ ጉዳዮችና አጀንዳዎችን መርምሮ መለየት፣ እሴት ባላቸው ክልላዊ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ጉዳዮች ላይ ጥናት እንዲካሄድና የተደረጃ መረጃ ለፖሊሲ አውጪዎችና ውሳኔ ሰጪዎች እንዲቀርብ በማድረግና የጥናቶቹ ተፈላጊነት እንዲያድግ ማድረግ፣ መረጃዎች በጥራትና በሚፈለገው መጠን እንዲሰበሰቡ ስልት የመቀየስ፣ ተመሳሳይ ስራ ላይ ከተሰማሩት የሀገር ውስጥና የውጭ ተቋማት ልምድ መቅሰም፣ ተሞክሮዎችን በመቀመር እና የጥናትና ስራዎችን ጥራትና ቅልጥፍና ለማሳደግ የሚያስችሉ የአሰራር ማሻሻያ ማኑዋሎችን ማዘጋጀት ሲሆን፣ ይህም ከቀን የሥራ ጊዜው 70% ይሆናል።

### 3.7.2. ስነልቦናዊ ጥረት

- ሥራው መረጃዎችን ማፈላለግና ማሰባሰብ፣ የጥናት ግኝቶች ለፖሊሲና ለውሳኔ ሐሳብ ግብዓትነት እንዲውሉ ማድረግና ባለድርሻ አካላቱ በአጋርነት እንዲቆዩ መስራት የሚፈጥረውን ውጥረት እንዲሁም የስራ አስፈላጊነትን በማስረዳት ሂደትና የጥናት ግኝቶችን መቀበል ባለመቀበል መካከል ከደንበኞች ጋር በሚፈጠረው አለመግባባት የሚከሰተውን ስነልቦናዊ ጫናን ተቋቁሞ መስራትን ይጠይቃል።

### 3.7.3 የዕይታ ጥረት፣

- ሥራው የተለያዩ ዕቅዶች፣ ሪፖርቶች፣ ህጎች፣ መመሪያዎች፣ ማኑዋሎች፣ የተሰበሰቡና የተደራጁ ሰነዶች፣ የጥናት ውጤቶች፣ የተሰጡ ግብረ መልሶን በኮምፒዩተርና በወረቀት የማንበብ፣ መፃፍና መተንተን ሲሆን፣ ከቀን የሥራ ጊዜው 50% ይሆናል።

**3.7.4 የአካል ጥረት**

**3.8. የሥራ ሁኔታ**

- ሥራው 80% በመቀመጥ፣ 20% በመንቀሳቀስ የሚሰራ ነው።

**3.8.1. ሥጋትና አደጋ**

- የለውም።

**3.8.2 የሥራ አካባቢ ሁኔታ**

- ሥራው በአብዛኛው በቢሮ ውስጥ የሚሰራ ነው።

**3.9. እውቀትና ክህሎት፣**

**3.9.1. ትምህርት**

| የትምህርት ደረጃ | የትምህርት ዓይነት |
|---|---|
| የመጀመሪያ ዲግሪ | በኮሚዩኒኬሽንና ጋዜጠኛነት፣ ፖለቲካል ሳይንስና አለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቋንቋና ስነ-ጽሁፍ፣ ስራ አመራር፣ ሶሺዮሎጂ እና ሶሻል አንትሮፖሎጂ ታሪክ ቢዝነስ አድምንስትሬሽን፣ ኢኮኖሚክስ በመጀመሪያ ዲግሪ ከስራው ጋር ግንኙነት ያለው 10 ዓመትየሥራ ልምድ ያለው /ያላት/ መሠረታዊ የኮምፒዩውተር እውቀትያለው /ያላት/ |

**3.9.2 ሥራውን ለመጀመር የሚያስፈልግ የሥራ ልምድ**

| የሥራ ልምዱ ለማግኘት የሚጠይቀው ጊዜ | ልምዱ የሚገኝበት የሥራ ዓይነት |
|---|---|
| በመጀመሪያ ዲግሪ 10 ዓመት | በማህበራዊ ሳይንስ ጥናትና ሥራዎች ላይ |

| የሥራ ትንተና ባለሙያ ሥም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| | | |

| የሥራ ዝርዝሩን ያጸደቀው የኃላፊው ሥም | የሥራ መደቡ መጠሪያ | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| | | | |

| የሥራ ዝርዝር መግለጫ ቅጽ | | |
|---|---|---|
| **I. አጠቃላይ መግለጫ** | | |
| **የመስሪያ ቤቱ ስም** | **የሥራ መደቡ መጠሪያ** | **የሥራ ዘርፍ** |
| የሲ/ብ/ክ/መ/መንግስት ኮሙኒኬሽን ቢሮ | የህዝብ አስተያየት ግምገማና ትንተና ቡድን መሪ | ህዝብ አስተያየት፣ ጥናትና የኮሙዩኒኬሽን አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር |
| **የቅርብ ኃላፊ የሥራ መደብ /ተጠሪነት** | | |
| | **የሥራው ደረጃ** | **የሥራው ኮድ** |
| ህዝብ አስተያየት፣ ጥናትና የኮሙዩኒኬሽን አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር | XV | |
| **መስሪያ ቤቱ የሚገኝበት ቦታ** | | |
| ሀዋሳ | | |
| **II. የሥራ መደቡ ዋና ዓላማ፤ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት** | | |

2.1. **የሥራ መደቡ ዓላማ፡**

- በተቋሙ ፍላጎት መሰረት ያደረጉ የህዝብ አስተያየት ማሰባሰቢያ አጀንዳ  በመለየት፣ ተገቢ የመረጃ መሰብሰቢያ መጠይቆችን በመቅረጽ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካ ጉዳዮች ዙሪያ ትክክለኛ መረጃ ማሰባሰብና ከህዝቡ መሰብሰብ ፤ ተቋሙና ተገልጋዮች ትክክለኛና የተደራጀ  መረጃ እንዲያገኙ ማድረግ ነው።

## 2.2. ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት፣

**ውጤት 1፡- የህዝብ አስተያየት መሰብሰቢያ አጀንዳ በመቅረጽ ና ዕቅዶችን በማዘጋጀት መረጃ  ማሰባሰብና መተንተን።**

- ለህዝብ አስተያየት ማሰባሰቢያ እቅድና የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት ይነድፋል፤ ትክክለኛ የህዝብ አስተያየት እንዲሰበሰብ ያደርጋል፤ ባለሙያዎች  ድጋፍ ይሰጣል፤
- ለህዝብ አስተያየት ማሰባሰቢያ የሚረዱ የመረጃ መሰብሰቢያ መጠይቆችን በመቅረጽ መረጃን በቀላሉ ለማግኘት በሚያስችል መልኩ ያዘጋጃል፤

- ከዳይሬክተሩ በሚሰጠው *መመሪያ መሠረት* ተገቢውን የተለያዩ ዘዴዎችን ተከትሎ የህዝብን አመለካከት፣ ስሜት፣ ፍላጎትና ዝንባሌ ለማወቅ በአዎንታ እና በአሉታ በመለየት ዕለታዊና ሣምንታዊ የህዝብ አስተያየት እንዲሰበሰብ ማድረግና ምላሽ የሚሹ ጉዳዮችን በመለየት ለሚመለከተው አካል እንዲቀርብ ያደርጋል፤
- በተቋሞች ጥያቄና ፍላጎት መሰረት የህዝብ አስተያየት ትንተና እና ግምገማ የሚካሄድላቸውን መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በመለየት የህዝቡን /ተገልጋዩን/ ስሜት፣ ዝንባሌ፣ አስተሳሰብና ፍላጎት ለማወቅና ለመተንተን የሚያስችሉ መረጃዎችን ያሰባስባል፤

**ውጤት 2 ፡- ለተቋሙ ይሁንታ የሚያስገኙ አጀንዳዎችን መቅረጽ።**

- በአጀንዳ ቀረፃ ላይ ርዕሰ ጉዳዮች መረጣ ላይ ይሳተፋል፤
- ገቢ የሚያስገኙ የፕሮጀክት ሐሳቦችን ያመነጫል፣ ፕሮጀክቶችን ይቀርፃል፤
- ከዳይሬክተሩ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፤ በፍላጎታቸውና መግባባት ለተደረሰባቸው ጉዳዮች የማስፈፀሚያ ዕቅድ ያዘጋጃል፤

**ውጤት 3 ፡- የህዝብ አስተያየት በመሰብሰብ ለሚመለከተው አካል ግኝቶችን ማቅረብ ፣ ግብረ መልስ መቀበልና መተግበር።**

- ከተሰበሰበው የህዝብ አስተያየት ግኝቶችን ለቅርብ ኃላፊው በማቅረብ እርማት ይቀበላል፤ የተሰጡ የማስተካከያ ሐሳቦችን ተቀብሎ ተግባራዊ ያደርጋል፤
- በተሰበሰበው አስተያየት ግብረ መልሶችን ይቀበላል፤ ይተገብራል።

## III. የሥራው ባህሪ መግለጫዎች

**3.1 የሥራ ውስብስብነት፡-**

- *ሥራው እቅድና የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት መንደፍን፤ ተቋሙ ለውስጥና ለውጪ የህዝብ አስተያየት የሚሰበሰብባቸው አጀንዳዎችን መቅረጽን፣ መረጃን በቀላሉ ለማግኘት የሚያስችሉ መጠይቶች መቅረጽን፣ ተገቢውን ዘዴዎች ተከትሎ የህዝብን አመለካከት፣ ስሜት፣ ፍላጎትና ዝንባሌ ለማወቅ የሚያስችሉ ጥናቶች ማካሄድን፣ ፣ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ግንኙነት ፈጥሮ በፍላጎታቸውና መግባባት ለተደረሰባቸው ጉዳዮች የማስፈፀሚያ ዕቅድ ማዘጋጀትን፣ ከህዝብ በተሰበሰበው አስተያየት ትንታኔ ውጤቶችን በቅርብ ኃላፊ በማስገምገም ለሚነሱ ጥያቄዎች ማብራሪያ መስጠትን፣*
- **በሥራው ክንውን ወቅት** የህዝብ አስተያየት በሚሰበሰብበት ወቅት የተሟላ መረጃ ለማግኘት

አለመቻል፣ ቀጥታ ከህዝብ የሚሰበሰበው አስተያየት ተሸራርፎ መድረስ ፣ ህዝቡ አስተያየት ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን ናቸው፡፡

- **እነዚህም ችግሮች** ተጨማሪ የመረጃ ማግኛ ዘዴዎችን በመፈለግ፣ በየደረጃው ያሉ የኮሙኒኬሽን ተቋማት በአግባቡ የህዝብ አስተየየት ተሰብስቦ እንዲላክ ማድረግ፣ አስተያየት ሰጪ የህብረተሰብ ክፍሎች የተሟላ መረጃ እንዲሰጡ ተገቢ የማግባባት ስራ በመስራት፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀምና ወቅታዊ መረጃዎችን በማደራጀት ይፈታሉ።

### 3.2 ራስን ችሎ መስራት፣

#### 3.2.1 ሥራው የሚከናወንበት አግባብ፣

- ሥራው ደንብ፣ መመሪያና የአሰራር ማኑዋሎችን ዕቅድ መሰረት በማድረግ ይከናወናል።

#### 3.2.2. ሥራው የሚጠይቀው የክትትልና ድጋፍ ደረጃ፣

- ሥራው ተፈላጊውን ግብ ከማሳካት አንጻር ስለመከናወኑ በመጨረሻ በኃላፊው ይገመገማል።

### 3.4 ተጠያቂነት

#### 3.4.2 ተጠያቂነት ለሥራ ውጤት /Responsibility for Impact/፣

- ሥራው እቅድና የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት የመንደፍ፤ በተለየዩ የልማትና የመልካም አስተዳደር ተግባራት ላይ ትክክለኛ የህዝብ አስተያየት ለመሰብሰብ አጀንዳ የመቅረጽ፣ መረጃን በቀላሉ ለማግኘት የሚያስችሉ መጠይቶች የመቅረጽ፣ ተገቢውን የህዝብ አስተያየት ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ተከትሎ የህዝብን አመለካከት፣ ስሜት፣ ፍላጎተና ዝንባሌ ለማወቅ የህዝብ አስተያየት ትንተና የማካሄድ፣ የተሰበሰቡ መረጃዎች የተሟሉና ትክክለኛ መሆናቸውን የማረጋገጥና የመተንተን፣ የህዝብ አስተያየት ትንተና ውጤቶችን ለቅርብ ኃላፊ በማስገምገም ለሚነሱ ጥያቄዎች ማብራሪያ የመስጠት፣ ሥራው በበቂ መረጃና እውቀት ላይ ተመስርቶ ለሚፈለገው ዓላማ ለማዋል በጥንቃቄና በትኩረት በወቅቱ ባይከናወን የተዛባ መልዕክት በማስተላለፍ በህዝብና በመንግስት፣ በአገልግሎት ሰጪዎችና ተጠቃሚዎች መካከል አለመስማማትና አለመተማመንን ይፈጥራል፣ በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ክፍተት ይፈጥራል፤ ይህ በተቋሙ ገጽታ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

#### 3.4.3 ተጠያቂነት ለሚስጥራዊ መረጃ፣

- የተሰበሰቡና የተተነተኑ የህዝብ አስተያየት መረጃዎች ከመንግስትና ከደንበኞች ፍላጎትና ፈቃድ ውጪ እንዲሁም መረጃው ይፋ መሆን ካለበት ጊዜ በፊት ከወጣ በተቋሙና በመረጃ ሰጪዎች መካከል አለመተማመንና ቅራኔን ሊፈጥር ይችላል።

### 3.5 ፈጠራ

- ሥራው አዳዲስ ሃሳቦችን በማመንጨት፣ ማኑዋሎችንና መመሪያዎችን በማዘጋጀት፣ የተሻሻሉ አሰራሮችን በመቀየስና ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲሰፋፉና ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግን ይጠይቃል።

3.5. የሥራ ግንኙነት /Work Communication/

3.5.1 የግንኙነት ደረጃ

- በውስጥ ከክፍል ኃላፊውና ከክፍሉ ባለሙያዎች፣ በውጭ በተለያዩ ተቋማት፣ በአምራቾችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ከሚገኙ ከፍተኛ ባለሙያዎችና ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

3.5.2 የግንኙነቱ ዓላማ

- የስራ መመሪያ ለመቀበል፣ ሪፖርት ለማቅረብ፣ ለማስረዳት፣ መረጃ ለማግኘት፣ የጥናት ውጤቶችን ለማቅረብ፣ ግብረ መልስ በመቀበልና በመስጠት ለሚፈለገው አገልግሎት እንዲውል ለማድረግ ነው።

3.5.3 የግንኙነቱ ድግግሞሽ

- ከቀን የስራ ጊዜው 50% ይሆናል፡፡

3.6 ኃላፊነት

3.6.1 ኃላፊነት ለሰው ሀብት

3.6.1.1 በኃላፊነት የሚመራቸው ሠራተኞች ብዛት

- ሦስት።

3.6.1.2 የኃላፊነት አይነትና ደረጃ

- የለበትም።

3.6.2 ኃላፊነት ለንዋይ

- የለበትም።

3.6.3 ኃላፊነት ለንብረት

- ለሥራው የሚያስፈልጉ በግምት ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ የሚሆኑ እንደ ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ ዴስክቶፕና ላፕቶፕ ኮምፒውተሮች፣ መቅረፀ ድምፅ ፣ ፋይል ማስቀመጫ ሼልፍ ያሉ ንብረቶችን በአግባቡ በመያዝ የመጠቀም ኃላፊነት አለበት።

## 3.7. ጥረት

3.7.1 የአዕምሮ ጥረት

- ሥራው እቅድና የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት መንደፍ፤ መረጃዎች የሚሰበሰቡበትን አጀንዳዎችን መቅረጽ፣

መረጃን በቀላሉ ለማግኘት የሚያስችሉ መጠይቆች መቅረጽ፣ ተገቢውን ዘዴዎች ተከትሎ የህዝብን አመለካከት፣ ስሜት፣ ፍላጎትና ዝንባሌ ለማወቅ የሚያስችሉ የህዝብ አስተያየት ትንተና ማካሄድ፣ ከህዝብ የሚሰበሰቡ መረጃዎች የተሟሉና ትክክለኛ መሆናቸውን ማረጋገጥና መተንተን፣ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ግንኙነት ፈጥሮ በፍላጎታቸውና መግባባት ለተደረሰባቸው ጉዳዮች የማስፈፀሚያ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ ከህዝብ አስተያየት ትንተና የተገኙ ውጤቶችን በቅርብ ኃላፊ አስገምግሞ ሲሆን ከቀን የሥራ ጊዜው 65 % ይሆናል።

**3.7.2.ስነልቦናዊ ጥረት**

- ስራው በአብዛኛው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት እንዲሁም ከአገልግሎት ሰጪ እና ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የሚያገናኝ በመሆኑ የስራውን አስፈላጊነት እና ዓላማ ለማሳመንና ለማግባባት በሚሞከርበት ጊዜ አልፎ አልፎ የሚከሰቱ አለመግባባቶች የሚፈጥሩትን ስነ ልቦናዊ ጫናን ተቋቁሞ ስራውን ውጤታማ ማድረግን ይጠይቃል።

**3.7.3 የዕይታ ጥረት፣**

- ስራው ከህዝብ የተሰበሰቡ አስተያየቶችን ትንታኔ በኮምፒዩተር ላይ መፃፍና ማንበብ፣ በወረቀት ላይም ሆነ በኮምፒዩተር ያሉ ህጎች፣ አዋጆች፣ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና ለስራው አጋዥ የሆኑ ተሞክሮዎችን መቀመር፣ የደንበኞችን ልዩ ልዩ ሰነዶች ማንበብና መረዳት የሚጠይቅ ሲሆን ይህም ከቀን የስራ ጊዜው 50% ይሆናል።

**3.7.4 የአካል ጥረት**

- ሥራው 75% በመቀመጥ እና 25% በመንቀሳቀስ የሚከናወን ነው።

**3.8. የሥራ ሁኔታ**

**3.8.1. ሥጋትና አደጋ**

- የለበትም።

**3.8.2 የሥራ አካባቢ ሁኔታ**

- ሥራው አልፎ አልፎ ከፍተኛ ሙቀትና ቅዝቃዜ፣ ወረርሽኝና የተለያዩ ግጭቶችና ሁከቶች፣ የተፈጥሮ አደጋዎች ባሉባቸው የተለያዩ መልክዓ ምድራዊ አካባቢዎች ሊሰራ ስለሚችል የጤና መታወክ ያጋጥማል።

**3.9. እውቀትና ክህሎት፣**

**3.9.1. ትምህርት**

| የትምህርት ደረጃ | የትምህርት ዓይነት |
|---|---|
| የመጀመሪያ ዲግሪ | በኮሚዩኒኬሽንና ጋዜጠኛነት፣ ፖለቲካል ሳይንስና አለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቋንቋና ስነ-ጽሁፍ፣ ስራ አመራር፣ ሶሺዮሎጂ እና ሶሻል አንትሮፖሎጂ ታሪክ፣ቢዝነስ አድምንስትሬሽን፣ ኢኮኖሚክስ በመጀመሪያ ዲግሪ ከስራው ጋር ግንኙነት ያለው 8 ዓመትየሥራ ልምድ ያለው /ያላት/ መሠረታዊ የኮምፒዩውተር እውቀትያለው /ያላት/ |

3.9.2 ሥራውን ለመጀመር የሚያስፈልግ የሥራ ልምድ

| የሥራ ልምዱ ለማግኘት የሚጠይቀው ጊዜ | ልምዱ የሚገኝበት የሥራ ዓይነት |
|---|---|
| በመጀመሪያ ዲግሪ 8 ዓመት | በማህበራዊ ጉዳዮች ጥናትና ሥራዎች የተገኘ ልምድ |

| የሥራ ትንተና ባለሙያ ሥም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| | | |

| የሥራ ዝርዝሩን ያጸደቀው የኃላፊው ሥም | የሥራ መደቡ መጠሪያ | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| | | | |

| የሥራ ዝርዝር መግለጫ ቅጽ | | |
|---|---|---|
| I. አጠቃላይ መግለጫ | | |
| **የመስሪያ ቤቱ ስም** | **የሥራ መደቡ መጠሪያ** | **የሥራ ዘርፍ** |
| የሲ/ብ/ክ/መ/መንግስት ኮሙኒኬሽን ቢሮ | የህዝብ አስተያየት ግምገማና ትንተና ባለሙያ IV | ህዝብ አስተያየት፣ ጥናትና የኮሙዩኒኬሽን አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር |
| | ብዛት፡- ሁለት ባለሙያ | |
| | | |
| **የቅርብ ኃላፊ የሥራ መደብ /ተጠሪነት** | | |
| | **የሥራው ደረጃ** | **የሥራው ኮድ** |
| ለቡድን መሪው | XIV | |
| | | |
| **መስሪያ ቤቱ የሚገኝበት ቦታ** | | |
| **ሀዋሳ** | | |
| II. የሥራ መደቡ ዋና ዓላማ፣ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት | | |

2.1. **የሥራ መደቡ ዓላማ፡**

- በተቋሙ ፍላጎት መሰረት ያደረጉ የህዝብ አስተያየት ማሰባሰቢያ አጀንዳ በመለየት፣ ተገቢ የመረጃ መሰብሰቢያ መጠይቆችን በመቅረጽ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካ ጉዳዮች ዙሪያ ትክክለኛ መረጃ ማሰባሰብና ከህዝቡ መሰብሰብ ፤ ተቋሙና ተገልጋዮች ትክክለኛና የተደራጀ መረጃ እንዲያገኙ ማድረግ ነው።

## 2.2. ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት፤

**ውጤት 1፦ የህዝብ አስተያየት መሰብሰቢያ አጀንዳ በመቅረጽ ና ዕቅዶችን በማዘጋጀት መረጃ ማሰባሰብና መተንተን።**

- ለህዝብ አስተያየት ማሰባሰቢያ እቅድና የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት ይነድፋል፤ ትክክለኛ የህዝብ አስተያየት እንዲሰበሰብ ያደርጋል፤ ባለሙያዎች ድጋፍ ይሰጣል፤

- ለህዝብ አስተያየት ማሰባሰቢያ የሚረዱ የመረጃ መሰብሰቢያ መጠይቆችን በመቅረጽ መረጃን በቀላሉ ለማግኘት በሚያስችል መልኩ ያዘጋጃል፤
- ከዳይሬክተሩ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ተገቢውን የተለያዩ ዘዴዎችን ተከትሎ የህዝብን አመለካከት፣ ስሜት፣ ፍላጎትና ዝንባሌ ለማወቅ በአዎንታ እና በአሉታ በመለየት ዕለታዊና ሣምንታዊ የህዝብ አስተያየት እንዲሰበሰብ ማድረግና ምላሽ የሚሹ ጉዳዮችን በመለየት ለሚመለከተው አካል እንዲቀርብ ያደርጋል፤
- በተቋሞች ጥያቄና ፍላጎት መሰረት የህዝብ አስተያየት ትንተና እና ግምገማ የሚካሄድላቸውን መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በመለየት የህዝቡን /ተገልጋዩን/ ስሜት፣ ዝንባሌ፣ አስተሳሰብና ፍላጎት ለማወቅና ለመተንተን የሚያስችሉ መረጃዎችን ያሰባስባል፤

**ውጤት 2 ፡- ለተቋሙ ይሁንታ የሚያስገኙ አጀንዳዎችን መቅረጽ።**

- በአጀንዳ ቀረፃ ላይ ርዕሰ ጉዳዮች መረጣ ላይ ይሳተፋል፤
- ገቢ የሚያስገኙ የፕሮጀክት ሐሳቦችን ያመነጫል፣ ፕሮጀክቶችን ይቀርፃል፤
- ከዳይሬክተሩ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፤ በፍላጎታቸውና መግባባት ለተደረሰባቸው ጉዳዮች የማስፈፀሚያ ዕቅድ ያዘጋጃል፤

**ውጤት 3 ፡- የህዝብ አስተያየት በመሰብሰብ ለሚመለከተው አካል ግኝቶችን ማቅረብ ፣ ግብረ መልስ መቀበልና መተግበር።**

- ከተሰበሰበው የህዝብ አስተያየት ግኝቶችን ለቅርብ ኃላፊው በማቅረብ እርማት ይቀበላል፤ የተሰጡ የማስተካከያ ሐሳቦችን ተቀብሎ ተግባራዊ ያደርጋል፤
- በተሰበሰበው አስተያየት ግብረ መልሶችን ይቀበላል፤ ይተገብራል።

## III. የሥራው ባህሪ መግለጫዎች

**3.2 የሥራ ውስብስብነት፦**

- ሥራው እቅድና የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት መንደፍን፤ ተቋሙ ለውስጥና ለውጪ የህዝብ አስተያየት የሚሰበሰብባቸው አጀንዳዎችን መቅረጽን፣ መረጃን በቀላሉ ለማግኘት የሚያስችሉ መጠይቆች መቅረጽን፣ ተገቢውን ዘዴዎች ተከትሎ የህዝብን አመለካከት፣ ስሜት፣ ፍላጎትና ዝንባሌ ለማወቅ የሚያስችሉ ጥናቶች ማካሄድን፣ ፣ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ግንኙነት ፈጥሮ በፍላጎታቸውና መግባባት ለተደረሰባቸው ጉዳዮች የማስፈፀሚያ ዕቅድ ማዘጋጀትን፣ ከህዝብ በተሰበሰበው አስተያየት

ትንታኔ ውጤቶችን በቅርብ ኃላፊ በማስገምገም ለሚነሱ ጥያቄዎች ማብራሪያ መስጠትን፣

- **በሥራው ክንውን ወቅት** የህዝብ አስተያየት በሚሰበሰብበት ወቅት የተሟላ መረጃ ለማግኘት አለመቻል፣ ቀጥታ ከህዝብ የሚሰበሰበው አስተያየት ተሸራርፎ መድረስ ፣ ህዝቡ አስተያየት ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን ናቸው፡፡
- **እነዚህም ችግሮች** ተጨማሪ የመረጃ ማግኛ ዘዴዎችን በመፈለግ፣ በየደረጃው ያሉ የኮሙኒኬሽን ተቋማት በአግባቡ የህዝብ አስተየየት ተሰብስቦ እንዲላክ ማድረግ፣ አስተያየት ሰጪ የህብረተሰብ ክፍሎች የተሟላ መረጃ እንዲሰጡ ተገቢ የማግባባት ስራ በመስራት፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀምና ወቅታዊ መረጃዎችን በማደራጀት ይፈታሉ።

## 3.2 ራስን ችሎ መስራት፣

### 3.2.1 ሥራው የሚከናወንበት አግባብ፣

- ሥራው ደንብ፣ መመሪያና የአሰራር ማኑዋሎችን ዕቅድ መሰረት በማድረግ ይከናወናል።

### 3.2.3. ሥራው የሚጠይቀው የክትትልና ድጋፍ ደረጃ፣

- ሥራው ተፈላጊውን ግብ ከማሳካት አንጻር ስለመከናወኑ በመጨረሻ በኃላፊው ይገመገማል።

## 3.6 ተጠያቂነት

### 3.6.2 ተጠያቂነት ለሥራ ውጤት /Responsibility for Impact/፣

- ሥራው እቅድና የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት የመንደፍ፣ በተለየዩ የልማትና የመልካም አስተዳደር ተግባራት ላይ ትክክለኛ የህዝብ አስተያየት ለመሰብሰብ አጀንዳ የመቅረጽ፣ መረጃን በቀላሉ ለማግኘት የሚያስችሉ መጠይቶች የመቅረጽ፣ ተገቢውን የህዝብ አስተያየት ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ተከትሎ የህዝብን አመለካከት፣ ስሜት፣ ፍላጎተና ዝንባሌ ለማወቅ የህዝብ አስተያየት ትንተና የማካሄድ፣ የተሰበሰቡ መረጃዎች የተሟሉና ትክክለኛ መሆናቸውን የማረጋገጥና የመተንተን፣ የህዝብ አስተያየት ትንተና ውጤቶችን ለቅርብ ኃላፊ በማስገምገም ለሚነሱ ጥያቄዎች ማብራሪያ የመስጠት፣ ሥራው በበቂ መረጃና እውቀት ላይ ተመስርቶ ለሚፈለገው ዓላማ ለማዋል በጥንቃቄና በትኩረት በወቅቱ ባይከናወን የተዛባ መልዕክት በማስተላለፍ በህዝብና በመንግስት፣ በአገልግሎት ሰጪዎችና ተጠቃሚዎች መካከል አለመስማማትና አለመተማመንን ይፈጥራል፣ በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ክፍተት ይፈጥራል፤ ይህ በተቋሙ ገጽታ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

### 3.6.3 ተጠያቂነት ለሚስጥራዊ መረጃ፣

- የተሰበሰቡና የተተነተኑ የህዝብ አስተያየት መረጃዎች ከመንግስትና ከደንበኞች ፍላጎትና ፈቃድ ውጪ እንዲሁም መረጃው ይፋ መሆን ካለበት ጊዜ በፊት ከወጣ በተቋሙና በመረጃ ሰጪዎች መካከል አለመተማመንና ቅራኔን ሊፈጥር ይችላል።

### 3.7 ፈጠራ

- ሥራው አዳዲስ ሃሳቦችን በማመንጨት፣ ማኑዋሎችንና መመሪያዎችን በማዘጋጀት፣ የተሻሻሉ አሰራሮችን በመቀየስና ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲሰፋፉና ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግን ይጠይቃል።

### 3.5. የሥራ ግንኙነት /Work Communication/

#### 3.5.1 የግንኙነት ደረጃ

- በውስጥ ከክፍል ኃላፊውና ከክፍሉ ባለሙያዎች፣ በውጭ በተለያዩ ተቋማት፣ በአምራቾችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ከሚገኙ ከፍተኛ ባለሙያዎችና ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

#### 3.5.2 የግንኙነቱ ዓላማ

- የስራ መመሪያ ለመቀበል፣ ሪፖርት ለማቅረብ፣ ለማስረዳት፣ መረጃ ለማግኘት፣ የጥናት ውጤቶችን ለማቅረብ፣ ግብረ መልስ በመቀበልና በመስጠት ለሚፈለገው አገልግሎት እንዲውል ለማድረግ ነው።

#### 3.5.3 የግንኙነቱ ድግግሞሽ

- ከቀን የስራ ጊዜው 50% ይሆናል፡፡

### 3.6 ኃላፊነት

#### 3.6.1 ኃላፊነት ለሰው ሀብት

##### 3.6.1.1 በኃላፊነት የሚመራቸው ሠራተኞች ብዛት

- ሦስት።

##### 3.6.1.2 የኃላፊነት አይነትና ደረጃ

- የለበትም።

#### 3.6.2 ኃላፊነት ለንዋይ

- የለበትም።

#### 3.6.3 ኃላፊነት ለንብረት

- ለሥራው የሚያስፈልጉ በግምት ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ የሚሆኑ እንደ ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ ዴስክቶፕና ላፕቶፕ ኮምፒውተሮች፣ መቅረፀ ድምፅ ፣ ፋይል ማስቀመጫ ሼልፍ ያሉ ንብረቶችን በአግባቡ በመያዝ የመጠቀም ኃላፊነት አለበት።

## 3.7. ጥረት

### 3.7.1 የአዕምሮ ጥረት

- ሥራው እቅድና የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት መንደፍ፤ መረጃዎች የሚሰበሰቡበትን አጀንዳዎችን መቅረጽ፣ መረጃን በቀላሉ ለማግኘት የሚያስችሉ መጠይቆች መቅረጽ፣ ተገቢውን ዘዴዎች ተከትሎ የህዝብን አመለካከት፣ ስሜት፣ ፍላጎትና ዝንባሌ ለማወቅ የሚያስችሉ የህዝብ አስተያየት ትንተና ማካሄድ፣ ከህዝብ የሚሰበሰቡ መረጃዎች የተሟሉና ትክክለኛ መሆናቸውን ማረጋገጥና መተንተን፣ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ግንኙነት ፈጥሮ በፍላጎታቸውና መግባባት ለተደረሰባቸው ጉዳዮች የማስፈፀሚያ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ ከህዝብ አስተያየት ትንተና የተገኙ ውጤቶችን በቅርብ ኃላፊ አስገምግሞ ሲሆን ከቀን የሥራ ጊዜው 65 % ይሆናል።

### 3.7.2.ስነልቦናዊ ጥረት

- ስራው በአብዛኛው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት እንዲሁም ከአገልግሎት ሰጪ እና ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የሚያገናኝ በመሆኑ የስራውን አስፈላጊነት እና ዓላማ ለማሳመንና ለማግባባት በሚሞከርበት ጊዜ አልፎ አልፎ የሚከሰቱ አለመግባባቶች የሚፈጥሩትን ስነ ልቦናዊ ጫናን ተቋቁሞ ስራውን ውጤታማ ማድረግን ይጠይቃል።

### 3.7.3 የዕይታ ጥረት፣

- ስራው ከህዝብ የተሰበሰቡ አስተያየቶችን ትንታኔ በኮምፒዩተር ላይ መፃፍና ማንበብ፣ በወረቀት ላይም ሆነ በኮምፒዩተር ያሉ ህጎች፣ አዋጆች፣ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና ለስራው አጋዥ የሆኑ ተሞክሮዎችን መቀመር፣ የደንበኞችን ልዩ ልዩ ሰነዶች ማንበብና መረዳት የሚጠይቅ ሲሆን ይህም ከቀን የስራ ጊዜው 50% ይሆናል።

### 3.7.4 የአካል ጥረት

- ሥራው 75% በመቀመጥ እና 25% በመንቀሳቀስ የሚከናወን ነው።

## 3.8. የሥራ ሁኔታ

### 3.8.1. ሥጋትና አደጋ

- የለበትም።

### 3.8.2 የሥራ አካባቢ ሁኔታ

- ሥራው አልፎ አልፎ ከፍተኛ ሙቀትና ቅዝቃዜ፣ ወረርሽኝና የተለያዩ ግጭቶችና ሁከቶች፣ የተፈጥሮ አደጋዎች ባሉባቸው የተለያዩ መልክዓ ምድራዊ አካባቢዎች ሊሰራ ስለሚችል የጤና መታወክ ያጋጥማል።

| |
|---|
| 3.9. **እውቀትና ክህሎት፣** |
| 3.9.1. **ትምህርት** |

| **የትምህርት ደረጃ** | **የትምህርት ዓይነት** |
|---|---|
| የመጀመሪያ ዲግሪ | በኮሚዩኒኬሽንና ጋዜጠኛነት፣ ፖለቲካል ሳይንስና አለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቋንቋና ስነ-ጽሁፍ፣ ስራ አመራር፣ ሶሺዮሎጂ እና ሶሻል አንትሮፖሎጂ ታሪክ ቢዝነስ አድምንስትሬሽን፣ ኢኮኖሚክስ በመጀመሪያ ዲግሪ ከስራው ጋር ግንኙነት ያለው 6 ዓመትየሥራ ልምድ ያለው /ያላት/ መሠረታዊ የኮምፒዩውተር እውቀትያለው /ያላት/ |

| |
|---|
| 3.9.2 **ሥራውን ለመጀመር የሚያስፈልግ የሥራ ልምድ** |

| **የሥራ ልምዱ ለማግኘት የሚጠይቀው ጊዜ** | **ልምዱ የሚገኝበት የሥራ ዓይነት** |
|---|---|
| **በመጀመሪያ ዲግሪ 6ዓመት** | በማህበራዊ ጉዳዮች ጥናትና ሥራዎች የተገኘ ልምድ |

| **የሥራ ትንተና ባለሙያ ሥም** | **ፊርማ** | **ቀን** |
|---|---|---|
| | | |

| **የሥራ ዝርዝሩን ያጸደቀው የኃላፊው ሥም** | **የሥራ መደቡ መጠሪያ** | **ፊርማ** | **ቀን** |
|---|---|---|---|
| | | | |

## የሥራ ዝርዝር መግለጫ ቅጽ

## I. አጠቃላይ መግለጫ

| **የመስሪያ ቤቱ ስም** | **የሥራ መደቡ መጠሪያ** | **የሥራ ዘርፍ** |
|---|---|---|
| የሲ/ብ/ክ/መ/መንግስት ኮሙኒኬሽን ቢሮ | የህዝብ አስተያየት ግምገማና ትንተና ባለሙያ III | ህዝብ አስተያየት፣ ጥናትና የኮሙዩኒኬሽን አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር |

| **የቅርብ ኃላፊ የሥራ መደብ /ተጠሪነት** | |
|---|---|
| | |

| | የሥራው ደረጃ | የሥራው ኮድ |
|---|---|---|
| ለቡድን መሪው | XIII | |
| | | |
| መስሪያ ቤቱ የሚገኝበት ቦታ | | |
| ሀዋሳ | | |
| II. የሥራ መደቡ ዋና ዓላማ፣ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት | | |

2.1. የሥራ መደቡ ዓላማ፡

- በተቋሙ ፍላጎት መሰረት ያደረጉ የህዝብ አስተያየት ማሰባሰቢያ አጀንዳ በመለየት፣ ተገቢ የመረጃ መሰብሰቢያ መጠይቆችን በመቅረጽ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካ ጉዳዮች ዙሪያ ትክክለኛ መረጃ ማሰባሰብና ከህዝቡ መሰብሰብ ፣ ተቋሙና ተገልጋዮች ትክክለኛና የተደራጀ መረጃ እንዲያገኙ ማድረግ ነው።

## 2.2. ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት፣

**ውጤት 1፦ የህዝብ አስተያየት መሰብሰቢያ አጀንዳ በመቅረጽ ና ዕቅዶችን በማዘጋጀት መረጃ ማሰባሰብና መተንተን።**

- ለህዝብ አስተያየት ማሰባሰቢያ እቅድና የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት ይነድፋል፤ ትክክለኛ የህዝብ አስተያየት እንዲሰበሰብ ያደርጋል፤ ባለሙያዎች ድጋፍ ይሰጣል፤
- ለህዝብ አስተያየት ማሰባሰቢያ የሚረዱ የመረጃ መሰብሰቢያ መጠይቆችን በመቅረጽ መረጃን በቀላሉ ለማግኘት በሚያስችል መልኩ ያዘጋጃል፤
- ከዳይሬክተሩ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ተገቢውን የተለያዩ ዘዴዎችን ተከትሎ የህዝብን አመለካከት፣ ስሜት፣ ፍላጎትና ዝንባሌ ለማወቅ በአዎንታ እና በአሉታ በመለየት ዕለታዊና ሣምንታዊ የህዝብ አስተያየት እንዲሰበሰብ ማድረግና ምላሽ የሚሹ ጉዳዮችን በመለየት ለሚመለከተው አካል እንዲቀርብ ያደርጋል፤
- በተቋሞች ጥያቄና ፍላጎት መሰረት የህዝብ አስተያየት ትንተና እና ግምገማ የሚካሄድላቸውን መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በመለየት የህዝቡን /ተገልጋዩን/ ስሜት፣ ዝንባሌ፣ አስተሳሰብና ፍላጎት ለማወቅና ለመተንተን የሚያስችሉ መረጃዎችን ያሰባስባል፤

**ውጤት 2 ፡- ለተቋሙ ይሁንታ የሚያስገኙ አጀንዳዎችን መቅረጽ።**

- በአጀንዳ ቀረፃ ላይ ርዕሰ ጉዳዮች መረጣ ላይ ይሳተፋል፤
- ገቢ የሚያስገኙ የፕሮጀክት ሐሳቦችን ያመነጫል፣ ፕሮጀክቶችን ይቀርፃል፤
- ከዳይሬክተሩ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፤ በፍላጎታቸውና መግባባት ለተደረሰባቸው ጉዳዮች የማስፈፀሚያ ዕቅድ ያዘጋጃል፤

**ውጤት 3 ፡- የህዝብ አስተያየት በመሰብሰብ ለሚመለከተው አካል ግኝቶችን ማቅረብ ፣ ግብረ መልስ መቀበልና መተግበር።**

- ከተሰበሰበው የህዝብ አስተያየት ግኝቶችን ለቅርብ ኃላፊው በማቅረብ እርማት ይቀበላል፤ የተሰጡ የማስተካከያ ሐሳቦችን ተቀብሎ ተግባራዊ ያደርጋል፤
- በተሰበሰበው አስተያየት ግብረ መልሶችን ይቀበላል፤ ይተገብራል።

## III. የሥራው ባህሪ መግለጫዎች

**3.3 የሥራ ውስብስብነት፡-**

- *ሥራው እቅድና የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት መንደፍን፤ ተቋሙ ለውስጥና ለውጪ የህዝብ አስተያየት የሚሰበሰብባቸው አጀንዳዎችን መቅረጽን፣ መረጃን በቀላሉ ለማግኘት የሚያስችሉ መጠይቶች መቅረጽን፣ ተገቢውን ዘዴዎች ተከትሎ የህዝብን አመለካከት፣ ስሜት፣ ፍላጎትና ዝንባሌ ለማወቅ የሚያስችሉ ጥናቶች ማካሄድን፣ ፣ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ግንኙነት ፈጥሮ በፍላጎታቸውና መግባባት ለተደረሰባቸው ጉዳዮች የማስፈፀሚያ ዕቅድ ማዘጋጀትን፣ ከህዝብ በተሰበሰበው አስተያየት ትንታኔ ውጤቶችን በቅርብ ኃላፊ በማስገምገም ለሚነሱ ጥያቄዎች ማብራሪያ መስጠትን፣*
- **በሥራው ክንውን ወቅት** የህዝብ አስተያየት በሚሰበሰብበት ወቅት የተሟላ መረጃ ለማግኘት አለመቻል፣ ቀጥታ ከህዝብ የሚሰበሰበው አስተያየት ተሸራርፎ መድረስ ፣ ህዝቡ አስተያየት ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን ናቸው፡፡
- **እነዚህም ችግሮች** ተጨማሪ የመረጃ ማግኛ ዘዴዎችን በመፈለግ፣ በየደረጃው ያሉ የኮሙኒኬሽን ተቋማት በአግባቡ የህዝብ አስተየየት ተሰብስቦ እንዲላክ ማድረግ፣ አስተያየት ሰጪ የህብረተሰብ ክፍሎች የተሟላ መረጃ እንዲሰጡ ተገቢ የማግባባት ስራ በመስራት፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀምና ወቅታዊ መረጃዎችን በማደራጀት ይፈታሉ።

**3.2 ራስን ችሎ መስራት፣**

3.2.1 ***ሥራው የሚከናወንበት አግባብ፣***

- *ሥራው ደንብ፣ መመሪያና የአሰራር ማኑዋሎችን ዕቅድ መሰረት በማድረግ ይከናወናል።*

3.2.4. ***ሥራው የሚጠይቀው የክትትልና ድጋፍ ደረጃ፣***

- *ሥራው ተፈላጊውን ግብ ከማሳካት አንጻር ስለመከናወኑ በመጨረሻ በኃላፊው ይገመገማል።*

3.8 **ተጠያቂነት**

3.8.2 **ተጠያቂነት ለሥራ ውጤት** /Responsibility for Impact/፣

- *ሥራው እቅድና የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት የመንደፍ፤ በተለየዩ የልማትና የመልካም አስተዳደር ተግባራት ላይ ትክክለኛ የህዝብ አስተያየት ለመሰብሰብ አጀንዳ የመቅረጽ፣ መረጃን በቀላሉ ለማግኘት የሚያስችሉ መጠይቶች የመቅረጽ፣ ተገቢውን የህዝብ አስተያየት ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ተከትሎ የህዝብን አመለካከት፣ ስሜት፣ ፍላጎተና ዝንባሌ ለማወቅ የህዝብ አስተያየት ትንተና የማካሄድ፣ የተሰበሰቡ መረጃዎች የተሟሉና ትክክለኛ መሆናቸውን የማረጋገጥና የመተንተን፣ የህዝብ አስተያየት ትንተና ውጤቶችን ለቅርብ ኃላፊ በማስገምገም ለሚነሱ ጥያቄዎች ማብራሪያ የመስጠት፣ ሥራው በበቂ መረጃና እውቀት ላይ ተመስርቶ ለሚፈለገው ዓላማ ለማዋል በጥንቃቄና በትኩረት በወቅቱ ባይከናወን የተዛባ መልዕክት በማስተላለፍ በህዝብና በመንግስት፣ በአገልግሎት ሰጪዎችና ተጠቃሚዎች መካከል አለመስማማትና አለመተማመንን ይፈጥራል፣ በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ክፍተት ይፈጥራል፤ ይህ በተቋሙ ገጽታ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡*

3.8.3 **ተጠያቂነት ለሚስጥራዊ መረጃ፣**

- *የተሰበሰቡና የተተነተኑ የህዝብ አስተያየት መረጃዎች ከመንግስትና ከደንበኞች ፍላጎትና ፈቃድ ውጪ እንዲሁም መረጃው ይፋ መሆን ካለበት ጊዜ በፊት ከወጣ በተቋሙና በመረጃ ሰጪዎች መካከል አለመተማመንና ቅራኔን ሊፈጥር ይችላል።*

3.9 ***ፈጠራ***

- *ሥራው አዳዲስ ሃሳቦችን በማመንጨት፣ ማኑዋሎችንና መመሪያዎችን በማዘጋጀት፣ የተሻሻሉ አሰራሮችን በመቀየስና ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲሰፋፉና ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግን ይጠይቃል።*

3.5. ***የሥራ ግንኙነት*** /Work Communication/

3.5.1 **የግንኙነት ደረጃ**

- በውስጥ ከክፍል ኃላፊውና ከክፍሉ ባለሙያዎች፣ በውጭ በተለያዩ ተቋማት፣ በአምራቾችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ከሚገኙ ከፍተኛ ባለሙያዎችና ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

3.5.2 **የግንኙነቱ ዓላማ**

- የስራ መመሪያ ለመቀበል፣ ሪፖርት ለማቅረብ፣ ለማስረዳት፣ መረጃ ለማግኘት፣ የጥናት ውጤቶችን ለማቅረብ፣ ግብረ መልስ በመቀበልና በመስጠት ለሚፈለገው አገልግሎት እንዲውል ለማድረግ ነው።

**3.5.3 የግንኙነቱ ድግግሞሽ**

- ከቀን የስራ ጊዜው 50% ይሆናል፡፡

**3.6 ኃላፊነት**

**3.6.1 ኃላፊነት ለሰው ሀብት**

**3.6.1.1 በኃላፊነት የሚመራቸው ሠራተኞች ብዛት**

- ሦስት።

**3.6.1.2 የኃላፊነት አይነትና ደረጃ**

- የለበትም።

**3.6.2 ኃላፊነት ለንዋይ**

- የለበትም።

**3.6.3 ኃላፊነት ለንብረት**

- ለሥራው የሚያስፈልጉ በግምት ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ የሚሆኑ እንደ ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ ዴስክቶፕና ላፕቶፕ ኮምፒውተሮች፣ መቅረፀ ድምፅ ፣ ፋይል ማስቀመጫ ሼልፍ ያሉ ንብረቶችን በአግባቡ በመያዝ የመጠቀም ኃላፊነት አለበት።

## 3.7. ጥረት

**3.7.1 የአዕምሮ ጥረት**

- ሥራው እቅድና የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት መንደፍ፤ መረጃዎች የሚሰበሰቡበትን አጀንዳዎችን መቅረጽ፣ መረጃን በቀላሉ ለማግኘት የሚያስችሉ መጠይቶች መቅረጽ፣ ተገቢውን ዘዴዎች ተከትሎ የህዝብን አመለካከት፣ ስሜት፣ ፍላጎትና ዝንባሌ ለማወቅ የሚያስችሉ የህዝብ አስተያየት ትንተና ማካሄድ፣ ከህዝብ የሚሰበሰቡ መረጃዎች የተሟሉና ትክክለኛ መሆናቸውን ማረጋገጥና መተንተን፣ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ግንኙነት ፈጥሮ በፍላጎታቸውና መግባባት ለተደረሰባቸው ጉዳዮች የማስፈፀሚያ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ ከህዝብ አስተያየት ትንተና የተገኙ ውጤቶችን በቅርብ ኃላፊ አስገምግሞ ሲሆን ከቀን የሥራ ጊዜው 65 % ይሆናል።

**3.7.2.ስነልቦናዊ ጥረት**

- ስራው በአብዛኛው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት እንዲሁም ከአገልግሎት ሰጪ እና ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የሚያገናኝ በመሆኑ የስራውን አስፈላጊነት እና ዓላማ ለማሳመንና ለማግባባት በሚሞከርበት ጊዜ አልፎ አልፎ የሚከሰቱ አለመግባባቶች የሚፈጥሩትን ስነ ልቦናዊ ጫናን ተቋቁሞ ስራውን ውጤታማ ማድረግን ይጠይቃል።

3.7.3 **የዕይታ ጥረት፣**

- ስራው ከህዝብ የተሰበሰቡ አስተያየቶችን ትንታኔ በኮምፒዩተር ላይ መፃፍና ማንበብ፣ በወረቀት ላይም ሆነ በኮምፒዩተር ያሉ ህጎች፣ አዋጆች፣ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና ለስራው አጋዥ የሆኑ ተሞክሮዎችን መቀመር፣ የደንበኞችን ልዩ ልዩ ሰነዶች ማንበብና መረዳት የሚጠይቅ ሲሆን ይህም ከቀን የስራ ጊዜው 50% ይሆናል።

3.7.4 **የአካል ጥረት**

- ሥራው 75% በመቀመጥ እና 25% በመንቀሳቀስ የሚከናወን ነው።

3.8. **የሥራ ሁኔታ**

3.8.1. **ሥጋትና አደጋ**

- የለበትም።

3.8.2 **የሥራ አካባቢ ሁኔታ**

- ሥራው አልፎ አልፎ ከፍተኛ ሙቀትና ቅዝቃዜ፣ ወረርሽኝና የተለያዩ ግጭቶችና ሁከቶች፣ የተፈጥሮ አደጋዎች ባሉባቸው የተለያዩ መልክዓ ምድራዊ አካባቢዎች ሊሰራ ስለሚችል የጤና መታወክ ያጋጥማል።

3.9. **እውቀትና ክህሎት፣**

3.9.1. **ትምህርት**

| **የትምህርት ደረጃ** | **የትምህርት ዓይነት** |
|---|---|
| የመጀመሪያ ዲግሪ | በኮሚዩኒኬሽንና ጋዜጠኛነት፣ ፖለቲካል ሳይንስና አለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቋንቋና ስነ-ጽሁፍ፣ ስራ አመራር፣ ሶሺዮሎጂ እና ሶሻል አንትሮፖሎጂ ታሪክ ቢዝነስ አድምንስትሬሽን፣ ኢኮኖሚክስ በመጀመሪያ ዲግሪ ከስራው ጋር ግንኙነት ያለው 4 ዓመትየሥራ ልምድ ያለው /ያላት/ መሠረታዊ የኮምፒዩውተር እውቀትያለው /ያላት/ |

3.9.2 **ሥራውን ለመጀመር የሚያስፈልግ የሥራ ልምድ**

<table>
<tr><td>የሥራ ልምዱ ለማግኘት የሚጠይቀው ጊዜ</td><td colspan="2">ልምዱ የሚገኝበት የሥራ ዓይነት</td></tr>
<tr><td>በመጀመሪያ ዲግሪ 4 ዓመት</td><td colspan="2">በማህበራዊ ጉዳዮች ጥናትና ሥራዎች የተገኘ ልምድ</td></tr>
<tr><td colspan="3"></td></tr>
<tr><td>የሥራ ትንተና ባለሙያ ሥም</td><td>ፊርማ</td><td>ቀን</td></tr>
<tr><td></td><td></td><td></td></tr>
<tr><td colspan="3"></td></tr>
</table>

| የሥራ ዝርዝሩን ያጸደቀው የኃላፊው ሥም | የሥራ መደቡ መጠሪያ | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| | | | |

| **የሥራ ዝርዝር መግለጫ ቅጽ፤** | | |
|---|---|---|
| **I. አጠቃላይ መግለጫ** | | |
| **የመስሪያ ቤቱ ስም** | **የሥራ መደቡ መጠሪያ** | **የሥራ ዘርፍ/የሥራ ሂደት** |
| **ሲ/ብ/ክ/መ/የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ** | **የኮሙዩኒኬሽን ጥናትና አቅም ግንባታ ቡድን መሪ** | **ህዝብ አስተያየት፣ ጥናትና የኮሙዩኒኬሽን አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት** |
| | | |
| **የቅርብ ኃላፊ የሥራ መደብ /ተጠሪነት** | **የሥራው ደረጃ** | **የሥራው ኮድ** |
| **ለዳይሬክተሩ** | XV | |
| | | |
| **መስሪያ ቤቱ የሚገኝበት ቦታ** | | |
| **ሀዋሳ** | | |
| **II. የሥራ መደቡ ዋና ዓላማ፤ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት** | | |

2.1. **የሥራ መደቡ ዓላማ፡-**

- *የጥናትና ምርምር ተግባራትን በማቀድ፣ በመምራት፣ በማስተባበር፣ የአሰራር ስርአት በመዘርጋትና ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲሁም የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በአፈፃፀም ወቅት የሚያጋጥማቸውን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ ጥናትና ምርምሮችን በማካሄድ፤ የመፍትሔ ሀሳብ በማመንጨት፤ በየወቅቱ ያለውን እድገት እና ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ ብቃትና ብስለት ያላቸው ሳይንሳዊና ዘመን ተሻጋሪ ሃሳቦችን በማፍለቅ፣ ክልላዊ የኢንፎርሜሽንና የሚዲያ ጥናትና ምርምር ስራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ ነው::*

2.2. **ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት**

**ውጤት1:- ክልላዊ የኮሙዩኒኬሽንና ሚዲያ ጥናትና ምርምር ስራዎችን ማቀድ፣ መምራት፣ ማስተባበርና መከታተል፡፡**

- *ከዳይሬክቶሬቱ እቅድ በመነሳት የጥናት-ምርምር ስራዎች የሚመሩበትን እቅድ አዘጋጅቶ ለባለሙያዎች ያወርዳል፤ ያስተባብራል፣ ተፈጻሚነቱን ይከታተላል፣ ውጤቱንም ይገመግማል፣*
- *የሚዲያና የኮሙዩኒኬሽን ኢንዱስትሪን ለማዘመን የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን፣ መልካም አጋጣሚዎችን የሚለይ*

እና የዘርፉን ስትራተጂክ ግቦችን የአፈጻጸም አቅጣጫዎች የሚያመላክት ፍኖተ-ካርታ በማዘጋጀት የፖሊሲ ምክረ ሃሳብ ያመነጫል፤

- በዘርፉ የጠለቀ የትብብር ምርምሮች እንዲካሄዱ ግንኙነት በመፍጠር ሥራዎችን በአመለካከት፣ ዕውቀትና ክህሎት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይደግፋል፣ ያበቃል፣
- የጥናትና-ምርምር ስራ የሚያከናውኑ በዘርፉ ስር ያሉ የተለያዩ ተቋማት የራሳቸውን ተግባራት በብቃት እንዲያከናውኑ ይደግፋል፣ ያስተባብራል፣
- የዳታ ኢንዱስትሪ ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ፕሮግራሞች በመፈተሽና ፎርማት ቅጾችን በማዘጋጀት ወደ ኮምፒውተር የሚገቡ መረጃዎችን ያረጋግጣል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣ ጥራቱን የጠበቀና አስተማማኝ መረጃ ለተጠቃሚው እንዲደርስ እገዛ ያደርጋል፡
- ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በቡድኑ ስር ያሉ ባለሙያዎችን እንዲሁም ለክልሉ ለጥናትና ምርምር መረጃ ሰብስበው የሚልኩ አካላትን የአቅም ክፍተቶች ይለያል፣ አቅማቸው እንዲጎለብት ያደርጋል፣
- መንግሥት ፈጣን ለውጥ ለማምጣት ከሚያደርጋቸውን ጥረት ጋር ተያይዞ ያሉትን ጉዳዮች በማጥናት የለውጥ መሳሪያዎችን በክልላችን እስከ አሁን ምን ለውጥ እንዳመጡና በተግባር ሲፈፀሙ ያጋጠሙ ችግሮችን ይለያል፤ የመፍትሄ አቅጣጫ እንዲሰጥበት ያደርጋል፡፡
- የባለሙያዎች የስራ አፈጻጸም በየደረጃው ይገመግማል፤ ሪፖርቶችን ያዘጋጃል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል፤
- የሰው ሀይል፣ የማቴሪያልና በጀት እንዲሟላለት የረጅምና የአጭር ጊዜ ዕቅዶችን ነድፎ ተግባራዊ ያደርጋል፤
- የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ለኃላፊዉ ያቀርባል፣

**ውጤት 2፣ በኮሙኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ በምርምር፣ በጥናት፣ በትንተና እና በስርጸት ብቃትና ብስለት ያላቸው ሳይንሳዊና ዘመን ተሻጋሪ ሃሳቦችን ማፍለቅና ማስረጽ፤**

- በቁልፍ ህገ መንግስትታዊ፣ ዓላማዎች፣ መርሆዎች፣ እሴቶች፣ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ስልቶችና ፕሮግራሞች እንዲሁም በሌሎች ወቅታዊ መሠረታዊ ጉዳዮች እና ክልላዊ አጀንዳዎች ዙሪያ የጋራ ብሄራዊ መግባባት መድረስን እንዲሁም ክልላዊ ገጽታችን በተመዘገቡና በሚመዘገቡ ስኬቶች መጠን መታወቁን በጥናት ያረጋግጣል፣
- የጥናትና የምርምር ስራዎች ውጤት ለመንግስት ከፍተኛ ሀላፊዎች ለተለያዩ ባለድርሻ አካላትና ለህዝብ ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል፣ ለግብአትነት መዋላቸውንም ያረጋግጣል፤

- የኮምዩኒኬሽን ምርምሮችና የህዝብ አስተያየት ጥናቶችን በዋና ዋና ክልላዊ ወይም ሰፊ ተደራሽነት ባላቸው የሃገር ውስጥና የውጭ ሚዲያዎች እንዲሰራጩ ያደርጋል፤ ዓውደ ጥናቶችና ምክክሮች ያካሂዳል፤ በክልላዊና በተለያዩ ዓለም አቀፍ ጆርናሎችም ታትመው ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
- መሠረታዊ በሆኑ የክልላችን ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ስራዎች ክፍተቶች ላይ ሙያዊና ፖለቲካዊ ጥናት ያካሂዳል፣ ይህንንም በማያቋርጥ ሂደት በየጊዜው በማከናወን ውጤታማነቱን ይገመግማል፤

- ቀልጣፋና ውጤታማ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ለማድረግ የመንግስት የኮሙኒኬሽን ፍላጎት(Government communication needs) እና የህዝቡ የኢንፎርሜሽን ፍላጎት(Public information needs) በጥናት ይለያል፣ የጥናቱን ውጤት በመገምገም ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለሀላፊው ያቀርባል፣
- ከውጭና ከአገር ውስጥ የጥናት-ምርምር ተቋማት የሚገኙ የጥናት ውጤቶች እንዲሁም በትምህርታዊ ጉብኝቶች የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችና ልምዶች እንዲቀመሩና እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ ውጤታማ የሚሆኑበትን ስልት በመንደፍ ያስገኙትን ውጤት ይገመግማል፤
- የኮሙኒኬሽንና የሚዲያ ምርምር እና የህዝብ አስተያየት ጥልቅ ጥናቶች ያካሂዳል፤ እንዲካሄዱም አመራር ይሰጣል፣ የተገኙ ውጤቶችን መሠረት በማድረግም የኮሙኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ በየወቅቱ በተለያዩ ቋንቋዎች የሚያስተገቧቸው ክልላዊ አጀንዳዎች እንዲቀረጹ የውሳኔ ሃሳብ ለኃላፊ ያቀርባል፣
- በሀገር ውስጥ ወይም በውጭ ሙያተኞች ጥልቅ ምርምር የሚሹ ጉዳዮችን በመለየት የጥናት- ምርምር ፕሮጀክት ምክረ ሃሳብ ያዘጋጃል፤ የፕሮጀክት ሰነዶችን ይገመግማል፣ እንዲጸድቁና ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣
- የክልላን ራዕይና የህዳሴውን ጉዞ እውን ለማድረግ በየወቅቱ የሚቀርጻቸው ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች፣ ስትራቴጂዎች፣ ስልቶች እንደግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ ክልላዊ የኮምዩኒኬሽን ምርምሮችና የህዝብ አስተያየት ጥናቶች ያካሂዳል፤ እንዲካሄዱ ያደርጋል፤ ለመንግስት ከፍተኛ አመራር አካላት ያቀርባል፤ ውጤቱንም ይገመግማል፤
- በልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ዝግጅትና ትግበራ ዙሪያ ህብረተሰቡ የተሟላ መረጃ እንዲኖራው የኮምዩኒኬሽን ምርምርና የህዝብ አስተያየት ጥናቶች የተቀመሩ ሰነዶችን የማህበራዊ ሚዲያ (social media) ጨምሮ በተለያዩ የኮምዩኒኬሽንና ሚድያ አውታሮች በተለያዩ ቋንቋዎች ወቅታዊና የደረጁ መረጃዎችን ለህዝቡ በማቅረብ ግልፅነት ይፈጥራል፤ በዓለም አቀፉ ህብረተሰብ ዘንድ ስለክልላችን ቀዳሚና የተሟላ የመረጃ ምንጭ መሆን የሚቻልበትን አቅም ይገነባል፤

**ውጤት 3:- በየወቅቱ ያለውን እድገት፣ ተጨባጭ ሁኔታ፣ አዳዲስ ፈጠራዎችንና አሰራሮችን መሰረት ያደረገ የፖሊሲ ምክረ-ሀሳብና የማማከር አገልግሎት መስጠት፡፡**

- ዓበይትና ወቅታዊ ክልላዊ ሁኔታዎች የሚገመግሙበት እንዲሁም ዓለማቀፍ ጉዳዮች የሚተነትኑበት፣ ከአገር ውስጥ እና ከውጭ ሃገር የምርምርና ጥናት ተቋማት ጋር በጋራ ልምድ የሚቀሰምበት፣ ፕላት ፎርም እና አሰራር እንዲኖርና ሁሉም በቅድመ - ዝግጅት የሚከናወኑበት አካሄድ እንዲበጅለት ይተልማል፤ አመራር በመስጠት ተግባራዊ ያደርጋል፤
- የባለድርሻ አካላት እንዲጎለብት መደበኛ የሥራ ግንኙነት ይፈጥራል፤ ተልዕኮን በጋራ ለመፈፀም የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ዘርግቶ ስኬታማ ተግባራት ያከናውናል፤
- የምክክር መድረክ በመፍጠር፣ ምርምርና ጥናት የሚሹ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን በመለየት ጉልህ ሚና ካላቸው

የምክር አገልግሎት ከሚሰጡ፣ የአሰራር ስርዓት ከሚዘረጉና ከሚገነቡ ተቋማት ጋር በጋራ ይሰራል፤

- የኮምዩኒኬሽንና ሚድያ ኢንዱስትሪው ከዩኒቨርሲቲዎችና ሌሎች የጥናት፣ ምርምር ተቋማት፣ የምክር ሰጪ ተቋማት ወዘተ/ ግንኙነት(leankage) የሚጠናከርበት ሥርዓት በአግባቡ እንዲዘረጋ በማድረግ ውጤታማ ተግባራት ያከናውናል፡፡
- የኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ ሳይንሳዊ በሆነ አግባብ ስትራቴጂክ አመራር ለመስጠት የሚያስችል የኮሙኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ የጥናትና ምርምር የልህቀት ማዕከል ያደራጃል፣ በውጤታማነት ይመራል፤
- የመንግስት ተልዕኮን የሚያሳካ የጥናት፣ የምርምር እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ተቋማት ዓይነትና ተልዕኮ እንዲሁም ትስስር ምን መሆን እንዳለበት የውጭ አገር ልምድ ይቀምራል፣ ምርጥ ተሞክሮው እንዲስፋፋ ያደርጋል፤
- ለፖሊሲ አውጭዎች ጠቃሚ የሆኑ ግብአቶች ለመስጠት የተቋቃሙ የሃገር ውስጥና የውጭ የግል ተቋማትና ታዋቂ ምሁራን ጋር ትስስር ይፈጥራል፤ ከውጭ አገር የመንግስት አካላት እና ከጥናትና ምርምር ተቋማት ጋር የምርጥ ተሞክሮች ልውውጥ እንዲካሄድ ያደርጋል፤
- የተቀረጹና የጸደቁ የአሠራር ሰነዶች /መመሪያ፣ ማንዋል፣ ጋይድላን ወዘተ/ ጥራታቸው የሚፈተሽበት ሥርዓት ተግባራዊ በማድረግ ወደ ተግባር የሚሸጋገሩበትን ዘዴዎች ያመቻቻል፣ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፣

## III. የሥራው ባህሪ መግለጫዎች፤

### 3.1 የሥራ ውስብስብነት

- ስራው ክልላዊ የኮሙዩኒኬሽን ጥናትና ምርምር ስራዎች የሚመራበትን እቅድ አዘጋጅቶ ማከፋፈል፤ ማስተባበር፣ ተፈጻሚነቱን መከታተል፣ ውጤቱንም መገምገም፣ የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በአፈፃፀም ወቅት የሚያጋጥማቸውን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ ጥናትና ምርምሮችን ማካሄድ፤ በምርምር በትንተና እና በስርጸት ብቃትና ብስለት ያላቸው ሳይንሳዊና ዘመን ተሻጋሪ ሃሳቦችን ማፍለቅ፤ በሃይማኖቶች እኩልነትና የሴኩላሪዝም መርሆዎች ዙሪያ፣ በመቻቻልና የጋራ እሴቶች የማጠናከር ጉዳይ እንዲሁም አክራሪነትና ፅንፈኝነት በመድፈቅ ዙሪያ በመላው ህዝብ ዘንድ ብሔራዊ መግባባት እንዲፈጠር ሁሉን አቀፍ፣ ተከታታይ፣ የተቀናጀና ወጥነት ያለው ሰፊ ምርምር ማካሄድ፤ ከክልሉ ፕሬዝደንት መግለጫዎችና ንግግሮች ሲቀርቡ የሕዝብ አስተያየቶችን በማሰባሰብና አያይዞ በመተንተን ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመንግስት ከፍተኛ ኃላፊዎች መስጠት፣ ለግብዓትነት መዋላቸውንም ማረጋገጥ፤ በሚዲያና ሞኒተሪንግ ውጤቶች ላይ የአዝማሚያ ትንተና እንዲካሄድ በማድረግ በህዝቡ ዘንድ የተፈጠሩ አዎንታዊና አሉታዊ አስተሳሰቦች እንዲሁም የዓለም ማህበረሰብ ያለውን አተያይ ማሳወቅ፤ ምርምርና ጥናት የሚሹ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን መለየትና ማካሄድ እንዲሁም የምክር አገልግሎት መስጠት፤ ጥናትና ምርምር የሚደረግባቸውንና ትኩረት የሚሹ ርዕሰ ጉዳዮችን በመለየት ሥራው የሚመራበትን ዝክረ ተግባር እንዲዘጋጅና ወደ ሥራ እንዲገባ ማድረግ፣ ተግባራዊነቱንም መከታተል፣ የኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ ሳይንሳዊ በሆነ አግባብ ስትራቴጂክ አመራር ለመስጠት የሚያስችል የኮሙኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ጥናትና ምርምር የልህቀት ማዕከል ለማደራጀት የሚያስችል አዳዲስ አሰራሮችን መዘርጋት፣ የኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ አሠራር በውጤታማነት

ተፈጻሚ እንዲሆን የሚያስችሉ አዳዲስ ሃሳቦችን በማፍለቅ ከማብራሪያ ጋር ማቅረብ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ለማድረግ የመንግስት የኮሙኒኬሽን ፍላጎትና የህዝቡ የኢንፎርሜሽን ፍላጎት በጥናት እንዲለዩ ማድረግ፣ የጥናቱን ውጤት ከውሳኔ ኃሳብ ጋር ለኃላፊው ማቅረብ፤ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን፣ መስፈርቶችና መርሃግብሮችን አዘጋጅቶ የማጸደቅ፣ ተግባር ላይ እንዲውሉም ማድረግ፣ አፈጻጸሙንም መከታተል፣ የኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፉን ውጤታማ ለማድረግ የተዘጋጁ የጥናትና ምርምር ፕሮጀክት ሰነዶችን በማዘጋጀትና ወደ ተግባር በማሸጋገር ውጤታማነቱን እየተከታተለ ለኃላፊው ማቅረብ፣ የምርምር ውጤቶች እንዲሁም የህዝብ አስተያየት ጥናቶች የክልላችን ራዕይና ህዳሴ እውን ለማድረግ መንግስት የሚቀርጻቸው ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ስልቶች እንደግብዓት ሆነው በሚያገለግል አግባብ እንዲጠና ማድረግ፤ የሁለትዮሽ የስምምነት ሰነድ ማዘጋጀት፣ በስራው ላይ ዕውቀት እንዲጨብጡ ማድረግና የተግባር ስምሪት መስጠት ሲሆን

- በክንውን ወቅት ክልላዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚው ለውጥ በሚፈለገው ደረጃ የጋራ አገራዊ አስተሳሰብ አለመፍጠር፣ በጎ ገፅታ አለመገንባት፣ በየወቅቱ ያለውን እድገት እና ተጨባጭ ሁኔታ አለመገንዘብ፤ የክልል የመንግስት አመራር አካላት ፈጣንና ወቅታዊ ውሳኔ አለመስጠት፤ በተሰጠው የጋራ አመራርና ስምሪት የባለድርሻ አካላት ተቀናጅተው አለመስራት፤ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እንዲሁም ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ተቋማት በትብብር ለመስራት ፍላጎት አለማሳየትና በቂ ድጋፍ አለመስጠት፤ መንግስት የሚያስቀምጣቸው አቅጣጫዎችና የሚያወርዳቸው አሰራሮች አስመልክቶ የጋራ አረዳድ አለመኖር፤ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ተልዕኳቸውን በህዝባዊ ኃላፊነት አለመወጣት፤ የጥናትና ምርምር ተቋማት በቅንጅት ለመስራት ፈቃደኛ አለመሆን፣ ህዝቡ የሚፈልገውን ኢንፎርሜሽንና ሃሳቡን በግልፅ አለማሳወቅ፣ የጥናትና ምርምር ሰነዶች፣ የፕሮጀክት ሰነዶች፣ መመሪያዎች፣ ማንዋሎችና ስታንዳርዶች የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው አለመዘጋጀት፣ አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶች ቶሎ ተቀባይነት አለማግኘት የሚያጋጥሙ ችግሮች ናቸው፡፡
- እነዚህም ችግሮች የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በአፈፃፀም የሚያጋጥማቸውን ችግሮች በጥናት ላይ ተመስርቶ በመፍታት፤ የመፍትሔ ሃሳብ በማመንጨት፤ በየወቅቱ ያለውን እድገት እና ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ አዳዲስ  ሀሳቦችን በማቅረብ፤ በሃይማኖቶች እኩልናትና የሴኩላሪዝም መርሆዎች ዙሪያ፣ በመቻቻልና የጋራ እሴቶች በማጠናከር፤ አክራሪነትና ፅንፈኝነት በመድፈቅ ዙሪያ በመላው ህዝብ ዘንድ ብሔራዊ መግባባት በመፍጠር፤ የሕዝብ አስተያየቶችን በማሰባሰብና በመተንተን ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመንግስት ከፍተኛ ኃላፊዎች በመስጠት፣ በህዝቡ ዘንድ የተፈጠሩ አዎንታዊና አሉታዊ አስተሳሰቦች እንዲሁም የዓለም ማህበረሰብ ያለውን አተያይ በማሳወቅ፤ ምርምርና ጥናት የሚሹ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን በመለየት፤ የምክር አገልግሎት በመስጠት፤ ተራማጅ አስተሳሰብ ያላቸው ዜጐች በማፍራት፤ መልካም ገፅታ ለመገንባት የሚያስችሉ የጥናትና ምርምር ተግባራትን በሚዲያና ኮሙኒኬሽን አግባብ በመፈጸምና በማጎልበት፤ የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት የማያቋርጥ የግንዛቤ ስራ በመስራት፣ በአለም ላይ ያለውን ተጨባጭ እውነታ ከክልሉ የዕድገት ደረጃ ጋር

የተጣጣመ ምርምርና ጥናት እንዲካሄድ በማድረግ፣ የተሟላ መረጃ እንዲይዙ ተገቢውን ጥረት በማድረግ፣ ከአሳማኝ መረጃ ጋር በማቅረብና አስፈላጊውን ማብራሪያ በማቅረብ፣ የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሞ የህብረተሰቡን ሀሳብ በማግኘት፣ የአደረጃጀቶችን ባህሪይ ታሳቢ ባደረገ መልኩ የዳሰሳ ጥናቱ እንዲካሄድ አቅጣጫ በመስጠት፣ የፕሮጀክት ሰነዶችና የአሰራር ስርአት ሰነዶች ጥራታቸው የሚፈተሽበት ሥርዓት ተግባራዊ እንዲሆን በማድረግ፣ የቅርብ የክትትል፣የድጋፍ፣የመግባባትና የማሳመን ስራ በመራስት የሚፈቱ ናቸው፡፡

## 3.2 ራስን ችሎ መስራት

### 3.2.1 ሥራው የሚከናወንበት አግባብ

- ሥራው ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ አዋጆችን፣ ደንቦችን፣ ስትራቴጂካዊና ታክቲካዊ ዕቅዶችን፣ አለም ዓቀፍ ተቀባይነት ያላቸው የስልጠናና ትምህርት ስታንዳርዶች እና መለኪያዎች፣ መመሪያዎች፣ ፕሮግራሞች፣ መርሆች፣ ንድፈ-ሐሳቦች፣ አለም ዓቀፍ ኮንቬንሽኖች፣ የፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ሰነዶች፣ ከሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር የተፈጸሙ የሁለትዮሽና የባለብዙ ስምምነት ሰነዶች መሠረት በማድረግ ይከናወናል፡፡

### 3.1.1. ሥራው የሚጠይቀው የክትትልና ድጋፍ ደረጃ

- ሥራው የጥራት ደረጃውን ጠብቆ ተፈላጊውን ግብ ያሳካ ከመሆኑና፣ ካስገኘው ለውጥ አንጻር ስለመከናወኑ አጠቃላይ ግምገማ ይደረግበታል፡፡

## 3.3 ተጠያቂነት

### 3.3.1 ተጠያቂነት ለሥራ ውጤት /Responsibility for Impact/፣

- ሥራው በየወቅቱ ያለውን እድገት፣ ተጨባጭ ሁኔታና አዳዲስ ፈጠራዎችን መሰረት ያደረገ የፖሊሲ ምክረ-ሀሳብና የማማከር አገልግሎት ባይሰጥ፡፡ ንድፈ-ሐሳቦች፣ ፕሮግራሞችና መርሆች ተነድፈው ባይተገበሩ፣ በምርምር በትንተና እና በስርጸት ብቃትና ብስለት ያላቸው ሳይንሳዊና ዘመን ተሻጋሪ ሃሳቦች ከመንግስታዊ፣ መንግስታዊ ካልሆኑ የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እንዲሁም ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ተቋሞች ጋር የትብብር ግንኙነት ባይመሰረትና ድጋፍ ባይደረግ፤ መንግስት የሚያስቀምጣቸው አቅጣጫዎች፣ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አስመልክቶ የጋራ አረዳድ ባይፈጠር፤ ክልላዊ የኮምዩኒኬሽንና ኢንፎርሜሽን የልህቀት ማዕከል አቋቁሞ ጥልቀትና ብስለት ያለው የኮሙዩኒኬሽንና ሚዲያ ጥናት-ምርምር እንዲሁም ከውጭ አገርና ከአገር ውስጥ የምርምር ተቋማትና የከፍተኛ የትምህርት ጋር ግንኙነት ባይፈጠር፤ የትብብር ምርምሮችን ለማካሄድ ስትራቴጂ ባይነድፍ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ለማድረግ የመንግስት የኮሙኒኬሽን ፍላጎትና የህዝቡ የኢንፎርሜሽን ፍላጎት በጥናት እንዲለዩ ባያደርግና የጥናቱን ውጤት ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለመንግሥት ባያቀርብ፣ ፕሮግራሞች፣ የአሰራር ስርአት ሰነዶችን ገምግሞ እንዲጸድቁና ተግባራዊ እንዲሆን ባያደርግ፣ ከውጭና ከአገር ውስጥ በጥናትና ምርምር ስራዎች የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችና ልምዶች እንዲቀመሩና እንዲስፋፉ ባያደርግና ውጤታማ የሚሆኑበትን ስልት በመንደፍ ያስገኙትን ውጤት ባይገመግም፣

የኮሙኒኬሽን ምርምርና የህዝብ አስተያየት ጥናቶች፣የኮምዩኒኬሽንና የሚድያ ሞኒተሪንግ ውጤቶች የአዝማሚያ ጥናቶች እንዲካሄዱ ባያደርግና ውጤትን መሠረት በማድረግ አጀንዳ እንዲቀረፅ የውሳኔ ሃሳብ ለኃላፊው ባያቀርብ፣ በአገር ውስጥ ወይም በውጭ ሙያተኞች ጥልቅ ምርምር የሚሹ ጉዳዮችን በመለየት የጥናት-ምርምርና አቅም ግንባታ የፕሮጀክት ሰነዶችን ገምግሞ እንዲጸድቁና፣ ተግባራዊ እንዲሆኑ ባያደርግ፣ የጥናትና የምርምር ስራዎች ውጤት ለከፍተኛ የመንግስት፣ ለተለያዩ ባለድርሻ አካላትና ለህዝብ ተደራሽ እንዲሆን ባያደርግ፣ ፕሮግራሞች፣ መርሆች፣ ንድፈ-ሐሳቦች ባይነደፉ አፈጻጸሙንም ባይከታተል ወይም እነዚህ ተግባራት የጥራት ደረጃውን ጠብቀው ባይከናወኑ ወይም በክንውን ወቅት የሚፈጸሙ ስህተቶች በወቅቱ ባይታረሙ በመረጃ የበለፀገና በክልሉ ጉዳይ ንቁ ተሳትፎ የሚያደርግ ኅብረተሰብ እንዳይገነባ ያደርጋል፣ የዘርፉ እንቀሳቃሾች ጥቅምና የፈጠራ ተነሳሽነትን ያዳክማል፣ መንግሥት ለሕዝብ ጥያቄዎች ፈጣን ምላሽ ለመስጠት ያለውን ብቃትም ያዳክማል፡፡ ይህም ህዝቡ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ በፍትሃዊነት ተጠቃሚ ስለማይሆን ለልማት፣ ለዲሞክራሲና ለሰላም የሚኖረው ተሳትፎ ሊዳከም ይችላል፤ ህዝቡና ዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ በመካሄድ ላይ ባለው ለውጥ እየተፈጠረ ያለውን አዲስ እውነታ በትክክል እንዳይገነዘብ ያደርጋል፤ በክልሉ ያለውን በጎ አመለካከትም ሊሸረሸር ይችላል፣ ይህም በተቋሙ ገጽታ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይፈጥራል፡፡

3.3.2 **ተጠያቂነት ለሚስጥራዊ መረጃ፣**

- ስራው የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነጻነትን ለመደንገግ በወጣ አዋጅ ቁጥር 590/2000 ዓ/ም በአንቀጽ 38 በንኡስ አንቀጽ 2 ላይ እንደተገለጸው፤ ማንኛውም የመንግስት አካል በእጁ የሚገኙ ሰነዶችን የመጠበቅ ግዴታ አለበት ይላል፡፡ እነዚህ ሚስጥራዊ መረጃዎች ማለትም የፖሊሲ ለውጥ የማድረግ ወይም ያለማድረግ ውጥንን፣ የውሳኔ አሰጣጥን ወይም የፖሊሲ ቀረጻን ለማገዝ የቀረቡ ወይም የተዘጋጁ አስተያየቶችና የውሳኔ ሃሳቦች እንዲሁም ህዝብና መንግስት በአስቸኳይ ሊያውቃቸው የሚገቡ መረጃዎችን፣ በሚመለከተው አካል ውሳኔ አግኝተው ይፋ ከመደረጋቸው አስቀድሞ በሚስጥር ካልተያዙ፣ በተለይም ግጭትን ወይም ቀውስን አስመልክቶ የሚካሄዱ ጥናትና ምርምሮች እንዲሁም የህዝብ አስተያየቶችና በርካታ ምስጢራዊ መረጃዎች ግንዛቤ ተይዞባቸውና ተለይተው በጥንቃቄ ጥቅም ላይ ካልዋሉና ካልተያዙ ወይም የመረጃው ባለቤት የሆነ ከፍተኛ የመንግስት አካል መረጃው እንዲገለጽ በጽሁፍ ካልፈቀደ ወይም ለሌላ አካል ተላልፈው ከተሰጡና ከባከኑ ላልተፈለጉና ጉዳት ለሚያደርሱ ዓላማዎች ይውላሉ፤ ይህም በተቋሙ ላይ ተአማኒነትን ያሳጣል፡፡

**3.4 ፈጠራ**

- ስራው በምርምር በትንተና እና በስርጸት ብቃትና ብስለት ያላቸው ሳይንሳዊና ዘመን ተሻጋሪ ሃሳቦችን መፍጠርን ወይም ማፍለቅን፣ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታን መረዳት፣ የብሔራዊ ፖሊሲዎች እና እስትራቴጂዎችን ጥንካሬና ክፍተት በመለየት የመፍትሔ ሃሳቦችን መቀመርና ለሚመለከታቸው አካላት የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብን፣ በየወቅቱ ያለውን ተለዋዋጭ ዓለማዊ፣ ከባቢያዊና ሃገራዊ ሁኔታና እድገት፣ በመገንዘብና አዳዲስ ፈጠራዎችን መሰረት ያደረገ የፖሊሲ ምክረ-ሀሳብ ማመንጨትን፡፡ ክልላዊ የኮሙኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ የጥናት ምርምር ፕሮጀክቶች መቀረጽን፤ ጥልቅና ምጥቀት ባላቸው የጥናትና ምርምር ስራዎች ላይ የተመሰረተ

አዳዲስና አስተማማኝ ሁሉን አቀፍ ዘዴዎችን በመዘርጋት አሰራር ማሻሻልን፤ የህዝብንና የክልሉን ችግሮች ሳይንሳዊና ዘመናዊ በሆነ የኮምዩኒኬሽን ምርምርና በህዝብ አስተያየት አመራር ጥበብ መፍታትን፤ ፕሮግራሞችንና መርሆችን መንደፍን፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ማስረጽና ማስፋፋትን ይጠይቃል፡፡

### 3.5. የሥራ ግንኙነት /Work Communication/

#### 3.5.1 የግንኙነት ደረጃ

- ከውስጥ ከዳይሬክተር ኃላፊው፣ ከቡድን መሪዎች፣ ከሌሎች ዳይሬክቶሬቶች እንዲሁም ከውጭ ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣናት፣ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት፣ በሀገር ውስጥ ካሉ የተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ነው፡፡ ከክልል ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት፣ ከሀገር ውስጥና ከዓለም አቀፍ ኮሙኒኬሽንና ሚዲያ ተቋማት፣ ከከፍተኛ የምርምር ተቋማት ኃላፊዎች፣ ከፌደራል ኮሙዩኒኬሽን ተቋማት የሙያና ህዝባዊ ማህበራት እንዲሁም የተለያዩ አደረጃጀት ኃላፊዎች፣ ከተለያዩ የህዝብ ክንፍ አመራር አካላት፣ ከክልላዊ የኮሙዩኒኬሽንና ሚዲያ ኮሚቴ አባላት፣ ቦርድ አካላትና ከሚመለከታቸው አደረጃጀቶች ጋር በተከታታይ ግንኙነት ማድረግን ይጠይቃል፡፡

#### 3.5.2 የግንኙነቱ ዓላማ

- ከዘርፍ ኃላፊው ዳይሬክተሩ ተወያይቶ መግባባት በመድረስ የአመራር አቅጣጫና የስራ መመሪያ ለመቀበል፣ ለመስጠት፣ ሪፖርት ለማቅረብና ስራዎችንና ፕሮጀክቶችን ለመገምገም፤ የማማከር አገልግሎት ለመስጠት፣ በጋራ ለመስራት፣ ግብረ-መልስ ለመስጠትና ለመቀበል፣ ከወቅታዊና ዋናዋና ክልላዊ ጉዳዮችን እንዲሁም ከመንግስት የትኩረት አቅጣጫዎች ጋር የሚናበቡ የኮምዩኒኬሽን ምርምር እና የህዝብ አስተያየት የጥናት ርዕሶችን ለመምረጥ፣ በትብብር የጥናት ስራዎችን ለማካሄድ፣ አውደ ጥናት ለማካሄድ፣ የሐሳብና የልምድ ልውውጥ ለማድረግ፣ የጥናት ውጤቶችን ሰፊ ተደራሽነት ባላቸው ሚዲያዎች ተደራሽ ማድረግ፣ በጥናት በተመላከቱ ዋና ዋና ግኝቶች ላይ ስምምነት ለመድረስ፣ የህዝብንና የክልሉን ችግሮች ሳይንሳዊና ዘመናዊ በሆነ የምርምርና የንድፈ ሃሳባዊ የአመራር ጥበብ በመጠቀም ለህዝብ ጥያቄ ቅድሚያ በመስጠት ለመፍታት ብሎም የህዝብና የክልሉን ጥቅምን ለማስከበር፣ በህዝብ አስተያየት ጥናት ውስጥ የተለያዩ ፍላጎቶች ወይም ግልጽ ያልሆኑ አስተያየቶች ሊዳሰሱ ስለሚችሉ ጥንቃቄ የተሞላበት ማብራሪያ ለመስጠት፣ ለመደራደርና ለመወያየት፣ ምርጥ ተሞክሮን ቀምሮ ለማስረጽና ተግባራዊ ለማድረግ ነው፡፡

#### 3.5.3 የግንኙነቱ ድግግሞሽ

- ከቀን የስራ ጊዜው 70 በመቶ ይሆናል፡፡

### 3.6 ኃላፊነት

#### 3.6.1 ኃላፊነት ለሰው ሀብት

### 3.6.1.1 በኃላፊነት የሚመራቸው ሠራተኞች ብዛት

- 17 ባለሙያዎችን በቀጥታ የመምራት ኃላፊነት አለበት፡፡

### 3.6.1.2 የኃላፊነት አይነትና ደረጃ

- በዘርፉና በቢሮው የሚከናወኑ የኮምዩኒኬሽን ምርምርና የህዝብ አስተያየት ጥናቶች በተመለከተ ሃሣብ የማፍለቅ፣ ለመስኩ የሚያገለግል ስትራቴጂክ /የረዥም፣ የመካከለኛ ዘመንና አጭር/ እንዲሁም የኦፕሬሽናል/ዓመታዊ/ ዕቅዶችን ካስኬድ አድርጎ በጥብቅ ዲሲፕሊን የመምራት፡፡ ከፍተኛ የጥናትና የምርምር ተግባር የሚያከናውኑ ባለሙያዎችን የመምራት፣ የምርምር ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች የመንደፍ፣ የመተግበር፣ የመደገፍ፣ አፈፃፀማቸውን የመከታተልና የመገምገም፣ የማስተባበርና የማብቃት ሃላፊነት አለበት፡፡

### 3.6.2 ኃላፊነት ለንዋይ

- የለበትም፡፡

### 3.6.3 ኃላፊነት ለንብረት

- ለሥራ ማከናወኛ የሚሆን ዲጂታል ካሜራና መቅረጸ ድምጽ፣ ፕሮጀክት ስላይድ፣ ሪከርዲንግ፣ ዲጂታል ስልክ ወይም የእጅ ስልክ፣ ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ ሼልፍ፣ ዴስክቶፕ ኮምፒውተር፣ ከለር ፕሪንተር፣ ላፕቶት፣ ስካነር፣ ፋክስ፣ የእንግዳ መቀበያ ወንበሮች፣ ዲጂታል ቴሌቪዥንና ሬድዮ በግምት እስከ ብር 200 ሺህ ብር የሚደርስ ንብረት የመያዝና የመጠቀም ኃላፊነት አለበት፡፡

## 3.7. ጥረት

### 3.7.1 የአዕምሮ ጥረት

- የጥናትና ምርምር ውጤቶችን በመገምገም ግብረመልስ መስጠት፣ ለመንግስት አመራር አካላት የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ፣ የተቀናጀ አመራርና የጋራ ስምሪት መስጠትና አፈጻጸሙን መገምገም፤ የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እንዲሁም ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው የምርምር እንዲሁም መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋሞች ጋር የትብብር ግንኙነት መመስረት፤ የአሰራር ስርአቶችን መዘርጋትንና ድጋፍ ማድረግ፤ መንግስት የሚያስቀምጣቸው አቅጣጫዎች፣ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አስመልክቶ የጋራ አረዳድ እንዲኖር ማድረግ፤ የዘርፉን ስራ የሚያከናውኑ ተቋማት የራሳቸውን የምርምርና ስርፀት ስራ በብቃት እንዲያከናውኑ ማቀድንና ተፈጻሚነታቸውን መከታተል፣ የትብብር ምርምሮች እንዳካሄዱ ማድረግና ሂደቱን በበላይነት መምራት፣ የመንግስት የኮሙኒኬሽን ፍላጎት(Government communication needs) እና የህዝቡ የኢንፎርሜሽን

ፍላጎት(Public information needs) በጥናት እንዲለዩ ማድረግንና የጥናቱን ውጤት ከውሳኔ ኃሳብ ጋር አቅርቦ ማፀደቅ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፤ ከውጭና ከአገር ውስጥ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችና ልምዶች እንዲቀመሩና እንዲስፋፉ ማድረግና ውጤታማ የሚሆኑበትን ስልት በመንደፍ ያስገኙትን ውጤት መገምገም፤ ዘርፉን ውጤታማ ለማድረግ የተዘጋጁ የጥናት- ምርምና አቅም ግንባታ የፕሮጀክት ሰነዶችን በመገምገም እንዲጸድቁና ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ፣ የዘርፉን የጥናት-ምርምር ስራዎችን ውጤታማ የሚያደርጉ አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶች መዘርጋትንና ተፈፃሚነታቸውን መከታተል፣ በጥናት- ምርምር ዙሪያ የተለያዩ መድረኮችን አዘጋጅቶ ባለድርሻ አካላትንና ምሁራንን ማወያየት፣ የማማከር አገልግሎት መስጠት፣ በምርምር በትንተና እና በስርጸት ብቃትና ብስለት ያላቸው ሳይንሳዊና ዘመን ተሻጋሪ ሃሳቦችን ማፍለቅ፣ በየወቅቱ ያለውን እድገት፣ ተጨባጭ ሁኔታና አዳዲስ ፈጠራዎችን መሰረት ያደረገ የፖሊሲ ምክረ-ሀሳብ ማመንጨት፣ ጥልቅና ምጥቀት ባላቸው የጥናትና ምርምር ስራዎች ላይ የተመሰረተ አዳዲስና አስተማማኝ ሁሉን አቀፍ ዘዴዎችን በመዘርጋት አሰራር ማሻሻል፤ ፕሮግራሞችንና መርሆችን መንደፍ፣ ተልዕኮን በአግባቡ መረዳትና ማሳካት፣ ኘሮግራም መተንተን፣ የአመለካከት ስህተቶችን ወይም ዝንፈቶችን ማጣራት፣ ጥናታዊ ትንተናዎችን ማጠቃለል፣ የመፍትሔ ሐሳቦችን ለማግኘት የሚደረጉ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችል ጥልቀትና ብቃት ያለው ሃሣብ ለማመንጨት ከፍተኛ የሆነ የአዕምሮ ጥረትን የሚጠይቅ ሲሆን፣ ይህም ከቀን የስራ ጊዜው እስከ 70 በመቶ ይሆናል፡፡

### 3.7.2.ስነልቦናዊ ጥረት

- የጥናትና ምርምር ውጤቶችን መሰረት አድርጎ መንግስት የተሳሳተ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩና ስተቱን ለማረም መጋፈጥን የሚጠይቅ በመሆኑ፣ መንግሥት ከህዝብ አስተያየት ጥናት ውጤት ተነስቶ ለሕዝብ ጥያቄዎች አስቸኳይና ፈጣን ምላሽ መስጠት ያለበት ሁኔታ መኖሩና ውጥረት በተሞላበት መስራትን የሚጠይቅ በመሆኑ፤ በተለይ ክልላዊ አውደ ጥናቶች በሚካሄዱበት ወቅት ከተሳታፊዎች የተዛቡ፣ አፍራሽ እና አደገኛ አስተሳሰቦች የሚቀርቡበት እና አስተሳሰቡን ለማስተካከል ሙግት የሚደረግበት በመሆኑ ይህንን ስራ በማከናወኑ ሂደት ጫና፣ ስሜታዊነት፣ ስም ማጥፋት፣ ዘለፋ፣ ዛቻና ማስፈራሪያ ሊደርስበት የሚችል በመሆኑ ይህንን ከህዝብና ከመንግስት የሚደርስ ስነ ልቦናዊ ተጽዕኖን ተቋቁሞ ስራን በትጋት፣ በትዕግስትና በቁርጠኝነት መምራትን ይጠይቃል፡፡

### 3.7.3 የዕይታ ጥረት፣

- በመሰረቱ የኮምዩኒኬሽን ምርምር፣ የህዝብ አስተያየት ጥናቶች የሚካሄዱት በተለዋዋጭና በመሠረታዊ ክልላዊና ወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ያላቸው አመለካከትና አተያይ ምን እንደሆነ በጥልቀት ለማወቅ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ሰፊ አድማስ፣ የጠለቀ ዕውቀት፣ ክህሎትና ብቃት ይጠይቃል፡፡ እንዲሁም የፕሮጀክት ሃሳቦችን ማፍለቅ፣ መገምገም፣ ከባለድርሻ አካላት መልካም ግንኙነት ፈጥሮ እልህ አስጨራሽ

ድርድር ማድረግን ይጠይቃል፡፡ እነዚህን በአግባቡ በመቀመርና በመምራት ክልላዊ አጀንዳ ለመቅረጽ የሚያስችሉ እንዲሁም ለፖሊሲ ግብዓት የሚሆኑ ጥልቀት ያላቸው የጥናትና የምርምር ሥራዎች መተንተን፣ ማኑዋሎችንና የምርምር ውጤቶችን በተከታታይ በኮምፒውተር መጻፍ፣ በጥልቀት ማንበብ፣ መተርጐም፣ ጥናታዊ ጽሁፎችንና የተቀረጹ ቪዲዮችን እንዲሁም በኦንላየን የተላኩ የህዝብ አስተያየቶችን ኤዲት ማድረግ፣ ተልዕኮን በአግባቡ መረዳትና ማሳካት፣ ፕሮግራም መተንተን፣ ጥንቃቄ የተሞላበት እርምት መስጠት፣ የዕይታ ጥረትን የሚጠይቅ ሲሆን ይህም ከሥራ ጊዜው 50 በመቶ ይሆናል፡፡

**3.7.4 የአካል ጥረት**

- ሥራው 70 መቶ በመቀመጥ፣ 30 በመቶ በመንቀሳቀስ ይከናወናል፡፡

**3.8. የሥራ ሁኔታ**

**3.8.1. ሥጋትና አደጋ**

- የለበትም፡፡

**3.8.2. የሥራ አካባቢ ሁኔታ**

- ሥራው በጤና ላይ ችግር በማያስከትል አካባቢ የሚከናወን ነው።

**3.9. እውቀትና ክህሎት**

**3.9.1. ትምህርት**

| የትምህርት ደረጃ | የትምህርት ዓይነት |
|---|---|
| የመጀመሪያ ዲግሪ | በኮሚዩኒኬሽንና ጋዜጠኛነት፣ ፖለቲካል ሳይንስና አለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቋንቋና ስነ-ጽሁፍ፣ ስራ አመራር፣ ሶሺዮሎጂ እና ሶሻል አንትሮፖሎጂ ታሪክ ቢዝነስ አድምንስትሬሽን፣ ኢኮኖሚክስ በመጀመሪያ ዲግሪ ከስራው ጋር ግንኙነት ያለው 8 ዓመትየሥራ ልምድ ያለው /ያላት/ መሠረታዊ የኮምፒዩውተር እውቀትያለው /ያላት/ |

**3.9.2 ሥራውን ለመጀመር የሚያስፈልግ የሥራ ልምድ**

| የሥራ ልምዱ ለማግኘት የሚጠይቀው ጊዜ | ልምዱ የሚገኝበት የሥራ ዓይነት |
|---|---|
| በመጀመሪያ ዲግሪ 8 ዓመት | በኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ጥናትና ምርምር የልህቀት ማዕከላትና ከስራው ጋር ተያያዥነት ያለው በጥናትና ምርምር የተገኘ ልምድ |

| የሥራ ትንተና ባለሙያ ሥም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| | | |

| የሥራ ዝርዝሩን ያጸደቀው የኃላፊው ሥም | የሥራ መደቡ መጠሪያ | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| | | | |

| የሥራ ዝርዝር መግለጫ ቅጽ፤ | | |
|---|---|---|
| I. አጠቃላይ መግለጫ | | |
| የመስሪያ ቤቱ ስም | የሥራ መደቡ መጠሪያ | የሥራ ዘርፍ/የሥራ ሂደት |
| ሲ/ብ/ክ/መ/የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ | የኮሙዩኒኬሽን ጥናትና ምርምር<br>ባለሙያ IV | ህዝብ አስተያየት፣ ጥናትና የኮሙዩኒኬሽን አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት |
| | ብዛት፡- ሁለት ባለሙያ | |

| የቅርብ ኃላፊ የሥራ መደብ /ተጠሪነት | የሥራው ደረጃ | የሥራው ኮድ |
|---|---|---|
| ለቡድን መሪው | XIV | |

| መስሪያ ቤቱ የሚገኝበት ቦታ | | |
|---|---|---|
| ሀዋሳ | | |

II. የሥራ መደቡ ዋና ዓላማ፣ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት

2.1. የሥራ መደቡ ዓላማ፡-

- የጥናትና ምርምር ተግባራትን በማቀድ፣ በመምራት፣ በማስተባበር፣ የአሰራር ስርአት በመዘርጋትና ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲሁም የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በአፈፃፀም ወቅት የሚያጋጥማቸውን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ ጥናትና ምርምሮችን በማካሄድ፤ የመፍትሔ ሀሳብ በማመንጨት፤ በየወቅቱ ያለውን እድገት እና ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ ብቃትና ብስለት ያላቸው ሳይንሳዊና ዘመን ተሻጋሪ ሃሳቦችን በማፍለቅ፣ ክልላዊ የኢንፎርሜሽንና የሚዲያ ጥናትና ምርምር ስራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ ነው::

2.2. ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት

**ውጤት1፡- ክልላዊ የኮሙዩኒኬሽንና ሚዲያ ጥናትና ምርምር ስራዎችን ማቀድ፣ መምራት፣ ማስተባበርና መከታተል፡፡**

- ከዳይሬክቶሬቱ እቅድ በመነሳት የጥናት-ምርምር ስራዎች የሚመሩበትን እቅድ አዘጋጅቶ ለባለሙያዎች ያወርዳል፤ ያስተባብራል፣ ተፈጻሚነቱን ይከታተላል፣ ውጤቱንም ይገመግማል፣
- የሚዲያና የኮሙዩኒኬሽን ኢንዱስትሪን ለማዘመን የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን፣ መልካም አጋጣሚዎችን የሚለይ

እና የዘርፉን ስትራተጂክ ግቦችን የአፈጻጸም አቅጣጫዎች የሚያመላክት ፍኖተ-ካርታ በማዘጋጀት የፖሊሲ ምክረ ሃሳብ ያመነጫል፤

- በዘርፉ የጠለቀ የትብብር ምርምሮች እንዲካሄዱ ግንኙነት በመፍጠር ሥራዎችን በአመለካከት፣ ዕውቀትና ክህሎት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይደግፋል፣ ያበቃል፣
- የጥናትና-ምርምር ስራ የሚያከናውኑ በዘርፉ ስር ያሉ የተለያዩ ተቋማት የራሳቸውን ተግባራት በብቃት እንዲያከናውኑ ይደግፋል፣ ያስተባብራል፣
- የዳታ ኢንዱስትሪ ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ፕሮግራሞች በመፈተሽና ፎርማት ቅጾችን በማዘጋጀት ወደ ኮምፒውተር የሚገቡ መረጃዎችን ያረጋግጣል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣ ጥራቱን የጠበቀና አስተማማኝ መረጃ ለተጠቃሚው እንዲደርስ እገዛ ያደርጋል፡
- ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በቡድኑ ስር ያሉ ባለሙያዎችን እንዲሁም ለክልሉ ለጥናትና ምርምር መረጃ ሰብስበው የሚልኩ አካላትን የአቅም ክፍተቶች ይለያል፣ አቅማቸው እንዲጎለብት ያደርጋል፣
- መንግሥት ፈጣን ለውጥ ለማምጣት ከሚያደርጋቸውን ጥረት ጋር ተያይዞ ያሉትን ጉዳዮች በማጥናት የለውጥ መሳሪያዎችን በክልላችን እስከ አሁን ምን ለውጥ እንዳመጡና በተግባር ሲፈፀሙ ያጋጠሙ ችግሮችን ይለያል፤ የመፍትሄ አቅጣጫ እንዲሰጥበት ያደርጋል፡፡
- የባለሙያዎች የስራ አፈጻጸም በየደረጃው ይገመግማል፤ ሪፖርቶችን ያዘጋጃል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል፤
- የሰው ሀይል፣ የማቴሪያልና በጀት እንዲሟላለት የረጅምና የአጭር ጊዜ ዕቅዶችን ነድፎ ተግባራዊ ያደርጋል፤
- የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ለኃላፊዉ ያቀርባል፣

**ውጤት 2፣ በኮሙኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ በምርምር፣ በጥናት፣ በትንተና እና በስርጸት ብቃትና ብስለት ያላቸው ሳይንሳዊና ዘመን ተሻጋሪ ሃሳቦችን ማፍለቅና ማስረጽ፤**

- በቁልፍ ህገ መንግስትታዊ፣ ዓላማዎች፣ መርሆዎች፣ እሴቶች፣ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ስልቶችና ፕሮግራሞች እንዲሁም በሌሎች ወቅታዊ መሠረታዊ ጉዳዮች እና ክልላዊ አጀንዳዎች ዙሪያ የጋራ ብሄራዊ መግባባት መድረስን እንዲሁም ክልላዊ ገጽታችን በተመዘገቡና በሚመዘገቡ ስኬቶች መጠን መታወቁን በጥናት ያረጋግጣል፣
- የጥናትና የምርምር ስራዎች ውጤት ለመንግስት ከፍተኛ ሀላፊዎች ለተለያዩ ባለድርሻ አካላትና ለህዝብ ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል፣ ለግብአትነት መዋላቸውንም ያረጋግጣል፤

- የኮምዩኒኬሽን ምርምሮችና የህዝብ አስተያየት ጥናቶችን በዋና ዋና ክልላዊ ወይም ሰፊ ተደራሽነት ባላቸው የሃገር ውስጥና የውጭ ሚዲያዎች እንዲሰራጩ ያደርጋል፤ ዓውደ ጥናቶችና ምክክሮች ያካሂዳል፤ በክልላዊና በተለያዩ ዓለም አቀፍ ጆርናሎችም ታትመው ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
- መሠረታዊ በሆኑ የክልላችን ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ስራዎች ክፍተቶች ላይ ሙያዊና ፖለቲካዊ ጥናት ያካሂዳል፣ ይህንንም በማያቋርጥ ሂደት በየጊዜው በማከናወን ውጤታማነቱን ይገመግማል፤

- ቀልጣፋና ውጤታማ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ለማድረግ የመንግስት የኮሙኒኬሽን ፍላጎት(Government communication needs) እና የህዝቡ የኢንፎርሜሽን ፍላጎት(Public information needs) በጥናት ይለያል፣ የጥናቱን ውጤት በመገምገም ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለሀላፊው ያቀርባል፣
- ከውጭና ከአገር ውስጥ የጥናት-ምርምር ተቋማት የሚገኙ የጥናት ውጤቶች እንዲሁም በትምህርታዊ ጉብኝቶች የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችና ልምዶች እንዲቀመሩና እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ ውጤታማ የሚሆኑበትን ስልት በመንደፍ ያስገኙትን ውጤት ይገመግማል፤
- የኮሙኒኬሽንና የሚዲያ ምርምር እና የህዝብ አስተያየት ጥልቅ ጥናቶች ያካሂዳል፤ እንዲካሄዱም አመራር ይሰጣል፣ የተገኙ ውጤቶችን መሠረት በማድረግም የኮሙኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ በየወቅቱ በተለያዩ ቋንቋዎች የሚያስተገቧቸው ክልላዊ አጀንዳዎች እንዲቀረጹ የውሳኔ ሃሳብ ለኃላፊ ያቀርባል፣
- በሀገር ውስጥ ወይም በውጭ ሙያተኞች ጥልቅ ምርምር የሚሹ ጉዳዮችን በመለየት የጥናት- ምርምር ፕሮጀክት ምክረ ሃሳብ ያዘጋጃል፤ የፕሮጀክት ሰነዶችን ይገመግማል፣ እንዲጸድቁና ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣
- የክልላን ራዕይና የህዳሴውን ጉዞ እውን ለማድረግ በየወቅቱ የሚቀርጻቸው ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች፣ ስትራቴጂዎች፣ ስልቶች እንደግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ ክልላዊ የኮምዩኒኬሽን ምርምሮችና የህዝብ አስተያየት ጥናቶች ያካሂዳል፤ እንዲካሄዱ ያደርጋል፤ ለመንግስት ከፍተኛ አመራር አካላት ያቀርባል፤ ውጤቱንም ይገመግማል፤
- በልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ዝግጅትና ትግበራ ዙሪያ ህብረተሰቡ የተሟላ መረጃ እንዲኖራው የኮምዩኒኬሽን ምርምርና የህዝብ አስተያየት ጥናቶች የተቀመሩ ሰነዶችን የማህበራዊ ሚዲያ (social media) ጨምሮ በተለያዩ የኮምዩኒኬሽንና ሚድያ አውታሮች በተለያዩ ቋንቋዎች ወቅታዊና የደረጁ መረጃዎችን ለህዝቡ በማቅረብ ግልፅነት ይፈጥራል፤ በዓለም አቀፉ ህብረተሰብ ዘንድ ስለክልላችን ቀዳሚና የተሟላ የመረጃ ምንጭ መሆን የሚቻልበትን አቅም ይገነባል፤

**ውጤት 3:- በየወቅቱ ያለውን እድገት፣ ተጨባጭ ሁኔታ፣ አዳዲስ ፈጠራዎችንና አሰራሮችን መሰረት ያደረገ የፖሊሲ ምክረ-ሀሳብና የማማከር አገልግሎት መስጠት፡፡**

- ዓበይትና ወቅታዊ ክልላዊ ሁኔታዎች የሚገመገሙበት እንዲሁም ዓለማቀፍ ጉዳዮች የሚተነትኑበት፣ ከአገር ውስጥ እና ከውጭ ሃገር የምርምርና ጥናት ተቋማት ጋር በጋራ ልምድ የሚቀሰምበት፣ ፕላት ፎርም እና አሰራር እንዲኖርና ሁሉም በቅድመ - ዝግጅት የሚከናወኑበት አካሄድ እንዲበጅለት ይተልማል፤ አመራር በመስጠት ተግባራዊ ያደርጋል፤
- የባለድርሻ አካላት እንዲጎለብት መደበኛ የሥራ ግንኙነት ይፈጥራል፤ ተልዕኮን በጋራ ለመፈፀም የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ዘርግቶ ስኬታማ ተግባራት ያከናውናል፤
- የምክክር መድረክ በመፍጠር፣ ምርምርና ጥናት የሚሹ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን በመለየት ጉልህ ሚና ካላቸው

የምክር አገልግሎት ከሚሰጡ፣ የአሰራር ስርዓት ከሚዘረጉና ከሚገነቡ ተቋማት ጋር በጋራ ይሰራል፤

- የኮምዩኒኬሽንና ሚድያ ኢንዱስትሪው ከዩኒቨርሲቲዎችና ሌሎች የጥናት፣ ምርምር ተቋማት፣ የምክር ሰጪ ተቋማት ወዘተ/ ግንኙነት(leankage) የሚጠናከርበት ሥርዓት በአግባቡ እንዲዘረጋ በማድረግ ውጤታማ ተግባራት ያከናውናል፡፡
- የኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ ሳይንሳዊ በሆነ አግባብ ስትራቴጂክ አመራር ለመስጠት የሚያስችል የኮሙኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ የጥናትና ምርምር የልህቀት ማዕከል ያደራጃል፣ በውጤታማነት ይመራል፤
- የመንግስት ተልዕኮን የሚያሳካ የጥናት፣ የምርምር እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ተቋማት ዓይነትና ተልዕኮ እንዲሁም ትስስር ምን መሆን እንዳለበት የውጭ አገር ልምድ ይቀምራል፣ ምርጥ ተሞክሮው እንዲስፋፋ ያደርጋል፤
- ለፖሊሲ አውጭዎች ጠቃሚ የሆኑ ግብአቶች ለመስጠት የተቋቃሙ የሃገር ውስጥና የውጭ የግል ተቋማትና ታዋቂ ምሁራን ጋር ትስስር ይፈጥራል፤ ከውጭ አገር የመንግስት አካላት እና ከጥናትና ምርምር ተቋማት ጋር የምርጥ ተሞክሮች ልውውጥ እንዲካሄድ ያደርጋል፤
- የተቀረጹና የጸደቁ የአሠራር ሰነዶች /መመሪያ፣ ማንዋል፣ ጋይድላን ወዘተ/ ጥራታቸው የሚፈተሽበት ሥርዓት ተግባራዊ በማድረግ ወደ ተግባር የሚሸጋገሩበትን ዘዴዎች ያመቻቻል፣ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፣

## III. የሥራው ባህሪ መግለጫዎች፤

### 3.2 የሥራ ውስብስብነት

- ስራው ክልላዊ የኮሙዩኒኬሽን ጥናትና ምርምር ስራዎች የሚመራበትን እቅድ አዘጋጅቶ ማከፋፈል፤ ማስተባበር፣ ተፈጻሚነቱን መከታተል፣ ውጤቱንም መገምገም፣ የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በአፈፃፀም ወቅት የሚያጋጥማቸውን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ ጥናትና ምርምሮችን ማካሄድ፤ በምርምር በትንተና እና በስርጸት ብቃትና ብስለት ያላቸው ሳይንሳዊና ዘመን ተሻጋሪ ሃሳቦችን ማፍለቅ፤ በሃይማኖቶች እኩልነትና የሴኩላሪዝም መርሆዎች ዙሪያ፣ በመቻቻልና የጋራ እሴቶች የማጠናከር ጉዳይ እንዲሁም አክራሪነትና ፅንፈኝነት በመድፈቅ ዙሪያ በመላው ህዝብ ዘንድ ብሔራዊ መግባባት እንዲፈጠር ሁሉን አቀፍ፣ ተከታታይ፣ የተቀናጀና ወጥነት ያለው ሰፊ ምርምር ማካሄድ፤ ከክልሉ ፕሬዝደንት መግለጫዎችና ንግግሮች ሲቀርቡ የሕዝብ አስተያየቶችን በማሰባሰብና አያይዞ በመተንተን ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመንግስት ከፍተኛ ኃላፊዎች መስጠት፣ ለግብዓትነት መዋላቸውንም ማረጋገጥ፤ በሚዲያና ሞኒተሪንግ ውጤቶች ላይ የአዝማሚያ ትንተና እንዲካሄድ በማድረግ በህዝቡ ዘንድ የተፈጠሩ አዎንታዊና አሉታዊ አስተሳሰቦች እንዲሁም የዓለም ማህበረሰብ ያለውን አተያይ ማሳወቅ፤ ምርምርና ጥናት የሚሹ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን መለየትና ማካሄድ እንዲሁም የምክር አገልግሎት መስጠት፤ ጥናትና ምርምር የሚደረግባቸውንና ትኩረት የሚሹ ርዕሰ ጉዳዮችን በመለየት ሥራው የሚመራበትን ዝክረ ተግባር እንዲዘጋጅና ወደ ሥራ እንዲገባ ማድረግ፣ ተግባራዊነቱንም መከታተል፣ የኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ ሳይንሳዊ በሆነ አግባብ ስትራቴጂክ አመራር ለመስጠት የሚያስችል የኮሙኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ጥናትና ምርምር የልህቀት ማዕከል ለማደራጀት የሚያስችል አዳዲስ አሰራሮችን መዘርጋት፣ የኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ አሠራር በውጤታማነት

ተፈጻሚ እንዲሆን የሚያስችሉ አዳዲስ ሃሳቦችን በማፍለቅ ከማብራሪያ ጋር ማቅረብ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ለማድረግ የመንግስት የኮሙኒኬሽን ፍላጎትና የህዝቡ የኢንፎርሜሽን ፍላጎት በጥናት እንዲለዩ ማድረግ፣ የጥናቱን ውጤት ከውሳኔ ኃሳብ ጋር ለኃላፊው ማቅረብ፤ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን፣ መስፈርቶችና መርሃግብሮችን አዘጋጅቶ የማጸደቅ፣ ተግባር ላይ እንዲውሉም ማድረግ፣ አፈጻጸሙንም መከታተል፣ የኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍን ውጤታማ ለማድረግ የተዘጋጁ የጥናትና ምርምር ፕሮጀክት ሰነዶችን በማዘጋጀትና ወደ ተግባር በማሸጋገር ውጤታማነቱን እየተከታተለ ለኃላፊው ማቅረብ፣ የምርምር ውጤቶች እንዲሁም የህዝብ አስተያየት ጥናቶች የክልላችን ራዕይና ህዳሴ እውን ለማድረግ መንግስት የሚቀርጻቸው ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ስልቶች እንደግብዓት ሆነው በሚያገለግል አግባብ እንዲጠና ማድረግ፤ የሁለትዮሽ የስምምነት ሰነድ ማዘጋጀት፣ በስራው ላይ ዕውቀት እንዲጨብጡ ማድረግና የተግባር ስምሪት መስጠት ሲሆን

- በክንውን ወቅት ክልላዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚው ለውጥ በሚፈለገው ደረጃ የጋራ አገራዊ አስተሳሰብ አለመፍጠር፣ በጎ ገፅታ አለመገንባት፣ በየወቅቱ ያለውን እድገት እና ተጨባጭ ሁኔታ አለመገንዘብ፤ የክልል የመንግስት አመራር አካላት ፈጣንና ወቅታዊ ውሳኔ አለመስጠት፤ በተሰጠው የጋራ አመራርና ስምሪት የባለድርሻ አካላት ተቀናጅተው አለመስራት፤ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እንዲሁም ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ተቋማት በትብብር ለመስራት ፍላጎት አለማሳየትና በቂ ድጋፍ አለመስጠት፤ መንግስት የሚያስቀምጣቸው አቅጣጫዎችና የሚያወርዳቸው አሰራሮች አስመልክቶ የጋራ አረዳድ አለመኖር፤ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ተልዕኳቸውን በህዝባዊ ኃላፊነት አለመወጣት፤ የጥናትና ምርምር ተቋማት በቅንጅት ለመስራት ፈቃደኛ አለመሆን፣ ህዝቡ የሚፈልገውን ኢንፎርሜሽንና ሃሳቡን በግልፅ አለማሳወቅ፣ የጥናትና ምርምር ሰነዶች፣ የፕሮጀክት ሰነዶች፣ መመሪያዎች፣ ማንዋሎችና ስታንዳርዶች የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው አለመዘጋጀት፣ አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶች ቶሎ ተቀባይነት አለማግኘት የሚያጋጥሙ ችግሮች ናቸው፡፡
- እነዚህም ችግሮች የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በአፈፃፀም የሚያጋጥማቸውን ችግሮች በጥናት ላይ ተመስርቶ በመፍታት፤ የመፍትሔ ሃሳብ በማመንጨት፤ በየወቅቱ ያለውን እድገት እና ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ አዳዲስ ሀሳቦችን በማቅረብ፤ በሃይማኖቶች እኩልናትና የሴኩላሪዝም መርሆዎች ዙሪያ፣ በመቻቻልና የጋራ እሴቶች በማጠናከር፤ አክራሪነትና ፅንፈኝነት በመድፈቅ ዙሪያ በመላው ህዝብ ዘንድ ብሔራዊ መግባባት በመፍጠር፤ የሕዝብ አስተያየቶችን በማሰባሰብና በመተንተን ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመንግስት ከፍተኛ ኃላፊዎች በመስጠት፣ በህዝቡ ዘንድ የተፈጠሩ አዎንታዊና አሉታዊ አስተሳሰቦች እንዲሁም የዓለም ማህበረሰብ ያለውን አተያይ በማሳወቅ፤ ምርምርና ጥናት የሚሹ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን በመለየት፤ የምክር አገልግሎት በመስጠት፤ ተራማጅ አስተሳሰብ ያላቸው ዜጐች በማፍራት፤ መልካም ገፅታ ለመገንባት የሚያስችሉ የጥናትና ምርምር ተግባራትን በሚዲያና ኮሙኒኬሽን አግባብ በመፈጸምና በማጎልበት፤ የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት የማያቋርጥ የግንዛቤ ስራ በመስራት፣ በአለም ላይ ያለውን ተጨባጭ እውነታ ከክልሉ የዕድገት ደረጃ ጋር

የተጣጣመ ምርምርና ጥናት እንዲካሄድ በማድረግ፣ የተሟላ መረጃ እንዲይዙ ተገቢውን ጥረት በማድረግ፣ ከአሳማኝ መረጃ ጋር በማቅረብና አስፈላጊውን ማብራሪያ በማቅረብ፣ የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሞ የህብረተሰቡን ሀሳብ በማግኘት፣ የአደረጃጀቶችን ባህሪይ ታሳቢ ባደረገ መልኩ የዳሰሳ ጥናቱ እንዲካሄድ አቅጣጫ በመስጠት፣ የፕሮጀክት ሰነዶችና የአሰራር ስርአት ሰነዶች ጥራታቸው የሚፈተሸበት ሥርዓት ተግባራዊ እንዲሆን በማድረግ፣ የቅርብ የክትትል፣የድጋፍ፣የመግባባትና የማሳመን ስራ በመራስት የሚፈቱ ናቸው፡፡

## 3.2 ራስን ችሎ መስራት

### 3.3.1 ሥራው የሚከናወንበት አግባብ

- ሥራው ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ አዋጆችን፣ ደንቦችን፣ ስትራቴጂካዊና ታክቲካዊ ዕቅዶችን፣ አለም ዓቀፍ ተቀባይነት ያላቸው የስልጠናና ትምህርት ስታንዳርዶች እና መለኪያዎች፣ መመሪያዎች፣ ፕሮግራሞች፣ መርሆች፣ ንድፈ-ሐሳቦች፣ አለም ዓቀፍ ኮንቬንሽኖች፣ የፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ሰነዶች፣ ከሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር የተፈጸሙ የሁለትዮሽና የባለብዙ ስምምነት ሰነዶች መሠረት በማድረግ ይከናወናል፡፡

### 3.1.2. ሥራው የሚጠይቀው የክትትልና ድጋፍ ደረጃ

- ሥራው የጥራት ደረጃውን ጠብቆ ተፈላጊውን ግብ ያሳካ ከመሆኑና፣ ካስገኘው ለውጥ አንጻር ስለመከናወኑ አጠቃላይ ግምገማ ይደረግበታል፡፡

## 3.4 ተጠያቂነት

### 3.3.3 ተጠያቂነት ለሥራ ውጤት /Responsibility for Impact/፣

- ሥራው በየወቅቱ ያለውን እድገት፣ ተጨባጭ ሁኔታና አዳዲስ ፈጠራዎችን መሰረት ያደረገ የፖሊሲ ምክረ-ሀሳብና የማማከር አገልግሎት ባይሰጥ፡፡ ንድፈ-ሐሳቦች፣ ፕሮግራሞችና መርሆች ተነድፈው ባይተገበሩ፣ በምርምር በትንተና እና በስርጸት ብቃትና ብስለት ያላቸው ሳይንሳዊና ዘመን ተሻጋሪ ሃሳቦች ከመንግስታዊ፣ መንግስታዊ ካልሆኑ የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እንዲሁም ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ተቋሞች ጋር የትብብር ግንኙነት ባይመሰረትና ድጋፍ ባይደረግ፤ መንግስት የሚያስቀምጣቸው አቅጣጫዎች፣ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አስመልክቶ የጋራ አረዳድ ባይፈጠር፤ ክልላዊ የኮምዩኒኬሽንና ኢንፎርሜሽን የልህቀት ማዕከል አቋቁሞ ጥልቀትና ብስለት ያለው የኮሙዩኒኬሽንና ሚዲያ ጥናት-ምርምር እንዲሁም ከውጭ አገርና ከአገር ውስጥ የምርምር ተቋማትና የከፍተኛ የትምህርት ጋር ግንኙነት ባይፈጠር፤ የትብብር ምርምሮችን ለማካሄድ ስትራቴጂ ባይነድፍ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ለማድረግ የመንግስት የኮሙኒኬሽን ፍላጎትና የህዝቡ የኢንፎርሜሽን ፍላጎት በጥናት እንዲለዩ ባያደርግና የጥናቱን ውጤት ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለመንግሥት ባያቀርብ፣ ፕሮግራሞች፣ የአሰራር ስርአት ሰነዶችን ገምግሞ እንዲጸድቁና ተግባራዊ እንዲሆን ባያደርግ፣ ከውጭና ከአገር ውስጥ በጥናትና ምርምር ስራዎች የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችና ልምዶች እንዲቀመሩና እንዲስፋፉ ባያደርግና ውጤታማ የሚሆኑበትን ስልት በመንደፍ ያስገኙትን ውጤት ባይገመግም፣

የኮሙኒኬሽን ምርምርና የህዝብ አስተያየት ጥናቶች፣የኮምዩኒኬሽንና የሚድያ ሞኒተሪንግ ውጤቶች የአዝማሚያ ጥናቶች እንዲካሄዱ ባያደርግና ውጤትን መሠረት በማድረግ አጀንዳ እንዲቀረፅ የውሳኔ ሃሳብ ለኃላፊው ባያቀርብ፣ በአገር ውስጥ ወይም በውጭ ሙያተኞች ጥልቅ ምርምር የሚሹ ጉዳዮችን በመለየት የጥናት-ምርምርና አቅም ግንባታ የፕሮጀክት ሰነዶችን ገምግሞ እንዲጸድቁና፣ ተግባራዊ እንዲሆኑ ባያደርግ፣ የጥናትና የምርምር ስራዎች ውጤት ለከፍተኛ የመንግስት፣ ለተለያዩ ባለድርሻ አካላትና ለህዝብ ተደራሽ እንዲሆን ባያደርግ፣ ፕሮግራሞች፣ መርሆች፣ ንድፈ-ሐሳቦች ባይነደፉ አፈጻጸሙንም ባይከታተል ወይም እነዚህ ተግባራት የጥራት ደረጃውን ጠብቀው ባይከናወኑ ወይም በክንውን ወቅት የሚፈጸሙ ስህተቶች በወቅቱ ባይታረሙ በመረጃ የበለፀገና በክልሉ ጉዳይ ንቁ ተሳትፎ የሚያደርግ ኅብረተሰብ እንዳይገነባ ያደርጋል፣ የዘርፉ እንቀሳቃሾች ጥቅምና የፈጠራ ተነሳሽነትን ያዳክማል፣ መንግሥት ለሕዝብ ጥያቄዎች ፈጣን ምላሽ ለመስጠት ያለውን ብቃትም ያዳክማል፡፡ ይህም ህዝቡ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ በፍትሃዊነት ተጠቃሚ ስለማይሆን ለልማት፣ ለዲሞክራሲና ለሰላም የሚኖረው ተሳትፎ ሊዳከም ይችላል፤ ህዝቡና ዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ በመካሄድ ላይ ባለው ለውጥ እየተፈጠረ ያለውን አዲስ እውነታ በትክክል እንዳይገነዘብ ያደርጋል፤ በክልሉ ያለውን በጎ አመለካከትም ሊሸረሸር ይችላል፣ ይህም በተቋሙ ገጽታ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይፈጥራል፡፡

3.3.4 **ተጠያቂነት ለሚስጥራዊ መረጃ፣**

- ስራው የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነጻነትን ለመደንገግ በወጣ አዋጅ ቁጥር 590/2000 ዓ/ም በአንቀጽ 38 በንኡስ አንቀጽ 2 ላይ እንደተገለጸው፤ ማንኛውም የመንግስት አካል በእጁ የሚገኙ ሰነዶችን የመጠበቅ ግዴታ አለበት ይላል፡፡ እነዚህ ሚስጥራዊ መረጃዎች ማለትም የፖሊሲ ለውጥ የማድረግ ወይም ያለማድረግ ውጥንን፣ የውሳኔ አሰጣጥን ወይም የፖሊሲ ቀረጻን ለማገዝ የቀረቡ ወይም የተዘጋጁ አስተያየቶችና የውሳኔ ሃሳቦች እንዲሁም ህዝብና መንግስት በአስቸኳይ ሊያውቃቸው የሚገቡ መረጃዎችን፣ በሚመለከተው አካል ውሳኔ አግኝተው ይፋ ከመደረጋቸው አስቀድሞ በሚስጥር ካልተያዙ፣ በተለይም ግጭትን ወይም ቀውስን አስመልክቶ የሚካሄዱ ጥናትና ምርምሮች እንዲሁም የህዝብ አስተያየቶችና በርካታ ምስጢራዊ መረጃዎች ግንዛቤ ተይዞባቸውና ተለይተው በጥንቃቄ ጥቅም ላይ ካልዋሉና ካልተያዙ ወይም የመረጃው ባለቤት የሆነ ከፍተኛ የመንግስት አካል መረጃው እንዲገለጽ በጽሁፍ ካልፈቀደ ወይም ለሌላ አካል ተላልፈው ከተሰጡና ከባከኑ ላልተፈለጉና ጉዳት ለሚያደርሱ ዓላማዎች ይውላሉ፤ ይህም በተቋሙ ላይ ተአማኒነትን ያሳጣል፡፡

**3.4 ፈጠራ**

- ስራው በምርምር በትንተና እና በስርጸት ብቃትና ብስለት ያላቸው ሳይንሳዊና ዘመን ተሻጋሪ ሃሳቦችን መፍጠርን ወይም ማፍለቅን፣ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታን መረዳት፣ የብሔራዊ ፖሊሲዎች እና እስትራቴጂዎችን ጥንካሬና ክፍተት በመለየት የመፍትሔ ሃሳቦችን መቀመርና ለሚመለከታቸው አካላት የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብን፣ በየወቅቱ ያለውን ተለዋዋጭ ዓለማዊ፣ ከባቢያዊና ሃገራዊ ሁኔታና እድገት፣ በመገንዘብና አዳዲስ ፈጠራዎችን መሰረት ያደረገ የፖሊሲ ምክረ-ሀሳብ ማመንጨትን፡፡ ክልላዊ የኮሙኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ የጥናት ምርምር ፕሮጀክቶች መቀረጽን፤ ጥልቅና ምጥቀት ባላቸው የጥናትና ምርምር ስራዎች ላይ የተመሰረተ

አዳዲስና አስተማማኝ ሁሉን አቀፍ ዘዴዎችን በመዘርጋት አሰራር ማሻሻልን፣ የህዝብንና የክልሉን ችግሮች ሳይንሳዊና ዘመናዊ በሆነ የኮምዩኒኬሽን ምርምርና በህዝብ አስተያየት አመራር ጥበብ መፍታትን፣ ፕሮግራሞችንና መርሆችን መንደፍን፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ማስረጽና ማስፋፋትን ይጠይቃል፡፡

### 3.5. የሥራ ግንኙነት /Work Communication/

#### 3.5.1 የግንኙነት ደረጃ

- ከውስጥ ከዳይሬክተር ኃላፊው፣ ከቡድን መሪዎች፣ ከሌሎች ዳይሬክቶሬቶች እንዲሁም ከውጭ ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣናት፣ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት፣ በሀገር ውስጥ ካሉ የተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ነው፡፡ ከክልል ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት፣ ከሀገር ውስጥና ከዓለም አቀፍ ኮሙኒኬሽንና ሚዲያ ተቋማት፣ ከከፍተኛ የምርምር ተቋማት ኃላፊዎች፣ ከፌደራል ኮሙዩኒኬሽን ተቋማት የሙያና ህዝባዊ ማህበራት እንዲሁም የተለያዩ አደረጃጀት ኃላፊዎች፣ ከተለያዩ የህዝብ ክንፍ አመራር አካላት፣ ከክልላዊ የኮሙዩኒኬሽንና ሚዲያ ኮሚቴ አባላት፣ ቦርድ አካላትና ከሚመለከታቸው አደረጃጀቶች ጋር በተከታታይ ግንኙነት ማድረግን ይጠይቃል፡፡

#### 3.5.2 የግንኙነቱ ዓላማ

- ከዘርፍ ኃላፊው ዳይሬክተሩ ተወያይቶ መግባባት በመድረስ የአመራር አቅጣጫና የስራ መመሪያ ለመቀበል፣ ለመስጠት፣ ሪፖርት ለማቅረብና ስራዎችንና ፕሮጀክቶችን ለመገምገም፣ የማማከር አገልግሎት ለመስጠት፣ በጋራ ለመስራት፣ ግብረ-መልስ ለመስጠትና ለመቀበል፣ ከወቅታዊና ዋናዋና ክልላዊ ጉዳዮችን እንዲሁም ከመንግስት የትኩረት አቅጣጫዎች ጋር የሚናበቡ የኮምዩኒኬሽን ምርምር እና የህዝብ አስተያየት የጥናት ርዕሶችን ለመምረጥ፣ በትብብር የጥናት ስራዎችን ለማካሄድ፣ አውደ ጥናት ለማካሄድ፣ የሐሳብና የልምድ ልውውጥ ለማድረግ፣ የጥናት ውጤቶችን ሰፊ ተደራሽነት ባላቸው ሚዲያዎች ተደራሽ ማድረግ፣ በጥናት በተመላከቱ ዋና ዋና ግኝቶች ላይ ስምምነት ለመድረስ፣ የህዝብንና የክልሉን ችግሮች ሳይንሳዊና ዘመናዊ በሆነ የምርምርና የንድፈ ሃሳባዊ የአመራር ጥበብ በመጠቀም ለህዝብ ጥያቄ ቅድሚያ በመስጠት ለመፍታት ብሎም የህዝብና የክልሉን ጥቅምን ለማስከበር፣ በህዝብ አስተያየት ጥናት ውስጥ የተለያዩ ፍላጐቶች ወይም ግልጽ ያልሆኑ አስተያየቶች ሊዳሰሱ ስለሚችሉ ጥንቃቄ የተሞላበት ማብራሪያ ለመስጠት፣ ለመደራደርና ለመወያየት፣ ምርጥ ተሞክሮን ቀምሮ ለማስረጽና ተግባራዊ ለማድረግ ነው፡፡

#### 3.5.3 የግንኙነቱ ድግግሞሽ

- ከቀን የስራ ጊዜው 70 በመቶ ይሆናል፡፡

### 3.6 ኃላፊነት

#### 3.6.1 ኃላፊነት ለሰው ሀብት

3.6.1.1 **በኃላፊነት የሚመራቸው ሠራተኞች ብዛት**

- 17 ባለሙያዎችን በቀጥታ የመምራት ኃላፊነት አለበት፡፡

3.6.1.2 **የኃላፊነት አይነትና ደረጃ**

- በዘርፉና በቢሮው የሚከናወኑ የኮምዩኒኬሽን ምርምርና የህዝብ አስተያየት ጥናቶች በተመለከተ ሃሣብ የማፍለቅ፣ ለመስኩ የሚያገለግል ስትራቴጂክ /የረዥም፣ የመካከለኛ ዘመንና አጭር/ እንዲሁም የኦፕሬሽናል/ዓመታዊ/ ዕቅዶችን ካስኬድ አድርጎ በጥብቅ ዲሲፕሊን የመምራት፡፡ ከፍተኛ የጥናትና የምርምር ተግባር የሚያከናውኑ ባለሙያዎችን የመምራት፣ የምርምር ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች የመንደፍ፣ የመተግበር፣ የመደገፍ፣ አፈፃፀማቸውን የመከታተልና የመገምገም፣ የማስተባበርና የማብቃት ሃላፊነት አለበት፡፡

3.6.2 **ኃላፊነት ለንዋይ**

- የለበትም፡፡

3.6.3 **ኃላፊነት ለንብረት**

- ለሥራ ማከናወኛ የሚሆን ዲጂታል ካሜራና መቅረጸ ድምጽ፣ ፕሮጀክት ስላይድ፣ ሪከርዲንግ፣ ዲጂታል ስልክ ወይም የእጅ ስልክ፣ ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ ሼልፍ፣ ዴስክቶፕ ኮምፒውተር፣ ከለር ፕሪንተር፣ ላፕቶት፣ ስካነር፣ ፋክስ፣ የእንግዳ መቀበያ ወንበሮች፣ ዲጂታል ቴሌቪዥንና ሬድዮ በግምት እስከ ብር 200 ሺህ ብር የሚደርስ ንብረት የመያዝና የመጠቀም ኃላፊነት አለበት፡፡

3.7. **ጥረት**

3.7.1 **የአዕምሮ ጥረት**

- የጥናትና ምርምር ውጤቶችን በመገምገም ግብረመልስ መስጠት፣ ለመንግስት አመራር አካላት የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ፣ የተቀናጀ አመራርና የጋራ ስምሪት መስጠትና አፈጻጸሙን መገምገም፤ የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እንዲሁም ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው የምርምር እንዲሁም መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋሞች ጋር የትብብር ግንኙነት መመስረት፤ የአሰራር ስርአቶችን መዘርጋትንና ድጋፍ ማድረግ፤ መንግስት የሚያስቀምጣቸው አቅጣጫዎች፣ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አስመልክቶ የጋራ አረዳድ እንዲኖር ማድረግ፤ የዘርፉን ስራ የሚያከናውኑ ተቋማት የራሳቸውን የምርምርና ስርፀት ስራ በብቃት እንዲያከናውኑ ማቀድንና ተፈጻሚነታቸውን መከታተል፣ የትብብር ምርምሮች እንዳካሄዱ ማድረግና ሂደቱን በበላይነት መምራት፣ የመንግስት የኮሙኒኬሽን ፍላጎት(Government communication needs) እና የህዝቡ የኢንፎርሜሽን

ፍላጎት(Public information needs) በጥናት እንዲለዩ ማድረግንና የጥናቱን ውጤት ከውሳኔ ኃሳብ ጋር አቅርቦ ማፀደቅ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፤ ከውጭና ከአገር ውስጥ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችና ልምዶች እንዲቀመሩና እንዲስፋፉ ማድረግና ውጤታማ የሚሆኑበትን ስልት በመንደፍ ያስገኙትን ውጤት መገምገም፤ ዘርፉን ውጤታማ ለማድረግ የተዘጋጁ የጥናት- ምርምና አቅም ግንባታ የፕሮጀክት ሰነዶችን በመገምገም እንዲጸድቁና ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ፣ የዘርፉን የጥናት-ምርምር ስራዎችን ውጤታማ የሚያደርጉ አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶች መዘርጋትንና ተፈፃሚነታቸውን መከታተል፣ በጥናት- ምርምር ዙሪያ የተለያዩ መድረኮችን አዘጋጅቶ ባለድርሻ አካላትንና ምሁራንን ማወያየት፣ የማማከር አገልግሎት መስጠት፣ በምርምር በትንተና እና በስርጸት ብቃትና ብስለት ያላቸው ሳይንሳዊና ዘመን ተሻጋሪ ሃሳቦችን ማፍለቅ፣ በየወቅቱ ያለውን እድገት፣ ተጨባጭ ሁኔታና አዳዲስ ፈጠራዎችን መሰረት ያደረገ የፖሊሲ ምክረ-ሀሳብ ማመንጨት፣ ጥልቅና ምጥቀት ባላቸው የጥናትና ምርምር ስራዎች ላይ የተመሰረተ አዳዲስና አስተማማኝ ሁሉን አቀፍ ዘዴዎችን በመዘርጋት አሰራር ማሻሻል፤ ፕሮግራሞችንና መርሆችን መንደፍ፣ ተልዕኮን በአግባቡ መረዳትና ማሳካት፣ ፕሮግራም መተንተን፣ የአመለካከት ስህተቶችን ወይም ዝንፈቶችን ማጣራት፣ ጥናታዊ ትንተናዎችን ማጠቃለል፣ የመፍትሔ ሐሳቦችን ለማግኘት የሚደረጉ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችል ጥልቀትና ብቃት ያለው ሃሣብ ለማመንጨት ከፍተኛ የሆነ የአዕምሮ ጥረትን የሚጠይቅ ሲሆን፣ ይህም ከቀን የስራ ጊዜው እስከ 70 በመቶ ይሆናል፡፡

### 3.7.2.ስነልቦናዊ ጥረት

- የጥናትና ምርምር ውጤቶችን መሰረት አድርጎ መንግስት የተሳሳተ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩና ስተቱን ለማረም መጋፈጥን የሚጠይቅ በመሆኑ፣ መንግሥት ከህዝብ አስተያየት ጥናት ውጤት ተነስቶ ለሕዝብ ጥያቄዎች አስቸኳይና ፈጣን ምላሽ መስጠት ያለበት ሁኔታ መኖሩና ውጥረት በተሞላበት መስራትን የሚጠይቅ በመሆኑ፤ በተለይ ክልላዊ አውደ ጥናቶች በሚካሄዱበት ወቅት ከተሳታፊዎች የተዛቡ፣ አፍራሽ እና አደገኛ አስተሳሰቦች የሚቀርቡበት እና አስተሳሰቡን ለማስተካከል ሙግት የሚደረግበት በመሆኑ ይህንን ስራ በማከናወኑ ሂደት ጫና፣ ስሜታዊነት፣ ስም ማጥፋት፣ ዘለፋ፣ ዛቻና ማስፈራሪያ ሊደርስበት የሚችል በመሆኑ ይህንን ከህዝብና ከመንግስት የሚደርስ ስነ ልቦናዊ ተጽዕኖን ተቋቁሞ ስራን በትጋት፣ በትዕግስትና በቁርጠኝነት መምራትን ይጠይቃል፡፡

### 3.7.3 የዕይታ ጥረት፣

- በመሰረቱ የኮምዩኒኬሽን ምርምር፣ የህዝብ አስተያየት ጥናቶች የሚካሄዱት በተለዋዋጭና በመሠረታዊ ክልላዊና ወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ያላቸው አመለካከትና አተያይ ምን እንደሆነ በጥልቀት ለማወቅ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ሰፊ አድማስ፣ የጠለቀ ዕውቀት፣ ክህሎትና ብቃት ይጠይቃል፡፡ እንዲሁም የፕሮጀክት ሃሳቦችን ማፍለቅ፣ መገምገም፣ ከባለድርሻ አካላት መልካም ግንኙነት ፈጥሮ እልህ አስጨራሽ

ድርድር ማድረግን ይጠይቃል፡፡ እነዚህን በአግባቡ በመቀመርና በመምራት ክልላዊ አጀንዳ ለመቅረጽ የሚያስችሉ እንዲሁም ለፖሊሲ ግብዓት የሚሆኑ ጥልቀት ያላቸው የጥናትና የምርምር ሥራዎች መተንተን፣ ማኑዋሎችንና የምርምር ውጤቶችን በተከታታይ በኮምፒውተር መጻፍ፣ በጥልቀት ማንበብ፣ መተርጐም፣ ጥናታዊ ጽሁፎችንና የተቀረጹ ቪዲዮችን እንዲሁም በኦንላየን የተላኩ የህዝብ አስተያየቶችን ኤዲት ማድረግ፣ ተልዕኮን በአግባቡ መረዳትና ማሳካት፣ ፕሮግራም መተንተን፣ ጥንቃቄ የተሞላበት እርምት መስጠት፣ የዕይታ ጥረትን የሚጠይቅ ሲሆን ይህም ከሥራ ጊዜው 50 በመቶ ይሆናል፡፡

**3.7.4 የአካል ጥረት**

- ሥራው 70 መቶ በመቀመጥ፣ 30 በመቶ በመንቀሳቀስ ይከናወናል፡፡

**3.8. የሥራ ሁኔታ**

**3.8.1. ሥጋትና አደጋ**

- የለበትም፡፡

**3.8.2. የሥራ አካባቢ ሁኔታ**

- ሥራው በጤና ላይ ችግር በማያስከትል አካባቢ የሚከናወን ነው።

**3.9. እውቀትና ክህሎት**

**3.9.1. ትምህርት**

| የትምህርት ደረጃ | የትምህርት ዓይነት |
|---|---|
| የመጀመሪያ ዲግሪ | በኮሚዩኒኬሽንና ጋዜጠኛነት፣ ፖለቲካል ሳይንስና አለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቋንቋና ስነ-ጽሁፍ፣ ስራ አመራር፣ ሶሺዮሎጂ እና ሶሻል አንትሮፖሎጂ ታሪክ ቢዝነስ አድምንስትሬሽን፣ ኢኮኖሚክስ በመጀመሪያ ዲግሪ ከስራው ጋር ግንኙነት ያለው 6 ዓመትየሥራ ልምድ ያለው /ያላት/ መሠረታዊ የኮምፒዩውተር እውቀትያለው /ያላት/ |

**3.9.2 ሥራውን ለመጀመር የሚያስፈልግ የሥራ ልምድ**

| የሥራ ልምዱ ለማግኘት የሚጠይቀው ጊዜ | ልምዱ የሚገኝበት የሥራ ዓይነት |
|---|---|
| በመጀመሪያ ዲግሪ 6 ዓመት | በኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ጥናትና ምርምር የልህቀት ማዕከላትና ከስራው ጋር ተያያዠነት ያለው በጥናትና ምርምር የተገኘ ልምድ |

| የሥራ ትንተና ባለሙያ ሥም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| | | |

| የሥራ ዝርዝሩን ያጸደቀው የኃላፊው ሥም | የሥራ መደቡ መጠሪያ | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| | | | |

| የሥራ ዝርዝር መግለጫ ቅጽ | | |
|---|---|---|
| I. አጠቃላይ መግለጫ | | |
| **የመስሪያ ቤቱ ስም** | **የሥራ መደቡ መጠሪያ** | **የሥራ ዘርፍ/የሥራ ሂደት** |
| ሲ/ብ/ክ/መ/የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ | የኮሙኒኬሽን አቅም ግንባታ ባለሙያ IV | ህዝብ አስተያየት፣ ጥናትና የኮሙዩኒኬሽን አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት |
| | | |
| **የቅረብ ኃላፊ የሥራ መደብ /ተጠሪነት** | **የሥራው ደረጃ** | **የሥራው ኮድ** |
| ለኮሙዩኒኬሽን አቅም ግንባታ ቡድን መሪ | XIV | |
| | | |
| **መስሪያ ቤቱ የሚገኝበት ቦታ** | | |
| ሀዋሳ | | |
| **II. የሥራ መደቡ ዋና ዓላማ፣ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት** | | |

**2.1. የሥራ መደቡ ዓላማ፡-**

የኮሙኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ አቅም ለመገንባት የሚያስችሉ ጥናቶችን በማድረግ አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶች መዘርጋት፣ሞጅሎችን ማዘጋጀት ስልጠና ፕሮግራሞችን መቅረፅና ስልጠና መስጠት፣ የስልጠናዎችና ልምድ ልውውችን ውጤታማነት መገምገም፣ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ሥራውን ውጤታማ ማድረግ ነው፡፡

**2.2.ከሥራ መደቡ  የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት**

**ውጤት 1. የኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ አሰራሮችን መዘርጋትና ማሻሻል**

- የስራ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣
- የኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ አቅም ግንባታ የአሰራር ክፍተቶችን በጥናት ይለያል፣ የመፍትሄ ሀሳብ በማዘጋጀት ለኃላፊው ያቀርባል፣
- ጥናቶችን በማድረግ ውጤታማ የሆነ የኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ አደረጃጀቶችን ይዘረጋል፣ በየወቅቱም ያሻሽላል፣
- ጥናቶችን በማድረግ ውጤታማ የሆነ በኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ አዳዲስ አቅም ግንባታ የአሰራር ስርዓቶችን ይዘረጋል፣ በየወቅቱ ያሻሽላል፣

- የኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ የአቅም ግንባታ አሰራሮችን ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ መመሪያዎችን፣ ማንዋሎችንና፣ ስታንዳርዶችን ያዘጋጃል፣ በየወቅቱም ያሻሽላል፡፡
- የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት በተጠኑ ጥናቶች እና በተዘጋጁ ሰነዶችን ዙሪያ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና ምሁራን ግብዓት ይሰበስባል፣ በጥናቶቹና ሰነዶቹ ላይ ያካትታል፡፡
- የኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ አቅም ግንባታ አሰራሮችን በተመለከተ ከውጭና ከአገር ውስጥ ምርጥ ተሞክሮዎችን ይቀምራል፤ ያስፋፋል፡፡

**ውጤት 2. የትምህርትና ስልጠና ሞጁሎችና ማንዋሎችን ማዘጋጀት፣ ስልጠና መስጠት**

- የኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ የአቅም ክፍተቶችን በጥናት ይለያል፤የመፍትሄ ሃሳብ በማዘጋጀት ለሃላፊው ያቀርባል፡፡
- የአቅም ክፍተቶች የሚሞሉበትን የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞችን ይቀርፃል፤
- ከውጭና ከአገር ውስጥ የልምድ ልውውጥ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ፕሮፖዛሎችን ያዘጋጃል፤
- በኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ የአቅም ግንባታ ማዕከላት እንዲከፈቱ ጥናቶችን ያደርጋል፤ የአቅም ግንባታ ማዕከሉንም ያደራጃል፤
- ጥናቶችን በማድረግ አቅም ለመገንባት የሚያስችሉ ፕሮጀክቶችን ፕሮፖዛሎችን በመቅረፅ የውጭና የአገር ውስጥ የትምህርትና ስልጠና ዕድሎችን እንዲሁም ሃብት ያፈላልጋል፤
- ጥናቶችን በማድረግ በኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽና ሚዲያ ዘርፍ አቅም ለመገንባት የሚያስችሉ የስልጠና ሞጁሎችና ማንዋሎች ያዘጋጃል፣ በየወቅቱም ያሻሽላል፤
- በተዘጋጁ የአሰራር ስርዓቶች፣ ስታንዳርዶች፣ መመሪያዎች፣ ማንዋሎችና ሞጁሎች ላይ ለኮሙኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ አመራሮች፣ ባለሙያዎች እና ባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ይሰጣል፤
- የኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍን አቅም ለመገንባት የሚያስችሉ የተለያዩ ስልጠናዎችን ይሰጣል፤
- ታዋቂ ምሁራንና ግለሰቦች በመጋበዝ ስልጠና እንዲሰጡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
- አቅምን ለመገንባት የሚያግዙ የተለያዩ የማስተማሪያና የግንዛቤ ማስጨበጫ ጽሁፎችን በማዘጋጀት በዌብ ሳይት እንዲለቀቁ ያደርጋል፤
- አቅምን ለመገንባት የሚያግዙ የተለያዩ መረጃዎችን መጽሐፍትና ጽሁፎችን በማሰባሰብና በማደራጀት በዌብ ሳይት እንዲለቀቁ ያደርጋል፤
- የክልሉን የኮሙዩኒኬሽንና ሚዲያ የዕድገት ደረጃ ያደጉ ክልሎችና አገሮች ከደረሱበት የዕድገት ደረጃ ጋር በማነጻጸር የዘርፉ የአቅም ግንባታ ክፍተት ይለያል፣ ማሻሻያ የሚደረግባቸውን ነጥቦች በፕሮፖዛል መልክ አዘጋጅቶ ለኃላፊው ያቀርባል፣

**ውጤት 3. ክትትልና ድጋፍ ማድረግ**

- የኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ አሰራሮችን ውጤታማ ለማድረግ የተዘጋጁ አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶችን፣ መመሪያዎችን፣ ማንዋሎች፣ ስታንዳርዶች በአግባቡ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፤
- በኮሙኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ ለሚደረጉ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች እና ጥናቶች በተመለከተ ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል፤
- በኮሙኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ የተሰጡ ስልጠናዎች ያመጡትን ውጤትና ፋይዳ ያጠናል፤ ይገመግማል፤
- የኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ የተካሄዱ የልምድ ልውውጥ ፕሮግራሞች ያመጡትን ውጤትና ፋይዳ ይገመግማል፤
- የኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍን አቅም ለመገንባት የተቀመሩ የውጭና የአገር ውስጥ ምርጥ ተሞክሮዎች በአግባቡ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፤
- ወቅታዊ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት በማዘጋጀት ለኃላፊው ያቀርባል፡፡

**III. የሥራው ባህሪ መግለጫዎች**

**3.1 የሥራ ውስብስብነት**

- ሥራው የኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽና ሚዲያ ዘርፍ አቅም ክፍተቶችን በጥናት መለየትን፣ የአቅም ክፍተቶች የሚሞሉበትን የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞችን መቅረፅን፣ ጥናቶችን በማድረግ ውጤታማ የሆኑ አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶችን፣ አደረጃጀቶችን፣ መመሪያዎችን፣ ማንዋሎችና ስታንዳርዶችን ማዘጋጀትን፣ በየወቅቱም ማሻሻል እና ማስረፅን፣ ሞጁሎችንና ማንዋሎችን እንዲሁም የግንዛቤ ማስጨበጫ ጽሁፎችን ማዘጋጀትንና በየወቅቱም ማሻሻልን፣ ፕሮጀክቶችን ማዘጋጀትንና የውጭና የአገር ውስጥ የትምህርትና ስልጠና ዕድሎች እንዲሁም ሃብት ማፈላለግ፣ ስልጠና መስጠትን፣ የውጭና የአገር ውስጥ ምርጥ ተሞክሮዎችን መቀመርን፣ ማስፋፋትን፣ የስልጠናና የልምድ ልውውጥ ውጤትና ፋይዳ መከታተልና መገምገምን ፣ የአፈጻጸም ክትትልና ድጋፍ ማድረግን የሚጠይቅ ሲሆን፡-
- ሥራው በሚከናወንበት ወቅት የመረጃ ትንተና ጥራት መጓደል፣ የሚዘጋጁ አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶችን፣ አደረጃጀቶችን፣ መመሪያዎችን፣ ማንዋሎችና ስታንዳርዶችን በዘርፉ ባለሙያዎችና ባለድርሻ አካላት ተቀባይነት አለማግኘት፣ ከክልላችን ተጨባጭ የዕድገት ደረጃ ጋር ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ የአቅም ግንባታ ማዕከላት ምርጥ ተሞክሮዎች /benchmark/ መረጃ በቀላሉ ያለማግኘት፣ ሰልጣኞች በአግባቡ የሥልጠና ሂደት አለመከታተል፣ በሰልጣኞች መካከል ስልጠናውን የመቀበል ደረጃ የተለያየ መሆን፣ በአመለካከት ችግር ምክንያት የሚሰጡ ስልጠናዎችና ግንዛቤ ማስጨበጫዎች ተቀባይነት ማጣት፣ የተሰጡ ስልጠናዎችን ተግባራዊ አለማድረግ፣ ዝቅተኛ አፈጻጸም፣ በክንውን ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮች ወይም ፈታኝ ሁኔታዎች ሲሆኑ፡-
- እነዚህን ፈታኝ ሁኔታዎች /ችግሮች/ ለመፍታት  የተተነተኑ መረጃዎችን በጥልቀት በመፈተሽና በመመርመር

የተጓደሉ ትንተናዎችን በሚሟላት፣ ተከታታይ የሆኑ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን በመስጠት፣ የፕሮጀክቱን ዓላማ ፋይዳ በማስረዳት፣ በማግባባትና በማሳመን እንዲገነዘቡ በማድረግ እንዲሁም ቀጣይነትና ተከታታይነት ያለው ስልጠናዎችንና ድጋፎችን በመስጠት ይፈታሉ፡፡

### 3.2 ራስን ችሎ መስራት

#### 3.2.1 ሥራው የሚከናወንበት አግባብ

- ሥራው የመንግስት ፖሊሲና ስትራቴጂዎች፣ አዋጆችን፣ ደንቦችን፣ መመሪያዎች፣ ስታንዳርዶችና መሰረት በማድረግ የሚከናወን ይሆናል፡፡

#### 3.2.2.ሥራው የሚጠይቀው የክትትልና ድጋፍ ደረጃ

- የኮሙዩኒኬሽንና የሚዲያ ዘርፍ አቅም ግንባታ ስራዎችን ውጤታማ ከማድረግ አንጻር በመጨረሻ ግምገማ ይደረግበታል፡፡

### 3.3. ተጠያቂነት

#### 3.3.1 ተጠያቂነት ለሥራ ውጤት /Responsibility for Impact/፣

- ሥራው የኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽና ሚዲያ ዘርፍ አቅም ክፍተቶችን በጥናት መለየትን፣ የአቅም ክፍተቶች የሚሞሉበትን የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞችን መቅረፅን፣ ጥናቶችን በማድረግ ውጤታማ የሆኑ አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶችን፣ አደረጃጀቶችን፣ መመሪያዎችን፣ ማንዋሎችና ስታንዳርዶችን ማዘጋጀትን፣ በየወቅቱም ማሻሻል እና ማስረፅን፣ ሞጁሎችንና ማንዋሎችን እንዲሁም የግንዛቤ ማስጨበጫ ጽሁፎችን ማዘጋጀትንና በየወቅቱም ማሻሻልን፣ ፕሮጀክቶችን ማዘጋጀትንና የውጭና የአገር ውስጥ የትምህርትና ስልጠና ዕድሎች እንዲሁም ሃብት ማፈላለግ፣ ስልጠና መስጠትን፣ የውጭና የአገር ውስጥ ምርጥ ተሞክሮዎችን መቀመርን፣ ማስፋፋትን፣ የስልጠናና የልምድ ልውውጥ ውጤትና ፋይዳ መከታተልና መገምገምን ፣ የአፈጻጸም ክትትልና ድጋፍ ማድረግን የሚጠይቅ ሲሆን፡-
- ይህ በአግባቡ ባይከናወን፣ የኮሙኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ አመራሮች፣ ፈፃሚዎች እንዲሁም የባለድርሻ አካላት አቅም በወቅቱ እንዳይጎለብት ያደርጋል፤ የዘርፍ አካላት ከቡድኑ ማግኘት ያለባቸውን አገልግሎት እንዳያገኙ ያደርጋል፤ የአመለካከትና ክህሎት ክፍተቶች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፤ የዘርፉ ተልዕኮዎች የሆኑት ክልላዊ የጋራ መግባባት እና አዎንታዊ የገጽታ ግንባታ ተግባራት ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርጋል ይህም በተቋሙ ገጽታ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

#### 3.3.2.ተጠያቂነት ለሚስጥራዊ መረጃ፣

- ሚስጥራዊ መረጃ የለበትም፡፡

### 3.4. ፈጠራ

- ሥራው በኮሙኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶችና ስልቶችን፣ መመሪያዎችን፣ ማንዋሎችን፣ ሞጁሎችን ማዘጋጀትና በየወቅቱ ማሻሻልን፣ ይጠይቃል፤ ለስራ መሻሻል የሚያግዙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ማስፋፋትን ይጠይቃል፡፡

3.5. **የሥራ ግንኙነት** /Work Communication/

3.5.1 **የግንኙነት ደረጃ**

- **ከውስጥ** ከቅርብ ኃላፊው፣ ከስራ ክፍሉና ከሌሎች የስራ ክፍሎች፣ በዘርፉ ከሚገኙ የኮሙኒኬሽንና ሚዲያ አካላት፣
- **ከውጭ** በየተቋማቱ ያሉ የህዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች፣ ከትምህርት ተቋማት፣ ከለጋሽ ድርጅቶች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ግንኙነት ያደርጋል፡፡

3.5.2 **የግንኙነቱ ዓላማ**

- ከቅርብ ኃላፊው የስራ መመሪያ ለመቀበልና ሪፖርት ለማድረግ፣ የስራ አቅጣጫ ላይ ለመወያየት፣ በጋራ ለመስራት፣ አዳዲስ አሠራሮችን ተግባራዊ ለማድረግ፣ መረጃ ለመስጠትና ለመቀበል፣ ስልጠና ለመስጠት፣ የትምህርትና ስልጠና ዕድሎችን ለማግኘት፣ ሀብት ለማፈላለግ፣ ልምድ ለመቅሰም፣ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ግንኙነት ያደርጋል፡፡

3.5.3 **የግንኙነቱ ድግግሞሽ**

- የግንኙነት ድግግሞሽ ከስራ ጊዜው ውስጥ 40 በመቶ ያህል ይሆናል፡፡

3.6 **ኃላፊነት**

3.6.1 **ኃላፊነት ለሰው ሀብት**

3.6.1.1 **በሀላፊነት የሚመራቸው ሠራተኞች ብዛት**

- የለበትም ፡፡

3.6.1.2 **የኃላፊነት አይነትና ደረጃ**

- የለበትም ፡፡

3.6.2 **ኃላፊነት ለንዋይ /ገንዘብ/**

- የለበትም ፡፡

3.6.3 **ኃላፊነት ለንብረት**

- ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች ዋጋቸው እስከ 300,000 ሺህ ብር የሚገመት እንደ ዲስክ ቶፕ ኮምፒዩተር፣

ላፕቶፕ፣ ፕሪንተር፣ ከለር ፕሪንተር፣ ፋክስ ማሽን፣ ስካነር፣ ፕሮጀክተር፣ የፎቶ ካሜራ፣ ሳውንድ ሲስተም፣ ሞንታርቦ፣ ሼልፍ፣ ወንበርና ጠረጴዛና የተለያዩ መፅሀፍት በጥንቃቄ የመያዝና የመጠበቅ ሃላፊነት አለበት፡፡

**3.7. ጥረት**

**3.7.1 የአዕምሮ ጥረት**

- ሥራው የኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና የሚዲያ ዘርፍ ጥናቶችን በማድረግ ውጤታማ የሆኑ አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶችን፣ አደረጃጀቶችን፣ መመሪያዎችን፣ ማንዋሎችና ስታንዳርዶችን ማዘጋጀትንና በየወቅቱም ማሻሻልንና ማስረፅን፣ የትምህርትና የስልጠና ፕሮግራሞችን መቅረፅን፣ መመሪያዎች፣ ማንዋሎችና ሞጁሎችን እንዲሁም የግንዛቤ ማስጨበጫ ጽሁፎችን ማዘጋጀትንና በየወቅቱም ማሻሻልን፣ ፕሮጀክቶችን ማዘጋጀት፣ የውጭና የአገር ውስጥ የትምህርትና ስልጠና ዕድሎች እንዲሁም ሃብት ማፈላለግን፣ ስልጠና መስጠትን፣ የስልጠናና የልምድ ልውውጥ ውጤትና ፋይዳ መከታተል፣ መገምገምን፣ የውጭና የአገር ውስጥ ምርጥ ተሞክሮዎች መቀመርና ማስፋትን፣ የአፈጻጸም ክትትልና ድጋፍ ማድረግን የሚጠይቅ ሲሆን ይህም 70 በመቶ የአዕምሮ ጥረት ይጠይቃል፡፡

**3.7.2.ስነልቦናዊ ጥረት**

- የኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ የአፈጻጸም ክትትል በሚደረገበት ወቅት የተሰጡ ስልጠናዎች እንዲሁም የተዘረጉ አዳዲስ አሠራሮችን በአግባቡ ተግባራዊ መሆንና አለመሆናቸው አስመልክቶ በየተቋሙ ካሉ የኮሙኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና የሚዲያ ዘርፍ አካላት፣ እንዲሁም ስልጠና በሚሰጥበት ወቅት የአመለካከትና የግንዛቤ ችግር ያለባቸው ሰልጣኞች ጋር የስልጠናውን ሂደት ለማወክ በሚያደርጉት እንቅስቃሴዎች አላስፈላጊ ጭቅጭቆችና አለመግባበቶች የሚፈጠሩ ሲሆን ይህንን በትግስትና በቁርጠኝነት ተቋቁሞ ማከናወንን ይጠይቃል፡፡

**3.7.3 የዕይታ ጥረት፣**

- ሥራው የስልጠና ሰነዶችን፣ መመሪያዎችንና ስታንዳርዶችን፣ ሞጁሎችን በኮምፒውተር በመታገዝ ማዘጋጀትና በየጊዜው ማሻሻልን፣ የተለያዩ ወቅታዊ መረጃዎችን እንዲሁም በኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ በአቅም ግንባታ ዙሪያ ያሉ ምርጥ ተሞክሮዎችን በየጊዜው ከኢንተርኔትና ከተለያዩ ጽሁፎች ማሰባሰብና ማንበብና፣ የሚጠይቅ በመሆን በአጠቃላይ ከስራ ጊዜው 45 በመቶ ያህል ይሆናል፡፡

**3.7.4 የአካል ጥረት**

- ሥራው 75 በመቶ በመቀመጥ፣ 15 በመቶ በመቆም፣ 10 በመቶ በመንቀሳቀስ የሚከናወን ነው፡፡

**3.8. የሥራ አካባቢ**

**3.8.1. ሥጋትና አደጋ**

- የለበትም፡፡

3.8.2. የሥራ አከባቢ

- በምቹ የስራ አካባቢ ሁኔታ የሚከናወን ነው፡፡

3.9. እውቀትና ክህሎት፣

3.9.1. ትምህርት

| የትምህርት ደረጃ | የትምህርት አይነት |
|---|---|
| ዲግሪ | በኮሚዩኒኬሽንና ጋዜጠኛነት፣ ፖለቲካል ሳይንስና አለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቋንቋና ስነ-ጽሁፍ፣ ስራ አመራር፣ ሶሺዮሎጂ እና ሶሻል አንትሮፖሎጂ ታሪክ ቢዝነስ አድምንስትሬሽን፣ ኢኮኖሚክስ በመጀመሪያ ዲግሪ ከስራው ጋር ግንኙነት ያለው 6 ዓመትየሥራ ልምድ ያለው /ያላት/ መሠረታዊ የኮምፒዩውተር እውቀትያለው /ያላት/ |

3.9.2 ሥራውን ለመጀመር የሚያስፈልግ የሥራ ልምድ

| የሥራ ልምዱ ለማግኘት የሚጠይቀው ጊዜ | ልምዱ የሚገኝበት የሥራ ዓይነት |
|---|---|
| በመጀመሪያ ዲግሪ 6 ዓመት | በውጭና በሃገር ውስጥ የጥናት-ምርምርና የአቅም ግንባታ ተቋማት፣ በህዝብ ግንኙነት |

| የሥራ ትንተና ባለሙያ ሥም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| | | |

| የሥራ ዝርዝሩን ያጸደቀው የኃላፊው ሥም | የሥራ መደቡ መጠሪያ | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| | | | |

| የሥራ ዝርዝር መግለጫ ቅጽ | | |
|---|---|---|
| I. አጠቃላይ መግለጫ | | |
| **የመስሪያ ቤቱ ስም** | **የሥራ መደቡ መጠሪያ** | **የሥራ ዘርፍ** |
| ሲ/ብ/ክ/መ/የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ | የኮሙዩኒኬሽን አቅም ግንባታ ባለሙያ III | ህዝብ አስተያየት፣ ጥናትና የኮሙዩኒኬሽን አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት |
| | | |
| | | |
| **የቅርብ ኃላፊ የሥራ መደብ /ተጠሪነት** | **የሥራው ደረጃ** | **የሥራው ኮድ** |
| ለኮሙኒኬሽን አቅም ግንባታ ቡድን መሪ | XIII | |
| | | |
| **መስሪያ ቤቱ የሚገኝበት ቦታ** | | |
| ሀዋሳ | | |
| **II. የሥራ መደቡ ዋና ዓላማ፣ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት፤** | | |

2.1. **የሥራ መደቡ ዓላማ፡-**

- አዳዲስ መመሪያዎችንና ማንዋሎችን በማዘጋጀትና ነባሮችን በመከለስ፣ ሚዲያዎች ባስተላለፉት መልዕክቶች ላይ የአዝማሚያ ትንተና በማድረግ፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን ቀምሮ በማስፋትና ጥናትና ምርምር በማካሄድ የኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ሥራን ውጤታማ ማድረግ ነው፡፡

2.2. **ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት**

**ውጤት 1፡- የአሠራር ሥርዓቱን የሚያግዙ አዲስ መመሪያዎችንና ማንዋሎችን ማዘጋጀትና ነባሮችን መከለስ**

- በኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ ሳይንሳዊ በሆነ አግባብ ስትራቴጂክ አመራር ለመስጠት የሚያስችል የጥናትና ምርምር ለማጠናከር የሚያስችል አሰራር ለመዘርጋት የተተነተኑ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ ረቂቅ ሰነዶችን ያዘጋጃል፣
- በየኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ የጥናትና ምርምር ሥራዎች የሚመሩበትን የአሠራር መመሪያዎችንና ማንዋሎችን ያዘጋጃል፣

- ተከልሰው እንዲዘጋጁ ውሳኔ የተሰጠባቸውን ነባር የአሠራር መመሪያዎችና ማንዋሎችን ከልሶ በማዘጋጀት ለቡድኑ ያቀርባል፣

- ለሥራ ቅልጥፍና የሚረዱ ስታዳርዶችን አዘጋጅቶ ለቡድኑ ያቀርባል፣
- የኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ አሠራር በውጤታማነት ተፈጻሚ እንዲሆን የሚያስችሉ አዳዲስ የጥናትና ምርምር ሃሳቦችን ያቀርባል፡፡

**ውጤት 2፡- የሀገር ውስጥና የውጭ ሚዲያዎች ባስተላለፉት መልዕክቶች ላይ የአዝማሚያ ትንተና ማካሄድ**

- የሀገር ውስጥና የውጭ ሚዲያዎች በክልሉ፤ እየተገነባ ያለውን የልማታዊ የዲሞክራሲ ሥርዓት አስመልክተው በአዎንታም ሆነ በአሉታ በሚያስተላልፉት መልዕክቶች ይዘት ላይ የተካሄዱ የሞኒተሪንግና የሚዲያ ውጤቶች ላይ አዝማሚያ ለመተንተን የሚያስችሉ የትኩረት ነጥቦችን ለይቶ ያወጣል፣ ያስወሰናል፣
- በህትመትና ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ውጤቶች በአዎንታም ሆነ በአሉታ በሚያስተላልፉት ይዘት ላይ የአዝማሚያ ትንተና እንዲካሄድ በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት መረጃዎቹን ተንትኖ ረቂቅ ሰነዱን ያቀርባል፣
- በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት በተለያዩ ተቋማት ሞኒተር የተደረጉ ሚዲያ ውጤቶች ላይ ባስተላለፉት መልዕክትና በፈጠሩትን ተጽዕኖ የአዝማሚያ ትንተና በማድረግ የረቂቅ ሰነዱን ውጤት ያቀርባል፣

**ውጤት 3፡- የኮሙዩኒኬሽን ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ስራዎችን በጥናትና ምርምር በማገዝ ውጤታማ ማድረግ**

- ከባቢያዊ ቅኝት በማድረግ ጥናትና ምርምር የሚካሄድባቸው ጉዳዮች ይለያል፣ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም መረጃ ለመሰብሰበ የሚያስችሉ መጠይቆችን ያዘጋጃል፣ ተዘጋጅተው በቀረቡት መጠይቆችም ላይ ግብዓት በመጨመር ያዳብራል፣

- የጥናትና ምርምር ስራዎችን ለማገዝ የሚያስችል የፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ምክረ ሃሳብ (proposal) ያዘጋጃል፣ አማራጭ ፕሮጀከቶችን ይለያል፣ ለቡድኑም ያቀርባል፣
- የጥናትና ምርምር ተግባራትን ለማከናወን የሚረዳ የድርጊት መርሃግብር አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፣
- የጥናቱ የመጀመሪያ ረቂቅ በኃላፊው ታይቶ ሙያዊ አስተያየት ከተሰጠበት በኋላ ከተሰጠው አስተያየት ላይ በመነሳት የመጨረሻውን ጥናት አዘጋጅቶ ያቀርባል፣
- የኮሙኒኬሽንና የሚዲያ የጥናትና ምርምር ውጤቶችን በውጭ ለሚኖሩ ለክልሉ ተወላጆች ለማሠራጨት የሚያግዙ የሚዲያ አማራጮችን በመለየት ሥራዎቹን ተደራሽ ያደርጋል፣
- በመረጃ ማሰባሰብ ሂደት በጋራ የሚሠሩ ድርጅቶችን የክትትል ተግባራት ያከናውናል፣ በታዩ ጉድለቶች ላይ የማስተካከያ ሥራዎችን ይሰራል፣

- ለጥናትና ምርምር ሥራዎች ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የሚያስችል የሁለትዮሽ የስምምነት ሰነድ ያዘጋጃል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣
- ከተለያዩ የሚዲያ ተቋማት የሚቀርቡ የጥናትና ምርምር ፍላጎቶችን በመቀበል ጥናቱን በማድረግ ውጤቱን ለቡድኑ ያቀርባል፣
- በመረጃ ቋት መያዝ ያለባቸውን የጥናትና ምርምር ስራዎችን ያደራጃል፣ በመረጃ ቋት ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋል፣

**ውጤት 4፡- ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር የሚስፋፉበትን ስልት መቀየስ**

- ከተያዙ መረጃዎች ላይ በመነሳት ምርጥ ተሞክሮዎችን ይቀምራል፣ ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የሚስፋፉበትን ስልት ይቀይሳል፣
- ክልላዊ የኮሙዩኒኬሽን፣ ሚዲያና ኢንፎርሜሽን የጥራት ደረጃን ለማሻሻል የሚያግዙ  አዳዲስ ሃሳቦችን በማፍለቅ ከማብራሪያ ጋር ያቀርባል፣
- ለክልሉና ለዞኑ ተቋማትና ባለድርሻ አካላት የማማከር አገልግሎት ይሰጣል፣ በጋራም ይሠራል፡፡

## III. የሥራው ባህሪ መግለጫዎች

### 3.1 የሥራ ውስብስብነት

- *ሥራው በኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ የጥናትና ምርምር ሥራዎች የሚመሩበትን አዳዲስ የአሠራር መመሪያዎችን፣  ማንዋሎችና ስታዳርዶች ማዘጋጀትን፣ ነባሮችን መከለስን፣ የውጭ ሚዲያዎችን ከባቢያዎ ቅኝት በማድረግ ባቀረቡት ዘገባዎች ይዘት ላይ የአዝማሚያ ትንተና ማካሄድን፣ ሚዲያዎች ያስተላለፉትን መልዕክትና የፈጠሩትን ተጽዕኖ መተንተንን፣ የፕሮጀክት ማስፈጸሚያ አማራጭ ፕሮጀክቶችን ለይቶ ማቅረብንና አፈጻጸሙን መከታተልን፣ ጥናትና ምርምር የሚካሄድባቸውን ጉዳዮች መለየትን፣ የተለያዩ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም መጠይቆችን ማዘጋጀትን፣ ተዘጋጅተው በቀረቡት መጠይቆችም ላይ ግብዓት በመጨመር ማዳበርን፣  የጥናትና ምርምር ውጤቶችን  በውጭ ለሚኖሩ ለክልሉ ተወላጆች ለማሠራጨት የሚያግዙ የሚዲያ አማራጮችን ለይቶ ሥራዎቹን ተደራሽ ማድረግን፣ ለጥናትና ምርምር ሥራዎች ለማከናወን የተደረጉ የሁለትዮሽ ስምምነቶች አፈጻጸም መከታተልን፣ በመረጃ ማሰባሰብ ሂደት በጋራ የሚሠሩ ድርጅቶችን መከታተልንና በታዩ ጉድለቶች ላይ ማስተካከያ ማድረግን፣ ከተቋማት የሚቀርቡ የጥናትና ምርምር ፍላጎቶችን በመቀበል ጥናት ማካሄድን፣ ከአገር ውስጥና ከውጭ ምርጥ ተሞክሮዎች የሚቀመሩባቸውን አካባቢዎች በመለየት ቀምሮ የሚስፋፉበት ስልት መቀየስን፣ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን የጥራት ደረጃን ማሻሻልን የሚጠይቅ ሲሆን*
- *ሥራው በሚከናወንበት ወቅት ጥራቱን የጠበቀ መረጃ አለመገኘት፣ የተዘጋጁትም በኃላፊው ተቀባይነት ማጣት፣ ሚዲያዎች ባስተላለፉት መልዕክት የፈጠሩትን ተጽዕኖ ትንተና ሰነድ ላይ ወቅታዊ ምላሽ አለመሰጠቱ፣ አማራጭ የጥናት ፕሮጀክቶችን ለማወዳደር የተሟላ መረጃ ይዘው አለመቅረብ፣ በምልከታና በተተኳሪ ቡድን ውይይት መረጃዎች ለመሰብሰብ ሦስተኛው ወገን ፈቃደኛ ሆኖ አለመገኘት፣ የጥናትና ምርምር ውጤቶችን  በውጭ ለሚኖሩ ለክልሉ ተወላጆች ለማሠራጨት የሚያግዙ የሚዲያ አማራጮችን እንደልብ አለመገኘት፣ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ለማከናወን የተደረጉ የሁለትዮሽ ስምምነቶች በውሉ መሠረት ተፈጻሚ አለመደረጋቸው፣ ተቋማት እንዲጠኑላቸው የሚፈልጉ ሥራዎች የጥራት ደረጃውን የጠበቀ*

አለመሆንና ተቀባይነት ማጣት፣ ተሞክሮዎች የሚቀመሩባቸውን አካባቢዎች ለመለየት በቂ መረጃ አለማግኘትን፣ የደራሽ ሥራዎች ባልተጠበቀ ጊዜ መምጣት የሚያጋጥሙ ችግሮች ናቸው፡፡

- እነዚህንም ችግሮች ለመፍታት ተቀባይነትን ያገኘና ደረጃውን የጠበቀ መመሪያ፣ ማንዋልና የአፈጻጸም ስታንዳርድ ማዘጋጀት፣ ተዘጋጅተው የቀረቡ የትንተና ሰነዶች ተከታትሎ ወቅታዊ ምላሽ እንዲሰጣቸው በማድረግ፣ መረጃ ለሚሰጡ አካላት ተገቢውን ቅድመ ግንዛቤ በማስጨበጥ፣ የጥናት ውጤቶችን የሚሰራጭባቸውን የተለያዩ አማራጭ ሚዲያዎችን በመጠቀም፣ ከተለያዩ አካላት ጋር የሚኖረውን የሥራ ላይ ግንኙነት በማጠናከር፣ የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁና ተቀባይነት ያላቸውን የጥናት ሰነዶችን በማዘጋጀት፣ የራስን የመፈጸም አቅምን በመገንባት፣ የአገር ውስጥና የውጭ ተሞክሮዎችን በመቀመርና በማሰፋት እንዲሁም የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ ችግሮች ይፈታሉ፡፡

### 3.2 ራስን ችሎ መስራት

#### 3.2.1 ሥራው የሚከናወንበት አግባብ

- ሥራው በአጠቃላይ ደንቦች፣ መመሪያዎችና የአሠራር ማንዋሎች መሠረት ይከናወናል፡፡

#### 3.2.2ሥራው የሚጠይቀው የክትትልና ድጋፍ ደረጃ

- ሥራው ውጤታማ የሆነ የጥናት ስራዎችን ከማከናወን አንጻር በመጨረሻ ይገመገማል፡፡

### 3.3 ተጠያቂነት

#### 3.3.1 ተጠያቂነት ለሥራ ውጤት /Responsibility for Impact/፣

- ሥራው በኮሙዩኒኬሽንና ኢንፎርሜሽን ዘርፍ የጥናትና ምርምር ሥራዎች የሚመሩበትን የአሠራር መመሪያዎችንና ማንዋሎችን ማዘጋጀት፣ ለሥራ ቅልጥፍና የሚረዱ ስታዳርዶች ባያዘጋጅ፣ የውጭ ሚዲያዎችን በተመለከተ ከባቢያዎ ቅኝት በማድረግ ባቀረቡት ዘገባዎች ይዘት ላይ የአዝማሚያ ትንተና ማካሄድ፣ ጥናትና ምርምር በማካሄድ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ፣ በመረጃ ማሰባሰብ ሂደት በጋራ የሚሠሩ ድርጅቶችን የክትትል ተግባራት ማከናውን፣ በታዩ ጉድለቶች ላይ የማስተካከያ ሥራዎችን መስራት፣ ከተለያዩ የሚዲያ ተቋማት የሚቀርቡ የጥናትና ምርምር ፍላጎቶችን በመቀበል ጥናቱን ማካሄድ የሚጠይቅ ሲሆን በአግባቡ ባይከናወን ወይም የሚፈጠሩ ስህተቶች በወቅቱ እርማት ባይደረግባቸው የጥናትና ምርምር ሥራው መንግስት ለህብረተሰቡ ማስተላለፍ የሚፈልገውን መረጃ ወቅቱን ጠብቆ እንዳይደርስ ያደርጋል፣ የተዛቡ መልዕክቶችና መረጃዎች ለህብረተሰቡ ይደርሳሉ በዚህም በክልላዊ መግባባትና ገጽታ ግንባታ ሥራን ያስተጓጉላል፣ በተቋሙ ገጽታ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያስከትላል፡፡

#### 3.3.1 ተጠያቂነት ለሚስጥራዊ መረጃ፣

- ሥራው የጥናት ውጤቶችን የመያዝ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን፣ እነዚህ መረጃዎች በሚመለከተው አካል ውሳኔ አግኝተው ይፋ ከመደረጋቸው በፊት ለማይመለከተው አካል ተላልፈው ቢሰጡ በመንግስትና በህብረተሰቡ መካከል አለመግባባትን፣ በዘርፉ ባለሙያዎች መካከል አለመተማመንን ያስከትላል፡፡

3.4 ፈጠራ

- ሥራው አዳዲስ ሃሳቦችን በማፍለቅ፣ አዳዲስ የጥናትና ምርምር ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ተግባራዊ ማድረግን፣ መመሪያዎችን፣ የአሠራር ማንዋሎችንና የአፈጻጸም ስታንዳርዶችን በማዘጋጀት አሠራር ማሻሻልን ይጠይቃል፡፡

3.5. **የሥራ ግንኙነት** /Work Communication/

3.5.1 **የግንኙነት ደረጃ**

- ሥራው **ከውስጥ** ከቅርብ ኃላፊው፣ ከዘርፉ ባለሙያዎች፣ ከሌሎች ዳይሬክቶሬቶች ባለሙያዎች፣
- **ከውጭ** ከአገር ውስጥና ከውጭ ሚዲያ ተቋማት እና ዜና ወኪሎች፣ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ባለሙያዎችና ኃላፊዎች፣ ከመረጃ ሰጪ አካላት ጋር ግንኙነት ማድረግን ይጠይቃል፡፡

3.5.2 **የግንኙነቱ ዓላማ**

- የሥራ መመሪያ ለመቀበልና ሪፖርት ለማድረግ፣ ሥራን በጋራ ለመሥራት፣ ጥናትና ምርምር በጋራ ለማድረግ፣ መረጃ ለመስጠትና ለመቀበል ነው፡፡

3.5.3 **የግንኙነቱ ድግግሞሽ**

- ከቀን የሥራ ጊዜው እስከ 50 በመቶ ይሆናል፡፡

3.6 **ኃላፊነት**

3.6.1 **ኃላፊነት ለሰው ሀብት**

- የለበትም፡፡

3.6.1.1 **በኃላፊነት የሚመራቸው ሠራተኞች ብዛት**

- የለበትም፡፡

3.6.1.2 **የኃላፊነት አይነትና ደረጃ**

- የለበትም፡፡

3.6.2 **ኃላፊነት ለንዋይ**

- **የለበትም፡፡**

3.6.3 **ኃላፊነት ለንብረት**

- ለሥራ ማከናወኛ የሚሆን ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ ሼልፍ፣ ዴስክቶፕ ኮምፒውተር፣ ፕሪንተር፣ ላፕቶት፣ መቅረጸ

*ድምጽ፣ የፎቶ ካሜራ፣ በግምት እስከ ብር 50 ሺህ ብር የሚደርስ ንብረት እና ቴሌቪዥንና ሬድዮ በጋራ የመያዝና የመጠቀም ሃላፊነት አለበት፡፡*

**3.7. ጥረት**

**3.7.1 የአዕምሮ ጥረት**

- *ሥራው በኮሙዩኒኬሽንና ኢንፎርሜሽን ዘርፍ የጥናትና ምርምር ሥራዎች የሚመሩበትን የአሠራር መመሪያዎችንና ማንዋሎችን ያዘጋጃል፣ ተከልሰው እንዲዘጋጁ ውሳኔ የተሰጠባቸውን ነባር የአሠራር መመሪያዎችና ማንዋሎችን ክልሶ ማዘጋጀትን፣ ለሥራ ቅልጥፍና የሚረዱ ስታዳርዶች ማዘጋጅትን፣ የኮሙዩኒኬሽንና ኢንፎርሜሽን አሠራር በውጤታማነት ተፈጻሚ እንዲሆን የሚያስችሉ አዳዲስ ሃሳቦችን ማቅረብን፣ የውጭ ሚዲያዎችን በተመለከተ ከባቢያዎ ቅኝት በማድረግ ባቀረቡት ዘገባዎች ይዘት ላይ የአዝማሚያ ትንተና ማካሄድን፣ ሚዲያዎችን በዓይነትና በስያሜያቸው በመለየት ባስተላለፉት መልዕክትና የፈጠሩትን ተጽዕኖ በተወሰነ የጊዜ ልዩነት በመተንተን፣የጥናትና ምርምር ስራዎችን ለማገዝ የሚያስችል የፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ምክረሃሳብ (proposal) ማዘጋጀትን፣ አማራጭ ፕሮጀክቶችን ለይቶ በማቅረብ ማጸደቅን፣ ጥናትና ምርምር ተግባራትን ለማከናወን የሚረዳ የድርጊት መርሃግብር አዘጋጅቶ በማቅረብ ተግባራዊ ማድረግን፣ ጥናትና ምርምር የሚካሄድባቸውን ጉዳዮችን በመለየት የተሰበሰቡና የተደራጁ መረጃዎችን ተንትኖ ረቂቅ ጥናት ማቅረብን፣ የጥናቱ የመጀመሪያ ረቂቅ በኃላፊው ታይቶ ሙያዊ አስተያየት ከተሰጠበት በኋላ ከተሰጠው አስተያየት ላይ በመነሳት የመጨረሻውን ጥናት አዘጋጅቶ ማቅረብን፣ለጥናትና ምርምር ሥራዎች ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የሚያስችል የሁለትዮሽ የስምምነት ሰነድ ማጋጀትና አፈጻጸሙንም መከታተልን፣ ከተለያዩ የሚዲያ ተቋማት የሚቀርቡ የጥናትና ምርምር ፍላጎቶችን በመቀበል ጥናቱን ማድረግን ፣ ከተያዙ መረጃዎች ላይ በመነሳት ምርጥ ተሞክሮዎችን ይቀምራል፣ ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የማስፋት ተግባርን ማከናወንን፣ ክልላዊ የኮሙዩኒኬሽን፣ ሚዲያና ኢንፎርሜሽን የጥራት ደረጃን ለማሻሻል የሚያግዙ አዳዲስ ሃሳቦችን በማፍለቅ ከማብራሪያ ጋር ማቅረብን፣ ለፌዴራል፣ ለክልል ተቋማትና ባለድርሻ አካላት የማማከር አገልግሎት መስጠትና በጋራ መስራትን የሚጠይቅ ሲሆን ይህም ከቀን የስራ ጊዜው እስከ 75 በመቶ ይሆናል፡፡*

**3.7.2. ስነ ልቦናዊ ጥረት**

- በፕሮጀክት ዝግጅትና በሁለትዮሽ ስምምነት ወቅት አለመግባባቶች እንድሁም የዳሰሳ ጥናት በሚደረግበት ወቅት ከተለያዩ አካላት ማስፈራሪያና ዛቻ ሊደርስበት በሚችልበት ሁኔታ ይከናወናል እነዚህን ተቋቁሞ ስራን በተረጋጋና በሰከነ መንፈስ ማከናወንን ይጠይቃል

**3.7.3 የዕይታ ጥረት፣**

- *ሥራው ፕሮጀክቶችን መቅረጽ፣ መመሪያዎችን ማዘጋጀት፣ የተለያዩ የጥናት ጽሁፎችን ማንበብና ለሁለትዮሽ ስምምነት የሚሆኑ ሰነዶችን ማዘጋጀትን የሚጠይቅ ሲሆን ይህም ከቀን የስራ ጊዜዉ እስከ 40*

በመቶ ይሆናል፡፡

3.7.4 የአካል ጥረት

- ስራዉ 80 በመቶ በመቀመጥ፣ 20 በመቶ በመንቀሳቀስ ይከናወናል፡፡

3.8. የሥራ ሁኔታ

3.8.1. ሥጋትና አደጋ

- የለበትም፡፡

3.8.2. የሥራ አካባቢ ሁኔታ

- ሥራዉ ምቹ በሆነ አካባቢ ይከናወናል፡፡

3.9. እውቀትና ክህሎት፣

3.9.1. ትምህርት

| የትምህርት ደረጃ | የትምህርት ዓይነት |
|---|---|
| የመጀመሪያ ዲግሪ | በኮሚዩኒኬሽንና ጋዜጠኛነት፣ ፖለቲካል ሳይንስና አለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቋንቋና ስነ-ጽሁፍ፣ ስራ አመራር፣ ሶሺዮሎጂ እና ሶሻል አንትሮፖሎጂ ቢዝነስ አድምንስትሬሽን፣ ኢኮኖሚክስ ታሪክ በመጀመሪያ ዲግሪ ከስራው ጋር ግንኙነት ያለው 4 ዓመትየሥራ ልምድ ያለው /ያላት/ መሠረታዊ የኮምፒዩውተር እውቀትያለው /ያላት/ |

3.9.2 ሥራውን ለመጀመር የሚያስፈልግ የሥራ ልምድ

| የሥራ ልምዱ ለማግኘት የሚጠይቀው ጊዜ | ልምዱ የሚገኝበት የሥራ ዓይነት |
|---|---|
| በመጀመሪያ ዲግሪ 4 አመት | በኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ጥናትና ምርምር የልህቀት ማዕከላትና ከስራው ጋር ተያያዥነት ያለው በጥናትና ምርምር የተገኘ ልምድ |

| የሥራ ትንተና ባለሙያ ሥም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| | | |

| የሥራ ዝርዝሩን ያጸደቀው የኃላፊው ሥም | የሥራ መደቡ መጠሪያ | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| | | | |